# መሠረተ ሕይወት

## በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልጆች መማሪያ መጽሐፍ

## ስድስተኛ ክፍል

አዘጋጅ - ቀሲስ ሰሎሞን መሉጌታ

www.zeorthodox.org

ነሐሴ ፳፻፮ ዓ.ም

© ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ ዘውዴ ፳፻፮ ዓ.ም

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
ALL RIGHTS RESERVED

# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን እምነት፣ ሥርዓት እና ትውፊት መሠረት በማድረግ የተዘጋጀ ሥርዓተ ትምህርት

አድራሻ፡-
ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ ዘውዴ
ፖ.ሳ.ቁ 43200
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

Email:- kesisolomon@gmail.com
Website;-www.zeorthodox.org

የኮምፒውተር ሌይ አውት ዲዛይን
ልደት አስፋው

## ማሳሰቢያ

www.zeorthodox.org

ይህ መጽሐፍ ተሰራጭቶ የሚገኘው ገቢ በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም፣ በቦሌ ደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል፣ በቦሌ ሰሚት መካነ ሰላም መድኃኔዓለም እና ወደ ፊትም በተለያዩ አጥቢያዎች ለሚከናወኑ የሕፃናት፣ አዳጊዎች፣ ወጣቶችና ወላጆች ኦርቶዶክሳዊ ትምህርትና ተመሳሳይ አገልግሎቶች የሚውል ይሆናል፡፡

# መታሰቢያነቱ

ለአቃቂ መንበረ ሕይወት መድኃኔዓለም

ቤተ ክርስቲያን ካህናት፣ ዲያቆናት፣

የሰንበት ት/ቤት አባላትና ምዕመናን

ይሁንልኝ፡፡

# ምስጋና

ይህ የመማሪያ መጽሐፍ ሲዘጋጅ በቀጥተኛ ተሳታፊነት የተሰለፉትን ዲ. ዘላለም ረድኤትና ዲ. ዮናታን ኢያሱን፣ መጽሐፉን በማረም የተባበሩትን መጋቤ ብሉይ አእመረ አሸብርን፣ መምህር ካሕሳይ ገብረ እግዚአብሔርን፣ ዲያቆን ዳንኤል ክብረትን፣ እና አቶ አስራት ከበደን እንዲሁም በኮምፒዩተር የለቀማ ሥራ ያገለገሉትን ልደት አስፋውን፤ መጻሕፍቱን ለማጠናቀቅ ሳደርግ በነበረው ጥረት ውድ ባለቤቴና ልጆቼ የእንቅልፍና የእረፍት ሰዓታቸውን ሳይቀር መሥዋዕት በማድረግ ስላሳለፉ ስለ ከፈሉት መሥዋዕትነት እግዚአብሔር ዋጋ ከፋይ ነውና ዋጋቸውን ይክፈላቸው እላለሁ፡፡ በመጨረሻም የሚያስፈልገውን ሁሉ የሚያከናውኑ የመርሐ ግብራችን አስተባባሪ የጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ሰንበቴ የሥራ አስፈጻሚ

www.zoorthodox.org

# ማውጫ



| ተ.ቁ. | አርእስት | ገጽ | ወር | ሳምንት | ልዩ በዓል |
|---|---|---|---|---|---|
| | **መቅድም** | I | | | |
| | **መግቢያ** | III | | | |
| 1. | የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ቲቶ | 1 | | አንደኛ | |
| 2. | ትንቢተ ዓሞጽ | 3 | | ሁለተኛ | |
| 3. | ጸሎተ ሠለስቱ ደቂቅ | 5 | | ሦስተኛ | |
| 4. | መጽሐፈ ሶስና | 7 | | አራተኛ | |
| 5. | መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት እናነባለን | 9 | | አምስተኛ | |
| 6. | ቁስቋም | 11 | | ስድስተኛ | |
| 7. | አስተርዮ ማርያም | 13 | | ሰባተኛ | |
| 8. | መምህር ኤስድሮስ | 15 | | ስምንተኛ | |
| 9. | ዘመነ ሐዋርያነ አበው (100-160) ፩ | 16 | | ዘጠነኛ | |
| 10 | ዘመነ ሐዋርያነ አበው (100-160) ፪ | 18 | | ዐሥረኛ | |
| 11. | ዘመነ ሐዋርያነ አበው (100-160) ፫ | 20 | | ዐሥራ አንደኛ | |
| 12. | ሃይማኖት ቅድመ ክርስትና በኢትዮጵያ | 22 | | ዐሥራ ሁለተኛ | |
| 13. | ሀልዎተ እግዚአብሔር | 24 | | ዐሥራ ሦስተኛ | |
| 14. | ባሕርየ እግዚአብሔር | 26 | | ዐሥራ አራተኛ | |
| 15. | ተአምራት | 28 | | ዐሥራ አምስተኛ | |
| 16. | ሰሎሞን የእግዚአብሔርን መቅደስ ሠራ | 30 | | ዐሥራ ስድስተኛ | |
| 17. | ተስፋ መቁረጥ | 32 | | ዐሥራ ሰባተኛ | |
| 18. | ኤልያስ የመበለቷን ልጅ ከሞት አስነሣ | 34 | | ዐሥራ ስምንተኛ | |
| 19. | አባ ጽጌ ንድግል | 36 | | ዐሥራ ዘጠነኛ | |
| 20. | ኢትዮጵያዊው ሙሴ | 38 | | ሃያኛ | |
| 21. | ቅዱሳን መላእክት ሎጥን ከሰዶም አወጡት | 40 | | ሃያ አንደኛ | |
| 22. | የተፈጥሮ አደጋዎች | 42 | | ሃያ ሁለተኛ | |
| 23. | ትዕግሥት | 44 | | ሃያ ሦስተኛ | |
| 24. | እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሰጠው ተስፋ ተፈጸመ | 46 | | ሃያ አራተኛ | |
| 25. | በኢያሱ መሪነት የተደረጉ ጦርነቶች | 48 | | ሃያ አምስተኛ | |
| 26. | ኢያሱ ለሕዝቡ ርስት አከፋፈለ | 50 | | ሃያ ስድስተኛ | |
| 27. | ክፉ ልማድ | 52 | | ሃያ ሰባተኛ | |



www.zeorthodox.org

| ተ. ቁ. | አርእስት | ገጽ | ወር | ሳምንት | ልዩ በዓል |
|---|---|---|---|---|---|
| 28. | ስንፍና | 54 | | ሃያ ስምንተኛ | |
| 29. | ስደት | 56 | | ሃያ ዘጠነኛ | |
| 30. | የንግግር ችሎታን ማሳደግ | 58 | | ሠላሳኛ | |
| 31. | የሐዲስ ኪዳን መግቢያ ፩ | 60 | | ሠላሳ አንደኛ | |
| 32. | የሐዲስ ኪዳን መግቢያ ፪ | 62 | | ሠላሳ ሁለተኛ | |
| 33. | የሐዲስ ኪዳን መግቢያ ፫ | 64 | | ሠላሳ ሦስተኛ | |
| 34. | የሴት ክብር | 66 | | ሠላሳ አራተኛ | |
| 35. | ክርስቶስ ሰው የሆነበት ምስጢር | 68 | | ሠላሳ አምስተኛ | |
| 36. | ክፉ ቅናት | 70 | | ሠላሳ ስድስተኛ | |
| 37. | ቃና ዘገሊላ | 72 | | ሠላሳ ሰባተኛ | |
| 38. | ጌዴዎን | 74 | | ሠላሳ ስምንተኛ | |
| 39. | የሰርጉ ቤት ጥሪ | 76 | | ሠላሳ ዘጠነኛ | |
| 40. | ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የደቀ መዛሙርቱን እግር አጠበ | 78 | | ዐርባኛ | |
| 41. | ሰሙነ ሕማማት (መከራ እግዚእ) | 80 | | ዐርባ አንደኛ | |
| 42. | የክርስቶስ መስቀል | 82 | | ዐርባ ሁለተኛ | |
| 43. | የተለሰነ መቃብር | 84 | | ዐርባ ሦስተኛ | |
| 44. | እስራኤል በተስፋይቱ ምድር | 86 | | ዐርባ አራተኛ | |
| 45. | ከሰዎች ጋር ተግባብቶ መኖር | 88 | | ዐርባ አምስተኛ | |
| 46. | ድህነት | 90 | | ዐርባ ስድስተኛ | |
| 47. | ስሕተትን ማመን | 92 | | ዐርባ ሰባተኛ | |
| 48. | ወጣትነት፡- አካላዊ ዕድገት ፩ | 94 | | ዐርባ ስምንተኛ | |
| 49. | ወጣትነት፡- የጉልምስና ጊዜ ፪ | 96 | | ዐርባ ዘጠነኛ | |
| 50. | ወጣትነት፡- ራስን መቀበል ፫ | 98 | | ሃምሳኛ | |

www.zeorthodox.org

# መቅድም

በአሁኑ ወቅት በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጪ የሚገኙ ኦርቶዶክሳውያን ሕፃናት፣ አዳጊዎችና ወጣቶች ቤተ ክርስቲያናቸውን እያወቁ በመልካም ሥነ ምግባር ታንጸው እንዲያድጉ የሚያደርግ፣ ጥያቄዎቻቸውን የሚመልስ ብሎም ችግሮቻቸውን የሚፈታ መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት የመኖሩ አስፈላጊነት በብዙዎቻችን ዘንድ ይታመንበታል፡፡ ቤተ ክርስቲያናችንም በዚሁ ዙሪያ በርካታ ተግባራትን እንደምታከናውን እምነቴ ነው፡፡

ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ቤተ ክርስቲያን በመላክ ለተስተካከለ ዕድገታቸው አስተዋጽዖ በማድረግ የወላጅነት ሓላፊነታቸውን ለመወጣት ፍላጐቱ አላቸው፡፡ ሆኖም በአንዳንድ ሁኔታዎች አለመመቻቸት የተነሣም ይሁን በሌላ ምክንያት ከሕፃንነታቸው ጀምሮ እንዲማሩላቸው ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚያቀርቡ ምእመናን እጅግ ጥቂቶች መሆናቸውን የተለያዩ አጋጣሚዎች ማሳያዎች ሆነውኛል፡፡

ከዛሬ ሰባት ዓመት በፊት በእግዚአብሔር ፈቃድ በምሥራበት መሥሪያ ቤት በኩል ለተዘጋጀ ሙያዊ ሥልጠና ከአገር ውጪ ባደረግሁት ጉዞ ዘወትር አብረውኝ የሚቆሙ ቤተሰቦቼ ምክንያት ሆነው ግብጽንና ገዳማቱን የመጐብኘት ዕድል አገኘሁ፡፡ ይህም የተቀደሰ አጋጣሚ ስለ ልጆች፣ በቅድመ ጋብቻ ስላሉ ወጣቶችና በትዳር ስለሚኖሩ ኦርቶዶክሳዊያን የተናጠል መርሐ ግብር እንዳስብ አደረገኝ፡፡ በእግዚአብሔር ፈቃድም በኅዳር ወር ፲፱፻፺፱ ዓ.ም. በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም መጥምቀ ዮሐንስና አቡነ አረጋዊ ቤተክርስቲያን የልጆች መርሐ ግብር በሃያ አራት ልጆች ተጀመረ፡፡ አሁን ከሙዓለ ሕፃናት እስከ አሥራ ሁለተኛ ክፍል የሆኑ ከሦስት ሺህ በላይ የሚሆኑ ልጆች፤ በየሳምንቱ ቅዳሜና እሑድ ቀን ከአራት እስከ ስድስት ሰዓት በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋ የሚሰጠውን መንፈሳዊ ትምህርት ይከታተላሉ፡፡ በርካታ ምእመናንም በየሳምንቱ ረቡዕ ከምሽቱ አሥራ ሁለት እስከ ሁለት ሰዓት ለአዋቂዎች በተዘጋጀው የትምህርት መርሐ ግብር ተሳታፊዎች ናቸው፡፡

ይሁን እንጂ ሁሉንም ልጆች በየትምህርት ደረጃቸው በመመደብ ማስተማር የሚያስችል መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት ማዘጋጀቱ አስፈላጊ ነበር፡፡ በመሆኑም ቀድመው የተዘጋጁትን ትምህርቶች ተካተውበት ለዚሁ ሥራ እገዛ የሚያደርጉ ወንድሞች ጋር በመመካከር ዲያቆን ዮናታን ኢያሱ እና ዲያቆን ዘላለም ረድኤት ተገኝተውበት ለትምህርቱ አጋዥ የሆኑ መጻሕፍትን ለማዘጋጀት ጥረት ተጀመረ፡፡ እግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ ከአራት ዓመታት ጥረት በኋላ፤ ለሥርዓተ ትምህርቱ አጋዥ የሆኑ ከሙዓለ ሕፃናት እስከ አሥራ በኋላ አጋዥ የሆኑ ከሙዓለ ሕፃናት እስከ አሥራ ሁለተኛ

www.zoorthodox.org

ክፍል ድረስ የሆኑ አሥራ ሦስት ጥራዝ የማስተማርያ መጻሕፍት ዝግጅት ተጠናቅቆ ለኅትመት እንዲበቁ ለማድረግ ወደ ማተሚያ ቤት ገብተዋል፡፡

በማስተማርያ መጻሕፍቱ ዝግጅት፤ ለመረጃ የምንገለገልባቸው ምንጮች፣ የምእመናን የኑሮና የትምህርት ደረጃ፣ የመኖሪያ ሥፍራዎችና የባህል ልዩነቶች፣ እንዲሁም በአገር ውስጥ እና ከሀገር ዉጪ በሚገኙ ኢትዮጵያዊያን መካከል ያሉ የአኗኗርና የሥራ ሁኔታዎችና አካባቢያዊ ልዩነቶችን ታሳቢ በማድረግ ከግንዛቤ ውስጥ እንዲገቡ ተሞክሮአል፡፡ በዚህ ሥራ ቀጥተኛ ተሳትፎ ላደረጉት ለዲያቆን ዮናታን ኢያሱ እና ለዲያቆን ዘላለም ረድኤት፤ እግዚአብሔር በቸርነቱ ጠብቆ ረጅም ዕድሜ ይስጥልን እላለሁ፡፡

ይኸው የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ ከሙዓለ ሕፃናት እስከ ዐሥራ ሁለተኛ ክፍል ድረስ ላሉ ወጣቶች ለሚሰጠዉ ‹‹መሠረተ ሕይወት›› መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት ማስተማሪያ የሚሆኑ መጻሕፍት ለኅትመት በቅተዉ ለአገልግሎት የተዘጋጁ መሆናቸውን በታላቅ ደስታ እገልጻለሁ፡፡

***“እስከ አሁን ድረስ እግዚአብሔር ረድቶናል፡፡” ፩ኛ ሳሙኤል ፯ ፥ ፲፪***

www.zeorthodox.org

# መግቢያ

የዚህ መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት ምንጭ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ሌሎችም የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍትና ትውፊተ ቤተክርስቲያን ናቸው፡፡ በዚህም መሠረት ጥርት ያለውን የቅድስት ቤተ ክርስቲንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ታሪክ ከመልካም ሥነ ምግባር ጋር፤ በዓለማዊ ትምህርት ቤት ለሚማሩ ሕፃናት፣ አዳጊዎችና ወጣቶች እንዲደርስ ለማድረግ፤ በየትምህርት ደረጃቸው እና ዕድሜአቸው እንዲመጥን ሆኖ የሥርዓተ ትምህርት አዘገጃጀትን ስልት በመከተል ለማዘጋጀት ተሞክሮአል፡፡ አንዳንዶቹ ትምህርቶች ልጆች ትምህርቱን በሚገባ ተረድተዉ ማስታወስ እንዲችሉ በየደረጃዉ በሚገኙ የተለያዩ ክፍሎች ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ በድጋሚ ተካትተዋል፡፡

ትምህርቶቹ በየወሩ ተከፋፍለው በቤተ ክርስቲያን ከሚከበሩ በዓላትም ጋር እየተቀራረቡ እንዲዘጋጁ ጥረት ተደርጎአል፡፡ በየመካከሉ ለሚኖሩ ክፍተቶች በሁሉም አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት በቅደም ተከተል አገልግሎት ላይ እንዲውል ሆኖ የማሚያ ትምህርቶቹ ተወስደው ተካትተዋል፡፡ ያም ሆኖ እንደየ ጊዜው ሁኔታ ዘመኑን እንዲዋጅ መሻሻልና መዳበር ያለበት መሆኑ ግን የማይዘነጋ ነው፡፡

በሙዓለ ሕፃናት የሚገኙ ልጆች በጣም አጫጭር ታሪኮችን ብቻ ሰምተው ጥቂቶቹን ብቻ ማስታወስ የሚችሉ ናቸው፡፡ ረጅም ጽሑፍና ሐሳብ በትኩረት አንብበዉ በቀላሉ ለመረዳትም ሆነ ለማስታወስ ስለማይችሉ ወይም ስለሚቸገሩ በመምህራን እንዲሁም በወላጆች መታገዝ ያስፈልጋቸዋል፡፡ በተረት፣ በታሪክ፣ በሕልምና በእውነታ መካከል ያለውን ልዩነት አገናዝቦ ለመረዳት ይቸገራሉ፡፡ በጣም ፈጠራ የታከለባቸው የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎች የሚያስፈልጓቸው ቢሆኑም መምህራ ኖቻቸው የሚዘምሩላቸዉን መዝሙሮች ማስታወስና በአእምሮአቸው መያዝ፣ በትምህርታዊ ጨዋታዎቻቸውም ሆነ በማንኛውም ሁኔታ መምሰልና ማስመሰል ይችላሉ፡፡ በዚህ ደረጃ የሚገኙ ልጆች የሚንቀሳቀሱና የተለያዩ ድምፆች ያሉባቸውን ነገሮች እንዲሁም ከሌሎች ጋር መጫወትንና ያዩትን በተግባር ማሳየትን ይወዳሉ፡፡

ልጆች ቤተ ክርስቲያን መምጣታቸው ደስታን እንዲፈጥርላቸውና ፈጽመውም የሚወደዱ መሆናቸውን እንዲሰማቸው ማድረግ እንጂ ቶሎ ሊያስደነግጣቸው ወደ ሚችል አቀራረብና ቅጣት ማዘንበል አይገባም፡፡ በየደረጃው የሚገኙ ልጆችን የሚያስተምሩ መምህራን በተፈጥሮ ለልጆች ፍቅር ያላቸውና ፍቅራቸውንም መግለጽ የሚችሉ መሆን ይገባቸዋል፡፡ በዚህ ትምህርት የሚጠበቁ መልካም ውጤቶችም በሚቀርቡላቸው መርጃዎችና በመምህራኑ ጥረት ላይ የተመረኮዙ ናቸው፡፡ መምህራኑ

www.zeorthodox.org

ልጆችን ለመሳብ ብሩህ ፈገግታና ፍቅር ያለው አቀራረብ እንዲሁም፤ ደመቅ ያሉ ቀለማትን፣ ድምፅና ተንቀሳቃሽ ምስሎችን ቢጠቀሙ መዝሙራትንም ቢያዘምሩላቸው ለትምህርቱ ታላቅ ኃይል ይሆናል። ከሥርዓተ ትምህርቱ ጋር መምህራን ልጆቹን በየዕለቱ የትምህርት መርሐ ግብሮች መዝሙራትን ሊዘምሩላቸውና ሊያስጠኑአቸው ያስፈልጋል። አንዳንድ ጊዜም ከትምህርቱ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ሥዕላትን ቢያሳዩአቸዉ፣ ቢሰጡአቸው የተማሩትን ትምህርት በቀላሉ ለማስታወስና ለሌሎችም ለማስረዳት የበለጠ ዕድል ይፈጥርላቸዋል። አንዳንድ ጊዜ ቤተሰቡ ሁሉ ወደ ቤተክርስቲያን እንዲመጣ ልጆች ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉና። ይህንኑ ለማገዝም በቀለም የሚቀቡ ሥዕሎችና የመዝሙር ጥራዞችን ዝግጅት አጠናቀናል። በሙዓለ ሕፃናት ደረጃ የሚገኙ ልጆች ከትምህርታቸዉ ጋር ተያያዥነት ያለውን ርእሰ ጉዳይ ሥዕሉን ቀለም በመቀባት የሚቀስሙት ትምህርት የበለጠ ስለሚሆን የተዘጋጁትን ሥዕሎች በአግባቡ ቀለም እንዲቀቡአቸው የወላጆች እገዛ እጅግ አስፈላጊ ነው።

በዓመቱ ውስጥ ባልተካተቱት ሁለት ሳምንታትም ገዳማትንና አብያተ ክርስቲያናትን መጐብኘታቸውና ክትትል ባለበት ሁኔታ በማኅበራዊ ነገሮች ተሳታፊ መሆናቸውም እጅግ ጠቃሚ ነው። ከሁሉም በላይ ግን መምህራን ለዚህ አገልግሎት በትጋት መጸለይና በየመካከሉ የሚቀሩ ወይም ጨርሰው ያልመጡ ልጆችንም መጐብኘት ይጠበቅባቸዋል። መምህራንን ማግኘት በማይቻልባቸው ሥፍራዎች ወላጆች በሥርዓተ ትምህርቱ በመመራት ልጆችን ማስተማር ይችላሉ። ልጆች በመንፈሳዊው ትምህርት እስከአሁን ድረስ ያደጉበት ሁኔታ ያልተመጣጠነ ስለሆነ የክፍል ደረጃቸው ከፍ ቢልም ከሙዓለ ሕፃናት መጽሐፍ ደረጃ ጀምረው መማራቸው ለመንፈሳዊዉ ዕዉቀታቸዉ መሠረት ስለሆነ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል። በዚህ አጋጣሚም በየአብያተ ክርስቲያናቱ የተከፈቱ ትምህርት ቤቶችም ይህንን ሥርዓተ ትምህርት መጠቀማቸው ልጆች በየደረጃው ቤተ ክርስቲያናችንን እያወቁ፣ ሃይማኖታቸውን ተረድተውና በበጐ ሥነ ምግባር ታንጸው እንዲያድጉ የሚረዳቸው ይሆናል ብዬ አምናለሁ።

በመጨረሻም ይኸን ዝግጅት የበለጠ ለማሻሻል የሁሉም አስተያየትና ምክር በጣም አስፈላጊ ስለሆነ እገዛችሁ እንዳይለየኝ እያልኩ አስቀድሞ በተጠቀሱት አድራሻዎች አስተያየቶቻችሁን እንድትልኩልኝ ስል በታላቅ ትሕትና እጠይቃለሁ።

www.zeorthodox.org

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ቲቶ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ቲቶ የላከውን መልእክት ይዘት እንዲያውቁ ማድረግ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** "ሰዎችን የሚያድን የእግዚአብሔር ጸጋ ተገልጦአል" ቲቶ. ፪÷፲፩

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ዕብ. ፲፩÷፴፯-፴፰ እና (ሃይማኖተ አበው ዘቅዱስ ቄርሎስ)

## መግቢያ

ቲቶ የቅዱስ ጳውሎስ ደቀ መዝሙር ነው፡፡ ቲቶ የግሪክ ሰው ሲሆን በኤፌሶንና በቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን በወንጌል ሥራ ከእነ ጢሞቴዎስ ጋር አብሮ ነበር፡፡ ቲቶ ኃላፊነቱን በሚገባ የተወጣ የመደመጥም ችሎታ የነበረው አገልጋይ ነው፡፡ ፪ቆሮ. ፯÷፮-፯፡፡ ቲቶ በቀርጤስ ቤተ ክርስቲያን እንዲያስተምር ቅዱስ ጳውሎስ መድቦታል፡፡ ቲቶ.፩÷፭-፯፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለመንፈስ ልጁ ለቲቶ ሦስት ምዕራፎች ያሉት መልእክት ጽፎለታል፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ቲቶ ከቅዱስ ጳውሎስ ዐሥራ አራት መልእክታት አንዱ ነው፡፡ የታሪክ መዛግብት እንደሚያመለክቱት ቅዱስ ጳውሎስ በሦስተኛው ሐዋርያዊ ጉዞ ቲቶ በኤፌሶንና በቆሮንቶስ አብያተ ክርስቲያናትን እንዲያጠናክር ልኮታል፡፡ በመጨረሻም በቀርጤስ ጳውሎስ የጀመረውን የወንጌል ሥራ እንዲፈጽም መታዘዙን መልእክቱ ይገልጻል፡፡ ቲቶ. ፩÷፭፤ ፪÷፲፭፡፡ ስለዚህ ቲቶ የምእመናን መምህርና የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር መሪ የመሆኑ ትምህርተ ኖሎት በሰፊው በሦስቱም ምዕራፎች ተገልጿል፡፡

**የመልእክቱ ጸሐፊ፡-** የመልእክቱ ጸሐፊ ቅዱስ ጳውሎስ ነው፡፡ ቲቶ.፩÷፩፡፡

**የመልእክቱ ዓላማ፡-** የተቃዋሚዎችን ተቃውሞ መቋቋም የሚያስችል ሥልጣንና መመሪያ ለቲቶ መስጠት ነበር፡፡ ቲቶ የምእምናንን እና የአገልጋዮችን ሕይወት የሚዋጅ መልእክት ነው፡፡

www.zoorthodox.org

**መልእክቱ የተጻፈበት ጊዜ፡-** ከ፷፫-፷፭/63-65/ ዓ.ም ባለው ጊዜ እንደጻፈ የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ፡፡

**የመልእክቱ ልዩ ባሕርይ፡-** ይህ መልእክት በቀርጤስ የነበረውን የሐሰት ትምህርት በማረም

በተክክለኛው ትምህርተ ወንጌል እንዲስተካከል ሲሆን ይኸውም “መልካም የሆነውን ማድረግ” በሚለው የክርስትና መሠረታዊ ትምህርት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡

**የመልእክቱ ተደራሲ፡-** የሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ደቀ መዝሙር የሆነው የመንፈስ ልጁ ቲቶ ነው፡፡ ቲቶ. ፩÷፬ “በሃይማኖት ኅብረት እውነተኛ ልጄ ለሚሆን ለቲቶ” በማለት ቅዱስ ጳውሎስ መስክሮአልና፡፡

## የመልእክቱ አከፋፈል፡-

ምዕራፍ ፩÷፩-፬፡ ሰላምታ፤

ምዕራፍ ፩÷፭-፱፡- ስለ ቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች የተሰጠ የመመዘኛ መመሪያ፤

ምዕራፍ ፩÷፲-፲፮፡- የሐሰት መምህራን ባሕርይ፤

ምዕራፍ ፪፡- የመልካም አርአያነት አስፈላጊነት፤

ምዕራፍ ፫÷፩-፪፡- የዜግነት ግዴታ፤

ምዕራፍ ፫÷፫-፰፡- ለመንፈሳዊ ሕይወት አነሣሽ ምክንያት፤

ምዕራፍ ፫÷፱-፲፩፡- ለስሑታን የተሰጠ ምላሽ፤

ምዕራፍ ፫÷፲፪-፲፭፡- ማጠቃለያ፤

## ማጠቃለያ

ቲቶ ግሪካዊ ዜግነት ያለው የቅዱስ ጳውሎስ የመንፈስ ልጅ፤ እውነተኛም ደቀ መዝሙር ነው፡፡ በቆሮንቶስ የጳውሎስ ተወካይ የነበረ፤ በኤፌሶን ያስተማረ፤ በቀርጤስ ቤተ ክርስቲያንን ያደራጀ፤ በአድራሻው መልእክት የተጻፈለት አገልጋይ ነው፡፡ የቲቶ መልእክት ስለቤተ ክርስቲያን አስተዳደር፣ ስለአማኞች ሕይወት፣ ስለአገልጋዮች ሹመትና ከኃጢአት ኃይል ሊያወጣን ስለተገለጠው የእግዚአብሔር ጸጋ ሰፊ ትንታኔ ይሰጣል፡፡

## ተግባር

- መምህሩ ወጣቶች የቲቶን መልእክት እንዲያጠኑ ይጋብዝ፡፡

www.zeorthodox.org

# ትንቢተ አሞጽ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ስለ ትንቢተ አሞጽ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ

**የሚጠና ጥቅስ፡-** "እኔን ፈልጉ በሕይወትም ትኖራላችሁ፡፡" አሞ. ፭÷፬

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ትንቢተ አሞጽ ከምዕራፍ ፩ እስከ ፱

## መግቢያ

አሞጽ በዳግማዊ ኢዮርብአም ዘመነ መንግሥት (783-746 ዓ.ዓ) በእስራኤል ያገለገለ ነቢይ ነው፡፡ አሞጽ በእግዚአብሔር ከመጠራቱ በፊት ላም ጠባቂና የዋርካ ፍሬ ለቃሚ ነበር፡፡ አገሩ ከቤተልሔም ዐሥር ኪ.ሜ ያህል ርቃ የምትገኘው የቴቁሔ ከተማ ናት፡፡ አሞጽ በአገልግሎቱ በምቾትና በግድ የለሽነት የሚኖሩትን የሰማርያን ሰዎች በጽኑ ገሠጻቸው፡፡ ግፍና ጣዖት አምልኮን ትተው ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱና በሕይወት እንዲኖሩ መከሮአል፡፡ የአሞጽ የትንቢት መጽሐፍ በፍርድ ቃል የተሞላ ነው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

አሞጽ የቴቁሔ ሰው ነበር፡፡ አሞ. ፩÷፩፡፡ በቤቴል አካባቢ አገልግሏል፡፡ አሞ. ፯÷፲-፲፫፡፡ ለደቡባዊውም ለሰሜናዊውም የእስራኤል መንግሥት ተደራሽ የመጽናናትና የፍርድ ቃል አምጥቷል፡፡

**የትንቢቱ መጽሐፍ የተጻፈበት ጊዜ፡-** ትንቢቱ የተጻፈው ከ/760-746/ ዓ.ዓ በዳግማዊ ኢዮርብዓምና በንጉሥ ኦዝያን ዘመነ መንግሥት እንደነበር የታሪክ መዛግብት ይመሠክራሉ፡፡

**የትንቢቱ ቃል ዓላማ፡-** እስራኤላውያን ከዓለም የቅንጦትና የግፍ ኑሮ በመላቀቅ ወደ እግዚአብሔር ዘወር እንዲሉ ማድረግ ነው፡፡ የፍትሕ ርኃብ ላለባቸው ድሆች የቆመው አሞጽ ሕዝቡ ፍትሕ በሰፈነበት ሥርዓት እንዲኖር ታግሏል፡፡ አገልግሎቱ በእግዚአብሔር ፍርድና ጽድቅ፤ ቸርነት እና ጸጋ፤ ምሕረትና ይቅርታ ላይ ያተኩራል፡፡

## የትንቢቱ መጽሐፍ አከፋፈል፡-

ምዕራፍ ፩÷፩-፳፫፡- ፍርድ በእስራኤል አጎራባች አገሮች ላይ፤

www.zeorthodox.org

ምዕራፍ ፪÷፮-፲፮ ፍርድ በእስራኤል ላይ፤

ምዕራፍ ፫÷፩-፲፮÷፲፬፡- የፍርዱ ምክንያት

ምዕራፍ ፯÷፩-፱÷፲ የፍርዱ አምስት ዓይነት መንገድ

ምዕራፍ ፱÷፲፩-፲፭፡- በፍጻሜ ዘመን ስላለው ተስፋ (የዳዊት ቤት እንደገና የመነሣት ተስፋ)

አሞጽ የሕዝቡን ማኅበራዊ ኑሮ ስለሚያውቅ ሙስናን፣ የፍትሕ መጓደልን፣ የድሆች መበደልን፣ የነጋዴዎችን አለአግባብ ዋጋ መቀበል እና የባለሥልጣኑን ጭካኔ ተቃውሞአል፡፡ ከኃጢአታቸው ሳይመለሱ፣ ግፋቸውን ሳይተውና ንስሐ ሳይገቡ የሚፈጽሙት የሃይማኖት ሥርዓት በእግዚአብሔር ፊት አስጸያፊ እንደሆነ ገለጠ፡፡ አሞጽ ፭÷፳፩-፳፬፤ ፰÷፫-፲፡፡

## ማጠቃለያ

አሞጽ የእግዚአብሔርን ጽድቅ ያለፍርሃት የሰበከ፤ ሰዎችን ከክፉ መንገዳቸው የመለሰ ብርቱ ነቢይ ነው፡፡ ትንቢተ አሞጽም የነቢዩ የአሞጽን ሙሉ አገልግሎት የመዘገበ የፍርድ መጽሐፍ ነው፡፡

## ተግባር

- መምህሩ ወጣቶች ትንቢት አሞጽን በማጥናት የተማሩትን እንዲያካፍሉ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# ጸሎተ ሠለስቱ ደቂቅ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** የሦስቱን ወጣቶች ጸሎት አጠቃላይ ይዘት ማሳወቅ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** "ባሪያዎቹን ያዳነ አምላክ ይባረክ፤ እንደዚህ የሚያድን ሌላ አምላክ የለም" ዳን. ፫÷፳፱

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ዳን. ፫÷፰-፴ (የሦስቱ ልጆች መዝሙር ቁ ፩-፷፯)

## መግቢያ

ሦስቱ ወጣቶች አናንያ፣ አዛርያና ሚሳኤል ይባላሉ፡፡ በናቡከደነጾር ዘመን በእምነታቸው ኃይል እሳት አጥፍተዋል፡፡ ዕብ. ፲፩÷፫፬፡፡ ወደ ባቢሎን ከወረዱ በኋላ በምርኮ በባዕድ ሀገርና ሕዝብ መካከል ሆነውም እንኳን ማንነታቸውን ያላጡ፤ እግዚአብሔርንም በጽናት በማምለክ የዳኑ ወጣቶች ናቸው፡፡ ናቡከደነጾር በእሳት ላይ በጣላቸው ጊዜ በሚነደው እሳት መካከል ሆነው እግዚአብሔርን በመዝሙር አመሰገኑ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

ሦስቱ ወጣቶች በጉድጓድ እሳት ውስጥ ተጥለው በዚያ መካከል እየተመላለሱ ያዳናቸውን እግዚአብሔርን ፈጽመው አመሰገኑት፡፡ የሦስቱ ልጆች መዝሙር በእሳት ላንቃ ውስጥ ሳሉ የተቀኙት ቅኔ ነው፡፡ ሦስቱም በአንድ አፍ፣ በአንድ ልብ፣ በአንድ ቃል እግዚአብሔርን አመሰገኑ፡፡

## የሦስቱ ወጣቶች መዝሙር ይዘት፡-

- እግዚአብሔር ብቻ እውነተኛ አምላክ እንደሆነ ይገልጻል፡፡
- እግዚአብሔርን ፍጥረተ ዓለም ሁሉ በቋንቋቸው እንደሚያመሰግኑት ይመሰክራል፡፡
- እግዚአብሔር ከሰማዮች በላይ ባለ ሰማይ፣ በምድር በታችና በቀላይ ሁሉ ለስሙ ምስጋና እንዳለው ያመለክታል፡፡
- እግዚአብሔር የሾማቸው ካህናት በማሕሌት፣ ባሪያዎቹ በዜማ፣ ጻድቃኑ በሁለንተናቸው፣ መላእክት በልሳን፣ ሊቃውንት በቅኔ እንደሚያመሰግኑት ያመለክታል፡፡
- ሦስቱ ወጣቶች "ከሞትና ከሲኦል እጅ ከሚነድም እሳት አድኖናልና፤ ለእግዚአብሔር ተገዙ፤ ስሙንም አመስግኑ፤ ቸርነቱ ለዘላለም ነውና" በማለት የምስጋና ጥሪ አስተላልፈው መዝሙራቸውን ፈጸሙ፡፡

www.zeorthodox.org

➔ ጸሎተ ሠለስቱ ደቂቅ ከተጨማሪ (ዲዮትሮካኖኒካል) መጻሕፍት ውስጥ አንዱ ሲሆን የምስጋና መጽሐፍ ነው፡፡ የአመስጋኞቹ የምስጋና አርእስት ያለበት የፍጥረትን ሁሉ ምስጋና የያዘ መጽሐፍ ነው፡፡

## ማጠቃለያ

ጸሎተ ሠለስቱ ደቂቅ በእሳት ምድጃ ከተጣሉት ወጣቶች አንደበት የተገኘ የፍጥረት ሁሉ የምስጋና መዝገብ ነው፡፡ የጻድቃን ሰውነታቸው፣ የካህናት ዜማቸው፣ የመላእክት ልሳናቸውና የፍጥረታት እስትንፋሳቸው እግዚአብሔርን እንደሚያመሰግን የሚያሳይ የምስጋና መጽሐፍ ነው፡፡

## ተግባር

- መምህሩ "የሦስቱን ወጣቶች መዝሙር" ወጣቶች አጥንተው በጋራ እንዲጸልዩት ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# መጽሐፈ ሶስና

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** የመጽሐፈ ሶስናን አጠቃላይ ይዘት ወጣቶች እንዲገነዘቡ ማድረግ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** "እግዚአብሔርን ከምበድል በእጃቸው መውደቅ ይሻለኛል" ሶስና ቁ. ፳፪

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** (መጽሐፈ ሶስና ቁ. ፩-፳፫)

## መግቢያ

ሶስና የኬልቅዩስ ልጅ፤ የባቢሎናዊው የኢዮአቄም ሚስት ናት፡፡ እግዚአብሔርን የምትፈራ ትዳሯንም የምታከብር ሴት ነበረች፡፡ በአይሁድ መምህራን የሐሰት ክስ መከራ ቢደርስባትም እግዚአብሔር ስለንጽሕናዋ ምስክር አቁሞ አድኖአታል፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

መጽሐፈ ሶስና በስልሣ ሦስት ቁጥሮች የተከፋፈለ መጽሐፍ ሲሆን የሶስናን ታሪክ መዝግቦአል፡፡ የመጽሐፉ ዋና መልእክት እግዚአብሔርን ብለው ከኃጢአት የሚርቁ ሰዎች እግዚአብሔር በመከራቸውና በኑሯቸው ሁሉ እንደሚረዳቸው ማሳየት ነው፡፡

ሶስና በቤቷ የምታስተናግዳቸው የአይሁድ መምህራን በዝሙት ፈተኗት፡፡ እርሷ ግን የንጽሕና መንገድዋን መረጠች፡፡ መምህራኑ የልባቸው ስላልሆነላቸው በሐሰት ከሰሷት፡፡ በድንጋይ ተወግራ እንድትሞትም አስፈረዱባት፡፡ ከሳሾቿ የሕዝቡ መምህራን በመሆናቸው በአደባባይ የተሰበሰቡት ሰዎች ሁሉ አመኑአቸው፤ ሶስናን ግን እንደ አመንዝራ ቆጥረው ሊገድሏት ወሰኑ፡፡

ሶስና "ዘላለም ጸንተህ የምትኖር የተሰወረውን የምትገልጥ፣ የሚደረገውን ሁሉ ሳይደረግ አስቀድሞ የምታውቅ ፈጣሪ ሆይ በሐሰት እንደ ጣሉኝ አንተ ታውቃለህ፡፡" በማለት ጸለየች፡፡ እግዚአብሔርም ቃሏን ሰማ፡፡ ነቢዩ ዳንኤልን እንዲመሰክርላት አነሣሣው፡፡

ዳንኤል እየጮኸ "እኔ ከዚህች ሴት ደም ንጹሕ ነኝ" አለ፡፡ ሕዝቡም ወደ እርሱ ሲዞሩ በሐሰት እንደሆነ ለሕዝቡ መሠከረ፡፡ ከሳሾቹን በየተራ ቃል ሲቀበል ቃላቸው በመለያየቱ ምክንያት ሐሰተኞች መሆናቸውን አስረዳ፡፡ ሶስናንም ከሞት አዳናት፡፡ ሕዝቡም ሶስናን ያዳናትን እግዚአብሔርን አመሰገኑ ንጹሕ በሆነችው ሶስና ላይ ድንጋይ ባለመወርወራቸው ደስ አላቸው፡፡

እግዚአብሔር የሐሰተኞችን ክስ በማፍረስ እውነትን መግለጥ ልማዱ ነው፡፡ ሶስና በእምነቷ ጸንታ በመገኘቷ የንጽሕናዋ መንገድ ፍጻሜ አገኘች፡፡ ለእውነት ልዕልና እና ለእግዚአብሔር ክብር ታምነን ብንሠራ እግዚአብሔር የሐሰተኞችን ምክር አፍርሶ ታሪካችንን በድል ያጠናቅቀዋል፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

መጽሐፈ ሶስና እግዚአብሔር ከእውነተኞችና ከንጹሐን ጋር መሆኑን ይመሰክራል፡፡ እግዚአብሔር የጠላትን ምክር አፍርሶ ክብርን ደግሶ ድልን ያጎናጽፋል፡፡

## ተግባር

➔ መምህሩ ወጣቶች መጽሐፈ ሶስናን እንዲያነቡና ከታሪኩ የተማሩትን እንዲያካፍሉ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት እናነባለን?

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** የመጽሐፍ ቅዱስን አጠናን ጥበብ ወጣቶች እንዲያውቁ ማድረግ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** “የምታነበውን ታስተውለዋለህን?” ሐዋ. ፰÷፴

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ፪ጢሞ ፫÷፲፯

## መግቢያ

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር የሥልጣን ቃል፤ የቅዱሳት መጻሕፍት መገኛ መዝገብ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ የሕይወት መመሪያ መጽሐፍ ሲሆን ሕይወታችንን እንዴት መምራት እንዳለብን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ምስጢራት የምናውቅበት መጽሐፍ ነው፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል በወንዝ ዳር እንደተተከለች ለምለም ዛፍ ዘወትር ለመመገብ፤ ሕጉንም በቀንና በሌሊት ለማሰብ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ይጠበቅብናል፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

የእግዚአብሔርን የልቡን አሳብ፣ ለእኛ ያለውን የፍቅር ዓላማና ምክር ለማወቅ መጽሐፍ ቅዱስን አዘውትረን ማንበብ አለብን፡፡

## መጽሐፍ ቅዱስን ለማንበብ የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች፡-

- መጽሐፍ ቅዱስ ሊኖረን ይገባል፡፡
- ማስታወሻ ደብተር ማዘጋጀት፤
- የምናነብበትን ጊዜና መርሐ ግብር ማውጣት፤
- ለማንበቢያ የሚሆን ምቹ ሥፍራ ማዘጋጀት፤
- የመጽሐፍ ቅዱስን አጠናን ዘዴ የሚያስረዱ መጻሕፍትን መጠቀም
- አጋዥ የትርጓሜ መጻሕፍትንም መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

www.zeorthodox.org

# የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ጥበብ

**በመጻሕፍቱ ቅደም ተከተል መሠረት ማንበብ፡-** በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉት መጻሕፍት ቅደም ተከተል አላቸው፡፡ በዚህም መሠረት ከኦሪት ዘፍጥረት ጀምረን የመጻሕፍቱን ቅደም ተከተል በመጠበቅ በተከታታይ ማጥናት ይቻላል፡፡ ይህ የአጠናን ዘዴ የመጽሐፍ ቅዱሳን ሙሉ መልእክት ለመረዳት የሚያግዝ ሲሆን አራት ዓመታት ይፈጃል፡፡

**በይዘት ተመሥርቶ ማንበብ፡-** ርእስ ጉዳይ በመምረጥ ስለምንፈልገው ርእስ ብቻ በመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት እየተመራን በመታገዝ ማጥናት እንችላለን፡፡ ለምሳሌ፡- ‹‹ፍቅር›› በሚል ርእሰ ጉዳይ የተጻፉ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ለይቶ በማውጣት ማንበብና ስለ ፍቅር መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን ማወቅ እንችላለን፡፡

**በሰዎች ታሪክ በመመሥረት ማንበብ፡-** የአንድን ሰው ታሪክ በሁለቱም ኪዳናት ያለውን ጥቅል መልእክት ለማወቅ ያስችላል፡፡ ለምሳሌ፡- ስለ አብርሃም ታሪክ መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን በማጥናት ማወቅ ይቻላል፡፡

## መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት እናንብብ?

- ➔ እግዚአብሔር ምስጢር እንዲገልጥልን በጸሎት እንጀምር፡፡
- ➔ ዋና ዋና ነጥቦችን በማስታወሻ ደብተራችን እንመዝግብ፡፡
- ➔ ያልገባንን ለይተን በመጻፍ የቤተክርስቲያን ሊቃውንትን ወይም መምህራንን እንጠይቅ፡፡
- ➔ ካነበብነው ክፍል ምን እንደተማርን ራሳችንን እንጠይቅ፡፡
- ➔ በተረዳነው የእግዚአብሔር ቃል በደረስንበት እውነተኛ ትምህርት ለመመላለስ እንትጋ፤ ፊልጵ. ፫÷፲፮፡፡
- ➔ በቃሉ የመከረንን እግዚአብሔርን በማመስገን የዕለቱን የጥናት ጊዜ እንዝጋ፡፡
- ➔ በቀጣይ የጥናት ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስን ለማንበብ እንናፍቅ፤ በሰበብ ንባባችንን ላለማቋረጥ እንወስን፡፡

## ማጠቃለያ

መጽሐፍ ቅዱስን ዘወትር የሚያነቡ አማኞች የማይቋረጥ አምላካዊ በረከት አላቸው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ የሕይወታችን መመሪያ በመሆኑ በየዕለቱ መለኮታዊውን ትእዛዝ ለመቀበል እና በቃሉ ጸንተን ለመገኘት በትጋት ማንበብ አለብን፡፡

## ተግባር

www.zeorthodox.org

- መምህሩ ወጣቶች ዘመናቸውን ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስን እንዲያነቡ ይምከራቸው፡፡

# ቁስቋም

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች የቁስቋምን በዓል ታሪክ እንዲያውቁ ማድረግ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** "የሕፃኑን ነፍስ የፈለጉት ሞተዋልና ተነሣ ሕፃኑንና እናቱን ይዘህ ወደ እስራኤል ሂድ፡፡" ማቴ. ፪÷፳

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ማቴ. ፪÷፲፫-፳፫

## መግቢያ

- ቁስቋም ማለት ምን ማለት ነው?
- በቤተ ክርስቲያናችን የቁስቋም በዓል መቼ ይከበራል?
- የቁስቋምን በዓል ለምን እናከብራለን?
- ከበዓለ ቁስቋም በፊት ያለው የፈቃድ ጾም ማን ይባላል?

## የሳምንቱ ትምህርት

በቤተልሔም ይሁዳ እመቤታችን የበኩር ልጇን በድንግልና ወለደች፡፡ የወለደችው ትንቢት የተነገረለት ሱባኤ የተቆጠረለትን አምላክ ነው፡፡ የጥበብ ሰዎች አምሀ ይዘው፤ "የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው?" በማለት ሲጠይቁ የቤተልሔም አውራጃ ንጉሥ የነበረው ሄሮድስ የሕፃኑን ነፍስ ሊገድል ፈለገ፡፡ በዚህ ጊዜ የእግዚአብሔር መልአክ ለአረጋዊ ዮሴፍ በሕልም ተገለጠለት፡፡ "የሕፃኑን ነፍስ ሄሮድስ ይፈልጋልና ተነሣ ሕፃኑንና እናቱን ይዘህ ወደ ግብጽ ሂድ፤ እስከነግርህም ድረስ በዚያ ተቀመጥ" አለው፡፡ ዮሴፍም ሕፃኑን ኢየሱስንና እናቱን ማርያምን ይዞ ወደ ግብጽ ሸሸ፡፡ "ልጄን ከግብጽ ጠራሁት" የተባለው ትንቢትም ተፈጸመ፡፡ ሆሴ. ፲፩÷፩፡፡

ሄሮድስ ከሞተ በኋላ የእግዚአብሔር መልአክ እንደገና ለአረጋዊ ዮሴፍ በሕልም ተገለጠ፡፡ "የሕፃኑን ነፍስ የፈለጉት ሞተዋልና ተነሣ ሕፃኑንና እናቱን ይዘህ ወደ እስራኤል ሂድ" አለው፡፡ ዮሴፍም መልአኩ እንዳዘዘው አደረገ፡፡

የቁስቋም በዓል በየዓመቱ ኅዳር ስድስት ቀን ይከበራል፡፡ የበዓሉ መከበር ምክንያት እመቤታችን ከሦስት ዓመት ከመንፈቅ የግብጽ ስደት በኋላ ወደ ገሊላ መመለሷን ለመዘከር ነው፡፡ በዘመነ ጽጌ የክርስቶስን ስደት እና የእናቱን የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ሐዘን እያሰብን ከሰነበትን በኋላ ኅዳር ስድስት ቀን ወደ እስራኤል መመለሷን በማሰብ በዓል እናደረጋለን፡፡

www.zeorthodox.org

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከግብጽ ስደት መልስ በነቢያት "ናዝራዊ" ይባላል፤ የተባለው ይፈጸም ዘንድ በናዝሬት ከተማ ኖረ፡፡ ለእናቱ እየታዘዘ፤ ከመምህራን መካከል ተቀምጦ እየተማረ፣ እየጠየቀና እየመለሰ በጥበብና በሞገስ በሰውና በእግዚአብሔር ፊት አደገ፡፡ ሉቃ. ፪÷፶፪፡፡

## ማጠቃለያ

የቁስቋም በዓል በየዓመቱ ኅዳር ስድስት ቀን ይከበራል፡፡ በበዓሉ የእመቤታችን ከስደት መመለስ ይዘከራል፡፡

## ተግባር

♦ መምህሩ ‹‹የቁስቋም በዓል እንዴት ይከበራል?›› በሚል ርእስ ወጣቶቹን ያወያያቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# አስተርእዮ ማርያም

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** የእመቤታችንን በዓለ ዕረፍት ልጆች እንዲያከብሩ ማስገንዘብ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** "በጌታ የሚሞቱ ብፁዓን ናቸው፡፡" ራእ. ፲፬÷፲፫

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ሉቃስ. ፩÷፵፮-፶፭ እና ዮሐ. ፲፩÷፳፮

## መግቢያ

እመቤታችን ማርያም የአምላክ እናት ናት፡፡ ድንግል ማርያም ትውልድ ሁሉ ብጽዕት የሚላት እመቤት ናት፡፡ እመቤታችን ማርያም ክብርት፣ ልዕልት፣ ንጽሕት፣ ቅድስት፣ ውድስትና ስብሕት ናት፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

እመቤታችን ማርያም በዚህ ዓለም ስልሣ አራት ዓመታት በቅድስና ኖራለች፡፡ በጎልጎታ ቃልኪዳን ከተቀበለች በኋላ ጥር ፳፩ ቀን በክብር አርፋለች፡፡ በየዓመቱ ጥር ፳፩ ቀን "አስተርእዮ ማርያም" በመባል ይከበራል፤ የድንግል ማርያም ዕረፍቷ ይዘከራል፡፡

አስተርእዮ ማለት መታየት፤ መገለጥ ማለት ነው፡፡ ጥር የአምላክ በሥጋ ማርያም መገለጥ የሚሰበክበት ወርኀ በመሆኑ ዘመነ አስተርእዮ ይባላል፡፡ እመቤታችን ማርያምም ከዕረፍቷ በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ ስለታየች በዓሉ አስተርእዮ ተብሏል፡፡

እመቤታችን ማርያም ባረፈች ጊዜ ደቀመዛሙርቱ አዘኑ፡፡ በጎልጎታ ሥጋዋን በክብር ሊቀብሩ ሲጓዙ፤ አይሁድ "ደግሞ እንደልጇ ተነሣች" እያሉ ያስቸግሩናል በሚል ስጋት ሥጋዋን ሊቃጥሉ መጡ፡፡ ታውፋንያ የሚባል አንድ ሰው ሥጋዋ የተኛበትን የአልጋ ሸንኮር /ጠርዝ/ ሲይዝ መልአኩ በሰይፍ ቀጣው፡፡ ጌታ የማልኮስን ጆሮ እንደፈወሰው በድንግል ምልጃ ቅዱስ ጴጥሮስ እንደነበረ አደረገለት (ፈወሰው)፡፡

መልአኩ የእመቤታችንን ሥጋ ወስዶ በገነት ከዕፀ ሕይወት ሥር አስቀመጠው፤ ይህንም ዮሐንስ ወንጌላዊው ተመልክቶአል፡፡ ሌሎቹም ደቀመዛሙርት ከነሐሴ ፩-፲፬ በመጾም ድንግልን ዳግም ለማየት ታድለዋል፡፡

www.zeorthodox.org

"አሚሚትሽ በጥር ነሐሴ መቃብር" እንዳሉት ሊቃውንቱ እመቤታችን ማርያም በጥር ብታርፍም መቃብሯ የተፈጸመው በነሐሴ ነው፡፡ ክብሯ የሆነ ልጇን "ጌታዬ መድኃቴ" ብላ ስላመነች፤ በልጇ ድል የተነሣ ሞት በእርሷ ላይ ኃይል ሊኖረው ስለማይችል እንደልጇ ተነሥታለች፡፡

## ማጠቃለያ

በየዓመቱ ጥር ፳፩ ቀን የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያምን በዓለ ዕረፍት እንዘክራለን፡፡ ይህ በዓል "አስተርእዮ ማርያም" እየተባለ ይጠራል፡፡

## ተግባር

- መምህሩ ለወጣቶቹ ስለበዓሉ አከባበር ይትበሃል (ሥርዓት) ይንገራቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# መምህር ኤስድሮስ

**የትምህርቱ ዓላማ:-** የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ባለውለታዎችን ወጣቶች እንዲያውቁ ማድረግ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ:-** "አባትህን ጠይቅ ያስታውቅህማል፡፡" ዘዳግም. ፴፪÷፯

**ተጨማሪ ምንባብ:-** (አማርኛ የቤተክርስቲያን መዝገበ ቃላት ዶ/ር ሥርግው ሐብለ ሥላሴ፣ ገጽ. 64-68፣ ፲፱የ፹፩/1981/ ዓ.ም)

## መግቢያ

መምህር ኤስድሮስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የትርጓሜ ስልትና ምርምርን ያሳዩ ታላቅ የቤተክርስቲያን ሊቅ ሲሆኑ የአራቱ ጉባኤያት መምህር ነበሩ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

መምህር ኤስድሮስ በትግራይ በተምቤን አውራጃ በ0ሥራ ስምንተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ተወለዱ፡፡ በሠላሳ ቀናቸው የዓይናቸውን ብርሃን ቢያጡም ልበ ብሩህ ሆነው የአራቱ ጉባኤያት መምህር ከመሆን አላስቀራቸውም፡፡

የትምህርት ጊዜያቸውን እንዳጠናቀቁ ወንበር ዘርግተው ማስተማር ጀመሩ፡፡ የቤተክርስቲያን ትምህርቶችን እና የመጽሐፍ ቅዱስን የትርጓሜ ስልት አሳይተዋል፡፡

መጻሕፍተ ሐዲሳትን ተርጉመዋል፡፡
አዲሱን የትርጓሜ ስልት የሚከተሉ ደቀመዛሙርት አፍርተዋል፡፡
በግራኝ ወረራ የተቃጠሉ መጻሕፍትን እንደገና ጽፈዋል፡፡

መምህር ኤስድሮስ ከኢትዮጵያውያን ታላላቅ ሊቃውንት መካከል ግንባር ቀደም ተጠቃሽ ናቸው፡፡ እጅግ በርካታ ደቀመዛሙርትን አስተምረው ታላላቅ የቤተክርስቲያን ሊቃውንት ያፈሩም ሊቅ ናቸው፡፡

## ማጠቃለያ

መምህር ኤስድሮስ በትግራይ ተንቤን ተወልደው በጎንደር የኖሩ ታላቅ ሊቅ ነበሩ፡፡ በግራኝ አህመድ የተቃጠሉ የትርጓሜ መጻሕፍትን እንደገና ጽፈዋል፡፡ ብዙ ታላላቅ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት መምህራንን አፍርተዋል፡፡

www.zeorthodox.org

## ተግባር

መምህሩ፤ ወጣቶች ስለሌሎች ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት በማንበብና በመጠየቅ እንዲረዱ ያድርግ፡፡

# ዘመነ ሐዋርያነ አበው ፩

**የትምህርቱ ዓላማ፦** ወጣቶች የክርስትናን ጉዞ እንዲያውቁ ማድረግ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፦** "ከእኔም የሰማኸውን ሊያስተምሩ ለሚችሉ ለታመኑ ሰዎች አደራ ስጥ" ፪ጢሞ. ፪÷፪

**ተጨማሪ ምንባብ፦** (የቤተክርስቲያን ታሪክ፤ በሉሌ መላኩ ገጽ 28-33)

## መግቢያ

ክርስትና በብዙ መከራ የሮምን ድንበር ተሻገረ፡፡ ለክርስትና እምነት ዋጋ የሚከፍሉ ብዙ አማኞች መቅደሱን ሞሉ፡፡ ከሐዋርያት የተማሩትን የሚያስተምሩ በርካታ አስተዋይ መምህራን አደባባዮቹን ሞሉ፡፡ እነዚህ መምህራን ሐዋርያነ አበው (የሐዋርያት ተከታዮች) ይባላሉ፡፡ የአገልግሎት ዘመናቸው ከ፻-፻፷/100-160/ ዓ.ም ነው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

ቅዱሳን ሐዋርያት የምሥራቹን ድምፅ እያሰሙ፤ የማዳኑንም አዋጅ እያወጁ በብዙ መከራ ወንጌልን እያስፋፉ ከሮም ድንበር አሻገሩ፡፡ ክርስትና በግብጽ፣ በአንጾኪያ፣ በአርመን፣ በሕንድ፣ በኢትዮጵያ፣ በኢጣሊያ፣ በኤፌሶን፣ በቂሳርያ፣ በቆላስየስና በሌሎች ታላላቅ የዓለም ሃገሮች ተሰበከ፡፡ ደቀመዛሙርቱ ስብከታቸውን በጽሑፍም ጭምር በመላክ ትውልዱ ከጨለማ ጥላ እንዲወጣ አደረጉ፡፡ ቅዱሳን ሐዋርያት በአርድእትና በመጀመያዎቹ ክርስቲያኖች እየታገዙ ካገለገሉ በኋላ እነርሱ ደግሞ ሊያስተምሩ ለሚችሉ ተተኪዎቻቸው ለታመኑ ሰዎች የወንጌልን አደራ ሰጡ፡፡

የወንጌልን አደራ የተቀበሉት ሰዎች አብዛኞቹ ከሐዋርያት የተማሩ ናቸው፡፡ ጢሞቴዎስ፣ በርናባስ፣ አጵሎስ፣ ቲኪቆስ፣ ኤጳፍራ፣ ሉቃስ፣ ማርቆስ፣ አርሰጥሮኮስ፣ ንምፉን፣ አንዲራኒቆን፣ ዩልያን፣ ጵልያጦን፣ ኢሩባኖንና ኤጤሌን በደቀ መዛሙርቱ ዙሪያ የነበሩ፤ከእነርሱ የተማሩ፣ የወንጌልንም አደራ የተቀበሉ የታመኑ ሰዎች ናቸው፡፡

በክርስትና የጎላ ታሪክ ያላቸው ከሐዋርያት ቀጥለው የተነሡ አባቶች ሐዋርያነ አበው ይባላሉ፡፡ የእነዚህ አባቶች የአገልግሎት ዘመን ከ፻-፻፷/100-160/ ዓ.ም ነው፡፡ ከእነዚህ አባቶች መካከል ቀሌምንጦስ ዘሮም፣ አግናጥዮስ ምጥው ለአንበሳ፣ ፖሊካርፕ ዘስምርና፣ ኖላዊው ሔርማስ፣ ሰማዕቱ ጀስቲን፣ ጡርቱሊያንና ኢራንዮስ ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህ ታላላቅ አባቶች የክርስትናን እውነት ከክፉዎች ትምህርት የጠበቁ ዕቅበተ እምነት (አፖሎጅስት) ይባላሉ፡፡ እንደ ሐዋርያት መልእክታትን የጻፉና ወንጌልን የሰበኩ ናቸው፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

ከሐዋርያት ቀጥለው የቤተ ክርስቲያን ጠበቆች የነበሩ አባቶች ሐዋርያነ አበው ይባላሉ፡፡ የአልግሎት ዘመናቸውም ከ፻-፻፷/100-160/ ዓ.ም ነው፡፡

## ተግባር

- መምህሩ፤ ወጣቶችን ከዛሬው ትምህርት ምን እንደተማሩ ይጠይቃቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ዘመነ ሐዋርያነ አበው ፪

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች የቤተ ክርስቲያንን ባለውለታዎች እንዲያውቁ ማድረግ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** "እስከሞት ድረስ የታመንህ ሁን የሕይወትንም አክሊል እሰጥሃለሁ፡፡" ራእ. 2÷01

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** (የቤተክርስቲያን ታሪክ፤ በሉሌ መላኩ ገጽ 28-33)

## መግቢያ

ከ፻-፻፷/100-160/ ዓ.ም ዘመነ ሐዋርያነ አበው ይባላል፡፡ ከሐዋርያት ቀጥለው የተነሡ አባቶች ወንጌልን እያስፋፉ ወንጌልን እያስፋፉ የክርስትናን ትምህርት ለማስቀጠል ሕይወታቸውን የሠዉበት ዘመን ነው፡፡ እነዚህ አባቶች የቤተ ክርስቲያን ጠበቆች (አፖሎጅስት) ይባላሉ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

### አግናጥዮስ ምጥው ለአንበሳ፤ ፴-፻፲ (30-110)ዓ.ም

ቅዱስ አግናጥዮስ የቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ ደቀ መዝሙር ነው፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ መንግሥተ ሰማያት ሲያስተምር፤ በደቀ መዛሙርቱ መካከል ያቆመውና ያቀፈው ሕፃን አግናጥዮስ እንደነበር የክርስትና ትምህርት ይጠቁማል፡፡ ማቴ. 08÷1-4፡፡ አግናጥዮስ ከቅዱስ ጴጥሮስና ከኤውዲዮስ ቀጥሎ የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ ሆኖ አገልግሏል፡፡

አግናጥዮስ ጌታ ያቀፈው ሕፃን ስለነበረ "ቴዎፍሮስ"፤ ሰማዕትነት የተቀበለው በአናብስት ተበልቶ ስለሆነ "ምጥው ለአንበሳ" ይባላል፡፡ አግናጥዮስ ወንጌልን በቃልና በጽሑፍ የሰበከ ታላቅ አባት ነው፡፡

### ፖሊካርፕ ዘስምርና ፸- ፻፶፮(70-156) ዓ.ም

ቅዱስ ፖሊካርፕ የኢሬንቶስ አስተማሪ ነበር፡፡ የስምርና ኤጲስ ቆጶስ በመሆን አገልግሏል፡፡ በመጨሻረም በፒዩስ ቄሳር ዘመነ መንግሥት በ፻፶፭/155/ ዓ.ም ወንጌልን በመስበኩ ክርስትናንና በማስተማሩ ተከስሶ ለፍርድ ቀረበ፡፡ "በቄሳር ማል" ተባለ፡፡ "እኔ ክርስቲያን ነኝ፤ መሐላ መፈጸም አልችልም" አላቸው፡፡ "ኢየሱስ ክርስቶስን ካድ" አሉት፡፡ "ሰማንያ ስድስት ዓመታት ሙሉ ሳገለግለው የኖርኩትን፤ ያልበደለኝንና የሚወደኝን ጌታዬን አልክድም" አላቸው፡፡ "ለጣዖት ስገድ" አሉት፤ "አልሰግድም፤ አምልኮ የሚገባው ለአምላኬ ብቻ ነው" አላቸው፡፡ በእዝሚር የጨዋታ ሜዳ በተሰበሰበው ሕዝብ ፊት በእሳት ተቃጥሎ በሰማዕትነት ዐረፈ፡፡

www.zeorthodox.org

### ቀሌምንጦስ ዘሮም ፺፩-፻፷(91-160)ዓ.ም

ቀሌምንጦስ ሮም ተወልዶ መንፈሳዊ ትምህርቱን ካጠናቀቀ በኋላ መዓርገ ክህነት ተቀብሎ የሐዋርያው የቅዱስ ጴጥሮስ ደቀ መዝሙር በመሆን የክርስትናን ትምህርት ያስተምር ነበር፡፡

የሮም አራተኛ ሊቀ ጳጳስ በመሆን አገልግሏል፡፡ ክርስትናን በጽሑፍና በቃል በማስተማር የኖረ አባት ነው፡፡ በትራጃን ዘመነ መንግሥት አንገቱ በመልሕቅ ታስሮ ጥቁር ባሕር ውስጥ ተጥሎ በሰማዕትነት ዐርፏል፡፡

## ኖላዊው ሔርማስ ፻-፻፷(100-160) ዓ.ም

ክርስትናን በጽሑፍ ካስተማሩና መንጋውን ተግተው ከጠበቁ አባቶች መካከል ተጠቃሽ ነው፡፡

## ሰማዕቱ ጀስቲን ፻-፻፷(100-160) ዓ.ም

የክርስትናን ትምህርት ከፈላስፎች ክህደት የጠበቀ አፖሎጅስት ነው፡፡

## ኢራሬንዮስ ፻፳፫-፪፻፫(123-203) ዓ.ም

ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝ አምላክ የመሆኑን ዜና በትጋት ካወጁ ሐዋርያነ አበው መካከል አንዱ ሲሆን፤ ትምህርቱን በጽሑፍ አስፍሮ ብዙ አማኞችን ጠቅሞአል፡፡

## ጠርቱሊያን ፻፷-፪፻፳(160-220)ዓ.ም

ይህ አባት በብዙ ክርስትና ትምህርቶቹ ይታወቃል፡፡ የእግዚአብሔርን ሦስት ፍጹማን አካላት "ሥላሴ" በማለት የጠራ ታላቅ መምህር ነው፡፡ በምስጢረ ሥላሴ የበረታ ጸሐፊ ነበር፡፡

## ማጠቃለያ

ሐዋርያነ አበው የክርስትናን ትምህርት በቃልና በጽሑፍ ለምእመናን ያበረከቱ፣ በመከራ ውስጥ በጽናት ያልፉ፣ ክርስቲያኖችን በእምነታቸው ጠንክረው ጸንተው እንዲቆሙ አማኞችን ያጽናኑና ከመናፍቃን ሴራ ሃይማኖትን የጠበቁ እውነተኛ የቤተ ክርስቲያን ጠበቆች (አፖሎጂስቶች) ናቸው፡፡

## ተግባር

www.zeorthodox.org

- መምህሩ፤ ከዛሬዎቹ ባለታሪኮች ወጣቶች ምን እንደተማሩ ይጠይቃቸው፡፡

# ዘመነ ሐዋርያነ አበው ፫

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** የቤተክርስቲያን ጠበቆች ለክርስትና ያደረጉትን አስተዋጽኦ ወጣቶች እንዲያውቋቸው ማድረግ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** "በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ፡፡" ማቴ. ፲÷፴፪

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** (የቤተክርስቲያን ታሪክ፤ በሉሌ መላኩ ገጽ 28-32)

## መግቢያ

ሐዋርያነ አበው በትክክለኛ ትምህርታቸው እውነተኛውን የክርስትናን እምነት ከመናፍቃን የስሕተት ዘር ጠብቀዋል፡፡ ምእመናንን አጽናንተዋል፡፡ በክርስትና እምነታቸው ጸንተው እንዲቆሙ አድርገዋል፡፡ ከ፶፬/54/ ዓ.ም ጀምሮ የመከራ ቋጥኝ ለወደቀበት ክርስትና ቆራጦች ያስፈልጉ ነበር፡፡ የሐዋርያነ አበው መኖር ክርስትና ከነሙሉ ክብሩ ለትውልድ እንዲደርስ አድርጓል፡፡ ክርስትና ለትውልድ የተሻገረው በመከራው ዘመን ብርቱ በነበሩት ሰማዕታት ደም ጸንቶ ነው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

## ሐዋርያነ አበው ለቤተክርስትያን ያደረጉት አስትዋጽኦ፡-

- የሐዋርያትን ትምህርት ለትውልድ አስተላልፈዋል፡፡
- መከራ እንዳያደከማቸው ክርስቲያኖችን አጽናንተዋል፡፡
- የእግዚአብሔርን መልእክት በዘመናቸው ለትውልድ በጽሑፍ ገልጠዋል፡፡
- የክርስትናን ትምህርት ከመናፍቃን ክህደት (ከጠላት ዘር) ጠብቀዋል፡፡
- የክርስትናን መሠረታዊ ትምህርቶች በመጻሕፍት አዘጋጅተዋል፡፡
- በኑሯቸው ሁሉ ለአማኞች ምሳሌ ሁነዋል፡፡
- በክርስትና እምነት ጸንተው ሕይወታቸውን በመሠዋት የልባቸውን እውነት ለትውልድ አሻግረዋል፡፡
- ወንጌል ከአድማስ እስከ አድማስ እንዲሰበክ ዋጋ ከፍለዋል፡፡

www.zeorthodox.org

## በዘመነ ሐዋርያነ አበው ከ፻-፻፷(100-160 ዓ.ም) የተከናወኑ ታላላቅ ሥራዎች፡-

- የክርስትና ትምህርት በአራቱም ማዕዘናት ተሰብኳል፡፡

- በአባቶች ትምህርት ብዙ ኢ-አማንያን ከጨለማ ግዛት ወጥተው ወደ ብርሃኑ ዘለዓለማዊ መንግሥት መጥተዋል፡፡
- ለክርስትና ሕይወት አጋዥ የሚሆኑ ብዙ መጻሕፍት ተጽፈዋል፡፡
- ብዙ ሰማዕታት የእምነታቸውን ፍሬ በሥራ አሳይተዋል፡፡
- አብያተ ጣዖታት ባዶ እስኪሆኑ፣ ካህናተ ጣዖታት እስኪራቡ አላውያን ነገሥታት በቁጣ እስኪነሡ ድረስ በኃይል የመንግሥቱ ወንጌል ተሰብኳል፡፡

## የሐዋርያን አበው ሥራዎች፡-

**የቀሌምንጦስ ሊቀ ጳጳስ ዘሮም ሥራዎች**፡- ከሥርዓት መጻሕፍት አንዱ የሆነውን መጽሐፈ ቀሌምንጦስ ጽፏል፡፡ በቅዳሴ ሰዓት ለምእመናን የሚነበቡ ሁለቱን ኪዳናት ማዕከል ያደረጉ ሁለት መልእክታት ጽፏል፡፡

**የመጀመሪያው መልእክት ይዘት**፡- ስለ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ አገልግሎት፣ ስለብዙ ሰማዕታት መሥዋዕትና ስለ መዓርገ ክህነት የሚናገር ነው፡፡

**የሁለተኛው መልእክት ይዘት**፡- ስለ ንስሐ፣ ስለቅድስና ኑሮ እና ስለ ሙታን ትንሣኤ ይናገራል፡፡

**የአግናጥዮስ ሥራዎች**፡- ቅዱስ አግናጥዮስ ለኤፌሶን፣ ለማግኔሲያ፣ ለትራሌስና ለሮም አብያተ ክርስቲያናት የተላኩ አራት መልእክታትን ጽፏል፡፡

**የፖሊካርፕ ሥራዎች**፡- ለፊልጵስዮስ ክርስቲያኖች የተላከ መልእክት ጽፏል፡፡ ግኖስቲኩን ቬሌንቲኑስን የሚቃወም ትምህርተ ክርስትናም ጽፏል፡፡

## ማጠቃለያ

ሐዋርያነ አበው በዘመናቸው የእግዚአብሔርን ሐሳብ አገልግለው ዐርፈዋል፡፡ በዘመነ ሐዋርያነ አበው ትልልቅ ሥራዎች ተሠርተዋል፤ ያ ጊዜ የቤተ ክርስቲያን ፍሬያማ ጊዜ ነበር፡፡

## ተግባር

- መምህሩ ወጣቶችን ከዛሬው ትምህርት ምን እንደተማሩ ይጠይቃቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ሃይማኖት ቅድመ ክርስትና በኢትዮጵያ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ከክርስትና በፊት የነበረውን የኢትዮጵያን ሃይማኖት ወጣቶች እንዲያውቁ ማድረግ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** “አንተን የወደደ በእስራኤልም ዙፋን ያስቀመጠህ አምላክህ እግዚአብሔር የተባረከ ይሁን፡፡” ፩ነገ. ፲÷፱

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ፩ነገ.፲÷፩-፩፫፣ ሐዋ. ፰÷፳፮-፴፱ (የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ፤ በአባ ጎርጎርዮስ ገጽ. 13-17)

## መግቢያ

ኢትዮጵያ በመጽሐፍ ቅዱስ ከአርባ ጊዜ በላይ ስሟ የተጠቀሰ ሃገረ እግዚአብሔር ናት፡፡ ኢትዮጵያ ቅድመ ክርስትና በሕገ ኦሪት በአንድ አምላክ ጸንታ ትኖር ነበር፡፡ በብሉይ ኪዳን መሥዋዕተ ኦሪት የተሠዋባት፤ በሐዲስ ኪዳንም ከሁሉ በፊት የክርስትና ወንጌል የተሰበከባት ታላቅ የሃይማኖት ሃገር ናት፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

ኢትዮጵያ የኖህ ልጅ አቢስ ስለተቀመጠባት፣ እስራኤላውያን ካህናተ ኦሪት በተለያዩ አጋጣሚዎች ስለገቡባትና መጻሕፍተ ብሉያትን ስላገኘች ሕገ ኦሪትን ተቀብላ ነበር፡፡

ንግሥተ ሳባ የሰሎሞንን ጥበብ ለመጎብኘት ወደ ኢየሩሳሌም በሄደች ጊዜ ምኒልክ ቀዳማዊውን ፀንሳ መጣች፡፡ ምኒልክ ባደገ ጊዜ አባቱን ለማየት ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ፡፡ ወደ አገሩ ሲመለስ ፫፻፲፰/318/ ሌዋውያን ካህናትን፣ ታቦተ ጽዮንንና መጻሕፍተ ብሉያትን ይዞ መጣ፡፡ በዚህ ምክንያት በአንድ አምላክ ማመን፣ በሕገ ኦሪት መኖርና መሥዋዕተ ኦሪት መሠዋት በኢትዮጵያ ተስፋፋ፡፡ በ፱፻፹/980/ ዓ.ዓ መጻሕፍተ ብሉያት በሳባ ቋንቋ (በግእዝ) ተተረጎሙ፡፡ አምልኮተ እግዚአብሔር ሰፋ፡፡ የጃንደረባው ባኮስ ትንቢተ ኢሳይያስን እያነበበ መገኘት ለዚህም በቂ ማስረጃ ነው፡፡ ሐዋ. ፰÷፴፪፡፡

ሥርዓተ ግዝረት፤ አመጋገብ፣ አለባበስ፣ የበዓላት አከባበርና ልማደ ኦሪቶች በኢትዮጵያ ዛሬም ድረስ በዝቶ መታየቱ ኢትዮጵያ ቅድመ ክርስትና በሕገ ኦሪት ለመኖሯ ሕያው ምስክር ነው፡፡

www.zeorthodox.org

ኢትዮጵያ በሁለቱም ኪዳናት እግዚአብሔርን ያመለከች፣ እጆቿን ወደፊቱ የዘረጋች፣ ቃሉን የሰማችና መሥዋዕት የሠዋችለት ሃገር ናት፡፡ ኢትዮጵያ ነገሥታቷ እንኳን ለሃይማኖት የሠሩ ናቸው፡፡

ኢትዮጵያ ነጻነቷን ጠብቃ የኖረች ከአምልኮተ እግዚአብሔር ያልወጣች፣ በሁለቱም ኪዳናት የተጠቀመችና ለትውልዱ ርትዕት ሃይማኖትን ያወረሰች የሃይማኖት ልጆች ዓምባ ናት፡፡ ታላላቅ ቅዱሳንና ሊቃውንትም የበቀሉባት የቃል ኪዳን ሃገር ናት፡፡

## ማጠቃለያ

ኢትዮጵያ በሕገ ኦሪትም በሕገ ወንጌልም እግዚአብሔርን አምልካለች፡፡ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር እንደምትዘረጋም በመጽሐፍ ቅዱስ ተመስክሮላታል፡፡ የተስፋው ትንቢት የተነገረበትና የፍጻሜው ወንጌል የተሰበከባት የሃይማኖት ዓምባ ናት፡፡

## ተግባር

- መምህሩ "ኢትዮጵያ ቅድመ ክርስትና ሕገ ኦሪትን እንዴት ልትቀበል ቻለች?" በሚል ርዕስ ወጣቶቹን ያወያያቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ኅልዎተ እግዚአብሔር

**የትምህርቱ ዓላማ:-** ለወጣቶች የእግዚአብሔርን መኖር ማስገንዘብ።

**የሚጠና ጥቅስ:-** "ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ እግዚአብሔር እንዳለ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋል።" ዕብ. ፲፩÷፮

**ተጨማሪ ምንባብ:-** መዝ. ፲፫÷፩

## መግቢያ

እግዚአብሔር የነበረ፣ያለ፣ የሚኖርና የሚያኖር አምላክ ነው። ህልዎት ማለት መኖር፣መገኘት፣መሆን ማለት ነው። የእግዚአብሔር መኖር በሥራው፣ በፍጥረቱና በቅዱሳት መጻሕፍት ተገልጧል።

## የሳምንቱ ትምህርት

"እግዚአብሔር የለም" የሚል ሰነፍ ነው። መዝ. ፲፫÷፩። ሰነፍ "እግዚአብሔር የለም" የሚለው ኃጢአትን እንደፈለገ ለመሥራት ነው። "እግዚአብሔር አለ" ብሎ ቢያምን ኃጢአቱ እንደሚያስቀጣው ያውቃልና።

እግዚአብሔር አለ። ዙፋኑ አይናወጽም፤ መንግሥቱ አይሻርም፤ ዘመኑም አያልቅም። እግዚአብሔር ማንም በማይቀርበው ብርሃን ማንም በማይደፍረው ዓለም ይኖራል፤ አይጠረጠርም። መምሽት መንጋቱ፤ የፍጥረት እንቅስቃሴ በሕይወት ሥርዓት መመራቱ ከእርሱ መኖር የተነሣ ነው። የእግዚአብሔር መኖር ለፍጥረት መኖር መሠረት ነውና።

እግዚአብሔር መኖሩን እንድናውቅ ራሱን በመግለጥ አስረድቶናል። የእግዚአብሔርን መኖር በምን እናውቃለን?

### 1.በፍጥረቱ:-

እግዚአብሔር ለፍጥረቱ በፍጥረቱ ይታወቃል። የፍጥረቱ ደኅንነት እና የተፈጥሮ እንቅስቃሴ ሁሉ የመኖሩ ማሳያ ነው። ሮሜ. ፩÷፳። የምናየውን የተፈጥሮ ፊት ያስዋበው የማይታየው አምላክ እጅ ነው። ነፋስን ስላላየነው የለም ማለት አንችልም። በእንቅስቃሴው ይታወቃልና። አምላካችንንም ስላላየነው የለም ማለት እንችልም በመግቦቱና በጥበቃው ይታያልና።

www.zeorthodox.org

### 2. በሰው ኅሊና ምስክርነት:-

የሰው ኅሊና እግዚአብሔር እንዳለ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንደሚሰጥ ይመሰክራል። አንድ ንጉሥ ስብሰባ ሲጀምር

"እግዚአብሔር የለም" በማለት የመክፈቻ ንግግር ያደርጋል፤ የነገሩ መደጋገም ያመማቸው አንድ ሊቅ "ሁልጊዜ ለምን እንዲህ ትለናለህ?" አሉት፡፡ ንጉሡም "ኅሊናዬ ሁልጊዜ እግዚአብሔር አለ ስለሚለኝ የኅሊናዬን ጩኸት ዝም ለማድረግ ነው" አለ፡፡ የሰው ኅሊና ሰሚ ካገኘ የአምላክን መኖር ይናገራል፡፡

## 3. በመጽሐፍ ቅዱስ አስረጅነት

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን መኖር ይመሠክራል፡፡ የእግዚአብሔርን መኖር ያመኑት መባረካቸውንና የተገዳደሩት መቀጣታቸውን ይናገራል፡፡

## 4. በክርስቶስ መገለጥ

ክርስቶስ በሥጋ ሲገለጥ፤ አምላካችን በሰው መካከል የጽድቅን ሥርዓት እያስተማረ ሲመላለስ፤ ከመለኮታዊ ዙፋኑ ወርዶ ሲፈልገን መኖሩ እውነት እንደሆነ አረጋግጧል፡፡

## ማጠቃለያ

እግዚአብሔር አለ፤ ነበረ፤ ከዘላለም እስከ ዘላለም ሕያው ነው ይኖራል፡፡ የሚያኖረንም ህያው ሆኖ ለዘላለም የሚኖረው እግዚአብሔር ነው፡፡ የሰነፎችን ትምህርት ሰምተን እንዳንሰናከል በማስተዋል እንጓዝ፡፡

## ተግባር

- መምህሩ የእግዚአብሔርን መኖር ላላመኑ ሰዎች ወጣቶች እንዴት ማስረዳት እንደሚችሉ ያወያያቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ባሕርዮ እግዚአብሔር

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** የእግዚአብሔርን ባሕርያት ለወጣቶች ማሳወቅ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** “አቤቱ አንተ ቸርና ይቅር ባይ ታጋሽም ምሕረትህም የዛ አምላክ እንደ ሆንህ አውቄ ነበር፡፡” ዮናስ ፬÷፪

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ዳን. ፪÷፳፣ መዝ. ፻፵፯÷፭፣ ፩ዮሐ. ፩÷፭ እና ኢሳ. ፵፮÷፲

## መግቢያ

የእግዚአብሔር ማንነት መገለጫ ባሕርያት አሉት፡፡ አምላካችን ማንም የማይመስለው በማንም የማንተካው ሉዓላዊ አምላክ ነው፡፡ ባሕርይው ሁሉን የቻለ ሰንነት፤ ፍጥረትን ያሳፈረ ውበት ነው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

### የእግዚአብሔር ባሕርይ

**1. እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው፡-** ኢዮ. ፵፪÷፪፡፡ ዘፍ. ፲፯÷፩፡፡ ባሕርን ያለመርከብ ያሻገረው፣ እሳትን አቀዝቅዞ መናፈሻ ያደረገው፣ የአንበሳን መንጋጋ የዘጋውና ድንግልን በድንግልና እንድትወልድ ያደረገው በሁሉን ቻይነቱ ነው፡፡ የሣራ ማኅፀን በሽምግልና የተከፈተው፣ ፀሐይም በገበኦን የቆመችው በሁሉን ቻይነቱ ነው፡፡ ሰው የሚችለውን ይሠራል፤ የማይችለውን በሁሉን ቻይ አምላኩ በእግዚአብሔር ክንድ ይችላል፡፡

**2. እግዚአብሔር አይለወጥም፡፡** ሚል. ፫÷፮፣ ዕብ. ፮÷፲፯፡፡ በዘመን፣ በሁኔታና በሥፍራ አይለዋወጥም፡፡ የሰው ጠባይ ተለዋዋጭ ነው፤ የእግዚአብሔር ባሕርይ ግን ለዘላለም የማይለዋወጥ ቋሚ ነው፡፡

**3. እግዚአብሔር አይወሰንም፡፡** መዝ. ፻፴፰÷፫፤ ፻፴፱÷፯፣ ሐዋ. ፲፯÷፳፯፡፡ እግዚአብሔር በጊዜ፣ በቦታና በሁኔታ አይወሰንም፡፡ እግዚአብሔር ጊዜን ያስርጃል እንጂ በጊዜ አያረጅም፡፡ እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ቦታ ይገኛል፤ መንፈስ ነውና፡፡

www.zeorthodox.org

**4. እግዚአብሔር ዘላለማዊ ነው፡፡** ራእ. ፩÷፰፤፲፰፡ እግዚአብሔር መጀመሪያና መጨረሻ የለውም፡፡ እርሱ ፊተኛና ኋለኛ፤ መጀመሪያና መጨረሻ፤ አልፋና ኦሜጋ ነው፡፡

**5. እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ ነው፡፡** ኢሳ. ፵፮÷፲፣ ፩ቆሮ. ፪÷፲፣ ፩ሳሙ. ፪÷፫፡፡ ሰው ከዕውቀት

**ከፍሎ ነው የሚያውቀው፤** እግዚአብሔር ግን ሁሉን አዋቂ ነው፡፡ የእውቀትም ምንጭ ነው፡፡ ፩ቆሮ. ፩፲፫÷፱፡፡

6. **እግዚአብሔር ጥበበኛ ነው፡፡** ዳን. ፪÷፳፡፡ **እግዚአብሔር የጥበብ ምንጭ ብቻ ሳይሆን ጥበበኛም ነው፡፡ ጥበቡ ምድርን** አስውቧል፤ ፍጥረትን አስጊጦአል፡፡ ያማረው ሰውነታችን የጥበቡ አደባባይና መገለጫ ነው፡፡

7. **እግዚአብሔር ቸር ነው፡፡** መዝ. ፻፵፭÷፩፣ ማቴ. ፭÷፵፬፡፡
8. **እግዚአብሔር መንፈስ ነው፡፡** ዮሐ. ፬÷፳፬፡፡
9. **እግዚአብሔር ቅን ፈራጅ ነው፡፡** ዘጸ. ፴
10. **እግዚአብሔር ፍቅር ነው፡፡** ፩ዮሐ. ፬÷፰፡፡
11. **እግዚአብሔር መሐሪ ነው፡፡** ዮና. ፬÷፪፡፡
12. **እግዚአብሔር ቅዱስ ነው፡፡** ኢሳ. ፮÷፫፣ ዕን. ፩÷፲፫፡፡
13. **እግዚአብሔር ጻድቅ ነው፡፡** ፩ጴጥ. ፩÷፲፯፡፡
14. **እግዚአብሔር ታማኝ ነው፡፡** ሮሜ. ፫÷፪፡፡
15. **እግዚአብሔር የሚሸፍን ብርሃን ነው፡፡** ፩ዮሐ. ፩÷፭፡፡
16. **እግዚአብሔር ይቅር ባይ ነው፡፡** ዮና. ፬÷፪፡፡

## ማጠቃለያ

እግዚአብሔር ረድቶና ተረድቶ የሚያኖር ዘላለማዊ አምላክ ነው፡፡ ፍቅሩ አይለወጥም፤ ምሕረቱ አይወሰንም፤ ቸርነቱ አይከለከልም፡፡ እግዚአብሔር ሁሉን የሚችልና ሁሉን የሚያስችል ጌታ ነው፡፡

## ተግባር

- መምህሩ ወጣቶች ከዛሬው ትምህርት ምን እንደተማሩ ይጠይቃቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ተአምራት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** የተአምራትን መንፈሳዊ ትርጓሜ ወጣቶች እንዲያውቁ ማድረግ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** "ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል፡፡" ማር. ፲፮÷፲፯

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ሐዋ. ፪÷፳፪፣ ፪ቆሮ. ፲፪÷፲፪

## መግቢያ

ተአምር ማለት ምልክት ማለት ነው፡፡ ተአምራት ማድረግ ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታ አንዱ ነው፡፡ ፩ቆሮ. ፲፪÷፲፡፡ ተአምራት ከዓለም ጥበብ የሚበረታ፣ የሥጋዊውን ዓለም ድርጊት የሚያስንቅ፣ ከሰው አእምሮና ከተፈጥሮ ሕግ በላይ ነው፡፡ ተአምራት በሰው ብቃት ሳይሆን በእግዚአብሔር ሁሉን ቻይነት እና ፈቃድ ይፈጸማሉ፡፡ የሐዲስ ኪዳን ተአምራት የተደረጉት የክርስቶስን ኃይል (አምላክነት) ለመግለጥ ነው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

እግዚአብሔር የተአምራት አምላክ ነው፡፡ መዝ. ፸፩÷፲፰፡፡ እውነተኛ ተአምራት የእግዚአብሔር ሁሉን ቻይነት መገለጫዎች ናቸው፡፡ እግዚአብሔር እስራኤልን ከባርነት ሲያወጣ ታላላቅ ተአምራትን አድርጓል፡፡ በጸናች ክንዱ የኤርትራን ባሕር ከፍሎ ሕዝቡን በደረቅ አሻግሮአል፤ ማንም በማያልፍበት ምድረ በዳ ለአርባ ዓመታት እየመገበ ወደ ርስታቸው ምድር አድርሷል፡፡ ዘዳ. ፬÷፴፬-፴፰፣ ኢያ. ፬÷፳፫-፳፬፣ ኤር. ፪÷፯፡፡ እግዚአብሔር በኤልያስ ዘመን አምላክነቱን ለመግለጥ በእሳት መልሷል፤ ተአምራት አድርጓል፡፡ ፩ነገ. ፲፱÷፲፯-፲፰፡፡

በሐዲስ ኪዳንም የእግዚአብሔር መንግሥት በክርስቶስ መገለጡን ለማብሰር ታላላቅ ተአምራት ተፈጽመዋል፡፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰው አእምሮ በላይ የሆኑ ታላላቅ ምልክቶችን ፈጽሞአል፡፡ እነዚህ ተአምራት የአምላክነቱ መገለጫዎች ናቸው፡፡ የደቀ መዛሙርቱንም አገልግሎት መንፈስ ቅዱስ በብዙ ተአምራት አጅቦታል፡፡ ዕብ. ፪÷፩-፯፣ ፩ቆሮ. ፲፪÷፳፰-፳፱፣ ፪ቆሮ. ፲፪÷፲፪፡፡

የባሕር መከፈል፣ የፀሐይ በገባዖን መቆም፣ የአናብስት አፍ መዘጋትና የእሳት መጥፋት የሙታንም መነሣት ታላላቅ ተአምራት ናቸው፡፡ የታላላቆቹ ሁሉ ታላቅ የሆነው ተአምር ግን ድንግል ማርያም በድንግልና ፀንሳ በድንግልና መውለድ፣ የአምላክ ሰው መሆንና ሞትን ድል መንሳት ነው፡፡ ሊቃውንቱ "ዓለምን ከፈጠረበት ጥበቡ ዓለምን ያዳነበት ይበልጣል" የሚሉት ለዚህ ነው፡፡

www.zeorthodox.org

የክርስቶስ ትንሣኤ ተአምራዊ የሆነ የእምነት መሠረት ነው፡፡ በክርስትና ተአምራት ያመኑትን ይከተላል እንጂ ያመኑት ተአምራትን አይከተሉም፡፡ ማር. ፲፮÷፲፯፡፡ በዘመናችን ብዙዎች በጠንቋዮች አስማትና በሰይጣን ምትሃት በመታለል ወድቀዋል፡፡

ሰይጣን ከሰማይ እሳት ሊያወርድ ይችላልና መንፈስን ሁሉ አትመኑ፡፡

## የተአምራት ዓላማ

የተአምራት ዓላማ ኃይሉንና ለትውልድ ያለውን የሕይወት ዓላማ ማሳወቅ ነው፡፡ ዮሐ. ፪÷፲፩ ተአምራት ሰው ወደ እግዚአብሔር የበረከት ሙላት እንዲመጣ እንጂ ማባበያ አይደለም፡፡ ተአምራት የእግዚአብሔር ሁሉን ቻይነት እና የድንቅ ሥራው መገለጫ ነው፡፡ እጅ በአፍ የሚያስጭኑ ታላላቅ ተአምራቱ ወደ ፍቅሩ መንግሥት የሚጠሩ ናቸው፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያደረጋቸው ተአምራት የአምላክነቱ መገለጫዎች ነበሩ፡፡ ደቀመዛሙርቱ ደግሞ ከእርሱ ለመላካቸውና ለመልእክቱ እውነትነት ማረጋገጫ እንዲሆን ብዙ ተአምራት አድርገዋል፡፡ ይህም በእነርሱ ኃይል ሳይሆን በአምላካቸው ሁሉን ቻይነት እንደሆነ መስክረዋል፡፡ ሐዋ. ፫÷፲፪፡፡

## ማጠቃለያ

ተአምራት የእግዚአብሔር ሁሉን ቻይነት እና የድንቅ ሥራው መገለጫ እንጂ የአገልጋዮች ማባበያና መነገጃ አይደለም፡፡ ከእግዚአብሔር የሆነው እውነተኛው ተአምር ያመኑ ልጆቹን ይከተላል እንጂ ያመኑት ተአምራትን አይከተሉም፡፡ ሰይጣን በሚሠራባቸው ሰዎች ምትሃታዊ ተአምራት እንዳንታለል መጠንቀቅ አለብን፡፡

## ተግባር

- መምህሩ ወጣቶች ከሐሰተኛ ተአምር አድራጊዎች እንዲጠበቁ ይምከራቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ሰሎሞን የእግዚአብሔርን መቅደስ ሠራ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** የእግዚአብሔር መቅደስ በኢየሩሳሌም በሰሎሞን እጅ መሠራቱን ለወጣቶች ማሳወቅ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** “ለዘላለም ስሜ በዚያ ያድር ዘንድ ይህን የሠራኸውን ቤት ቀድሻለሁ” ፩ነገ. ፱÷፫

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ፩ነገ. ፯-፱፣ ሐዋ. ፯÷፵፯

## መግቢያ

የነቢዩ ንጉሥ ዳዊት ልጅ ሰሎሞን የእስራኤል ሦስተኛ ንጉሥ ነው፡፡ ሰሎሞን በጥበቡ፤ በሥብከቱና በልባምነቱ ዝነኛ ንጉሥ ነበር፡፡ የጥበብ መጻሕፍትን የጻፈ ታላቅ ጸሐፊ ነው፡፡ ጥበበኛው ንጉሥ ሰሎሞን በዘመኑ የእግዚአብሔርን መቅደስ ሠራ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

ንጉሥ ዳዊት የእግዚአብሔርን መቅደስ ለመሥራት ይፈልግ ነበር፤ ነገር ግን አምላካዊ ፈቃድ አላገኘም፡፡ ስለዚህ በዘመኑ ለመቅደሱ ሥራ የሚያስፈልጉትን ቁሳቁስ አሟልቶ ዐረፈ፡፡ ፩ዜና. ፳፪÷፪-፲፮፡፡ ልጁ ሰሎሞን የአባቱ ቃልኪዳን ይፈጸም ዘንድ “መቅደሴን ሥራ” የሚል አምላካዊ ፈቃድ አገኘ፡፡ ለሕንጻው ሥራ ሠራተኞችን መለመለ፡፡ ፪ነገ. ፭÷፲፫-፲፯፡፡ በጢሮስ ንጉሥ በኪራም ርዳታ ቤተ መቅደስንና ቤተ መንግሥቱን አነጸ፡፡ ፩ነገ. ፭-፰፣ ፪ዜና ፪-፯፡፡ ከኪራም ውድ የግንባታ መሣሪያዎችን ከእስራኤል ገበሬዎች በተሰበሰበ ብር ገዛ፡፡ ፩ነገ. ፭÷፩-፲፩፡፡

ሰሎሞን የሠራው ቤተመቅደስ አራት ጎን ያለው የድንጋይ ሕንጻ ሲሆን ከፊት ለፊት በረንዳ፣ ከኋላውና ከጎኑ ሦስት መጋዘኖች ነበሩት፡፡ ፩ነገ. ፮÷፩-፲፡፡ ሁለት ትልልቅ የነሐስ ምሰሶዎች በረንዳው ላይ ለጌጥነት ቆመውለት ነበር፡፡ ከበረንዳው ወደ ቤተመቅደሱ የሚያስገቡት በሮች በዕደ ጥበብ ሥራዎች ያጌጡና ተጣጣፊ ነበሩ፡፡ ፩ነገ. ፮÷፴፫-፴፭፡፡

ሕንጻው በሚማርክ ሁኔታ በተጠረቡ ድንጋዮች የተገነባና ልዩ ልዩ ውብ ቅርፆች ባላቸው እንጨቶች የተሠራ ሲሆን፤ እንጨቶቹ በወርቅ ተለብጠው ነበር፡፡ የመቅደሱ ውስጠኛ ክፍል ሁለት ክፍሎች ነበሩት፡፡ የመጀመሪያው ኢደባባይ ሁለተኛው የአምልኮ ሥፍራ ነበር፡፡ የቃልኪዳኑ ታቦት የነበረው በሁለተኛው ክፍል ነው፡፡

www.zeorthodox.org

ከሕንጻው ውጪ ባለው ገላጣ ሜዳ ላይ ትልቅ የነሐስ የመሥዋዕት ማቅረቢያ ነበር፡፡ የቤተ መቅደሱ ጌጣጌጥ ውድነትና የዕቃዎች ብዛት በጣም ማራኪና የሚያጓጉ በመሆናቸው ለብዙ ጠላት መነሻ ምክንያት ነበር፡፡

ሰሎሞን እጅግ የተዋበውን ታላቅ ቤተ መቅደስ ሠርቶ ከፈጸመ በኋላ ሃያ ሁለት ሺህ በሬዎችና አንድ መቶ ሃያ ሺሕ በጎችን መሥዋዕት አድርጎ አቀረበ፡፡ ፩ነገ. ፰÷፷፫፡፡ እግዚአብሔርን እንዲባርክለት በጸሎት ለመነ፡፡ እግዚአብሔርም በመቅድሱ ተገልጦ

“በፊቴ የጸለይኸውን ጸሎትህንና ልመናህን ሰምቻለሁ፤ ለዘላለም ስሜ በዚያ ያድር ዘንድ ይህን የሠራኸውን ቤት ቀድሼአለሁ፤ ዓይኖቼና ልቤ በዘመኑ ሁሉ በዚያ ይሆናሉ፡፡” በማለት የዘላለም ቃል ኪዳን ሰጠው፡፡

## ማጠቃለያ

የዳዊት ልጅ ሰሎሞን ውድ በሆኑ ዕቃዎች የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ሠራ፡፡ እግዚአብሔርም ቃል ኪዳን ሰጠው፡፡

## ተግባር

- መምህሩ ወጣቶች ጠቢቡ ንጉሥ ሰሎሞን የሠራው ቤተ መቅደስ መቼ እንደፈረሰ ታሪክን መሠረት በማድረግ እንዲወያዩ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# ተስፋ መቁረጥ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ባለሙሉ ተስፋ ሆነው እንዲኖሩ መምከር፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** "እናመነታለን እንጂ ተስፋ አንቆርጥም" ፪ቆሮ. ፬÷፰

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ፪ጴጥ. ፫÷፱፣ ፩ዮሐ. ፪÷፳፫ እና ምሳ. ፳፫÷፲፰

## መግቢያ

ተስፋ መሠረት የሌለው የምኞት አሳብ አይደለም፡፡ ተስፋ በክርስቶስ የተሰጠ ሊገለጥ ያለ እውነት ነው፡፡ በዓይን ባይታይም በእምነት የተረጋገጠ ነው፡፡ ዕብ. ፲፩÷፩፡፡ ተስፋ የዚህን ዓለም ድንበር ያልፋል፡፡ ሰው ያለ ተስፋ ሊኖር አይችልም፡፡ ሕይወትም ያለተስፋ ትርጉም ታጣለች፡፡ ተስፋ መቁረጥ ማለት ሕይወትን ሆነ ብሎ ወይም አቅዶ ትርጉም አልባ እንዲሆን ማድረግ፤ የመኖርን ኃይል ማጣት ማለት ነው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

ተስፋ የእውነተኛ እምነት ማኅተም ነው፡፡ ተስፋ መቁረጥ የእምነት ማነስ ውጤት ነው፡፡ ተስፋ መቁረጥ መኖር ማቆም ነው፡፡ ተስፋ ሰጪው እግዚአብሔር ታማኝ መሆኑን በማመን መኖር አለብን፡፡

እግዚአብሔር ለአብርሃም ተስፋ ሰጠው፡፡ የተስፋው ቃል ፍጻሜ በዘገየ ጊዜ ግን ተስፋ ቆረጠ፡፡ ዘፍ ፲፫÷፩፡፡ እግዚአብሔርም ተስፋውን በማጽናት አበረታው፤ አብርሃምም አመነ፡፡ እግዚአብሔር በጊዜው የአብርሃምን ተስፋ ፈጸመለት፡፡ ዘፍ. ፳፩÷፩፡፡ እግዚአብሔር የሰጠን ተስፋ የራቀ ቢመስልም በጊዜው መፈጸሙ አይቀርም፤ ስለተስፋ ቃሉ ጌታ አይዘገይምና፡፡ ፪ጴጥ. ፫÷፱፡፡

እግዚአብሔር ለሙሴ ተስፋ ሰጠው፤ ሙሴም ከሞት ተነሥቶ ተስፋው ሲፈጸም አየ፡፡ ማቴ. ፲፯÷፫፡፡ እግዚአብሔር ከሙታን ቀስቅሶም እንኳን የተስፋችንን ዓለም ሊያሳየን የታመነ ነው፡፡

ሰው ተስፋ የሚቆርጠው ያሰበው አልሆን፤ የተመኘው አልሳካ፤ የፈለገው አልፈጸም፤ የጠበቀው አልደረግ ሲለው ነው፡፡ የፈለግነው ነገር በፈለግነው ጊዜ ስላልሆነ፤ የናፈቅነው ስለራቀ ተስፋ መቁረጥ የለብንም፡፡

www.zoorthodox.org

ተስፋ የሚቆርጡ ሰዎች ሕይወትን በደስታ አይኖሯትም፡፡ ለበሽታና ለጭንቀትም ይዳረጋሉ፡፡ ተስፋ ስንቆርጥ ራሳችንን መጥላት፣ ባለን አለመደሰት፣ ስልቹዎችና ሞታችንን ናፋቂዎች እንሆናለን፡፡ ወደሚፈልገው የሞት ወጥመድ ለማስገባት የተመቻቹ መሆናቸው ተስፋ በሚቆርጡ ሰዎች ሰይጣን ደስተኛ ይሆናል፡፡ ወደ መዳፉ እየገቡ ነውና፡፡ የአምላካችን ፍላጎት ግን በተስፋ ደስ

እያለን እንድንኖር ነው፡፡

ተስፋ መቁረጥ እምነትን ያጎድላል፤ ፍቅርን ይጥላል፡፡ እምነት፣ ተስፋና ፍቅር የሕይወት ምሰሶዎች መሆናቸውን አንዘንጋ፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ በብዙ መከራ መካከል እንኳ እያለፈ “ተስፋ አንቆርጥም” አለ፡፡ ክርስቲያን ተስፋ አይቆርጥም፤ አይጣልምና፡፡ ፪ቆሮ. ፬÷፰፡፡

ተስፋ ለማድረግ ማመን፣ የማንችለውን ሁሉን ለሚችለው አምላክ መተው፣ መመኪያችን እግዚአብሔር መሆኑን ማመን እና መታመን አለብን፡፡ ባለን መደሰት በሚያጋጥሙን ችግሮች ከመንበርከክ እና ተስፋ ከመቁረጥ ይልቅ መፍትሔ ላይ ብቻ ማተኮርና ዘላለማዊን ተስፋ ማሰብ ያስፈልጋል፡፡ ሰው ተስፋ ማድረግ ያለበት እግዚአብሔርን ነው፤ አያሳፍርምና፡፡ እርሱን ተስፋ የሚያደርጉ ኃይላቸው ይታደሳል፤ እንደንስር በክንፍ ይሮጣሉ፤ አይታክቱም፡፡ ይሄዳሉ አይደክሙም፡፡ መዝ.፻፳፭÷፩፣ ኢሳ. ፵÷፴፩፡፡

## ማጠቃለያ

ተስፋ መቁረጥ የእምነት ማነስ ውጤት ነው፡፡ ሰው ያለተስፋ ሊኖር አይችልም፡፡ ያለ ተስፋ ሕይወት ትርጉም አልባ ትሆናለች፡፡ ተስፋ መቁረጥ ማለት በፈቃዳችን የመኖርን ኃይል መጣል ማለት ነው፡፡ እግዚአብሔርን ተስፋ እናድርግ፤ በተስፋ ደስ ይበለን እንጂ ተስፋ አንቁረጥ፡፡

## ተግባር

- ወጣቶች በምን ተስፋ ይቆርጣሉ? በሚል ርእስ መምህሩ ያወያያቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ኤልያስ የመበለቷን ልጅ ከሞት አስነሣ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** የጻድቅ ሰው ጸሎት ለሥራዋ እጅግ ኃይል እንዳላት ማስገንዘብ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** "አቤቱ የዚህ ብላቴና ነፍስ ወደ እርሱ ትመለስ ዘንድ እለምንሃለሁ፡፡" ፩ነገ. ፲፯÷፳፩

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ፩ነገ. ፲፯÷፩-፳፬ እና ያዕ. ፭÷፲፯

## መግቢያ

ኤልያስ ለእግዚአብሔር በመቅናቱ የሚታወቅ ታላቅ ነቢይ ነው፡፡ ኤልያስ ጸጋ የበዛለት መምህር፤ የድሃዋን ጎጆ የባረከ ጻድቅ፣ ሰማይን ለሦስት ዓመት ከስድስት ወር ዘግቶ ዝናብን ያቆመ ብርቱ ጸሎተኛ፣ የኤልዛቤልን መንፈስ የተዋጋና ለእግዚአብሔር ክብር የቆመ ታላቅ ነቢይ ነው፤ ትንቢቱ በጽሑፍ አልሰፈረም፤ በቃል የተላለፈለት ነቢይ ነው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

በአንድ ወቅት ነቢዩ ኤልያስ በሲዶና አጠገብ በሰራፕታ ወዳለች አንዲት መበለት ቤት እንዲሔድ የእግዚአብሔር ድምፅ መራው፡፡ በመበለቷ ቤት የቀራትን ትንሽ ዱቄት እንጎቻ በላ፡፡ የመበለቷንም ቤት ባረከው፡፡ በነቢዩ በረከት ከተሞላው የመበለቷ ቤት የረኃቡ ዘመን እስኪፈጸም ድረስ ዱቄት ከማድጋ አላለቀም፤ ዘይት ከማሰሮ አልጎደለም፡፡ ከዚያም በኋላ የመበለቷ ልጅ ታመመ፤ ሞተም፡፡ እርስዋም "ኤልያስ የእግዚአብሔር ሰው ሆይ ከአንተ ጋር ምን አለኝ? ኃጢአቴንስ ታስብ ዘንድ ልጄንስ ትገድል ዘንድ ወደ እኔ መጥተሃልን?" አለችው፡፡

ኤልያስም "ልጅሽን ስጪኝ" አላት፡፡ ከብብትዋም ወስዶ ወደ ሰገነት አወጣውና በአልጋ ላይ አጋደመው፡፡ እጆቹን ዘረጋና "አቤቱ አምላኬ ሆይ ልጅዋን በመግደልህ ይህችን ትቀበለኝ የነበረችቱን ባልቴት አስጨነቅኻትን?" ብሎ ጮኸ፡፡ በብላቴናውም ላይ ሦስት ጊዜ ተዘረጋበት፤ ወደ እግዚአብሔርም፤ "አቤቱ አምላኬ ሆይ የዚህ ብላቴና ነፍስ ወደ እርሱ ትመለስ ዘንድ እለምንሃለሁ" ብሎ ጸለየ፡፡

እግዚአብሔር የአገልጋዩን የኤልያስን ጸሎት ሰማ፡፡ የብላቴናውም ነፍስ ተመለሰች ሕፃኑም ዳነ፡፡ ኤልያስ ብላቴናውን ይዞ ከሰገነቱ ወደ ቤት አወረደው፡፡ "እነሆ ልጅሽ በሕይወት ይኖራል" አላት፡፡ ሴቲቱም ኤልያስን "የእግዚአብሔር ሰው እንደሆንህ የእግዚአብሔርም ቃል በአፍህ እውነት እንደሆነ አወቅሁ" አለችው፡፡ ይህ የተፈወሰ (ከሞት የዳነ) ልጅ ነቢዩ ዮናስ ነው የሚሉ አሉ፡፡

www.zeorthodox.org

በዚህ ታሪክ የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል እንደምታደረግ ተምረናል፡፡ ቅዱስ ያዕቆብ፤ የኤልያስ ጸሎት የሰማይን መስኮት እንደዘጋና እንደከተፈ በመጥቀስ የጸሎትን ኃይል አስተምሯል፡፡

## ማጠቃለያ

የሰራፕታዋ መበለት ልጅ በሞተ ጊዜ ኤልያስ ጸለየ፡፡ እግዚአብሔርም የነቢዩን ጸሎት ሰማ፡፡ የመበለቷ ልጅ ዳነ፡፡ የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል እንደምታደርግ ተገለጠ፡፡

## ተግባር

♦ መምህሩ ወጣቶች ስለኤልያስ የሚያውቁትን እንዲያካፈሉ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# አባ ጽጌ ድንግል

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንን ባለውለታዎች እንዲዘክሩ ማድረግ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** “ሰው ዓለሙን ሁሉ ሲያተርፍ ነፍሱንም ሲያጎድል ምን ይጠቅመዋል?” ማቴ. ፲፮÷፳፮

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** (የኢትዮጵያውያን ተወላጆች ቅዱሳን ታሪክ፤ ሊቀ ብርሃናት መርቆርዎስ አረጋ)

## መግቢያ

- ወጣቶች፤ ስለ አባ ጽጌ ድንግል የምታውቁትን ለመምህራችሁ ንገሩ?
- አባ ጽጌ ድንግል በስንተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነበሩ?
- አባ ጽጌ ድንግል የማኅሌተ ጽጌ ደራሲ መሆኑን ታውቃላችሁ?

## የሳምንቱ ትምህርት

አባ ጽጌ ድንግል ሃገራቸው ወሎ ቦረና ሲሆን ደራሲና ማሕሌታዊ ናቸው፡፡ አባ ጽጌ ድንግል እግዚአብሔርን በማምለክ በጽድቅ ሥርዓት የተጓዙ ኢትዮጵያዊ ጻድቅ ሲሆኑ ማሕሌተ ጽጌን ደርሰዋል፡፡

በቤተ ክርስቲያናችን በወርኀ ጽጌ የሚዘመረው ‹‹ማሕሌተ ጽጌ›› የዚህ ታላቅ አባት ድርሰት ነው፡፡ ማሕሌተ ጽጌ ምድርን በሥነ ጽጌያት ያስጌጠው ጌታ ከድንግል መወለዱን በመጥቀስ ድንግልን በምስጋና ቃል ያወድሳል፡፡

አባ ጽጌ ድንግል በቆሎና በውኃ ለዘጠኝ ዓመታት በትጋት ጸልየዋል፡፡ በስማቸው የተሠራ ከአለት ተፈልፍሎ የታነፀ ውቅር ቤተክርስቲያን ከአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ገዳም በእግር ጉዞ የስድስት ሰዓት ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ አባ ጽጌ ድንግል ጥቅምት ፳፯ ቀን ያረፉ ሲሆን መካነ ዕረፍታቸውም በዚሁ ስፍራ ነው፡፡

www.zeorthodox.org

ብዙ የብራና መጻሕፍትን የጻፉት አባ ጽጌ ድንግል መጻሕፍታቸው በስማቸው በታነፀው ቤተክርስቲያን ይገኛሉ፡፡ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ማሕሌተ ጽጌ በተቆመ ቁጥር የዚህን ታላቅ አባት ፍሬ እናያለን፡፡ አብዛኛዎቹ ሥራዎቹ ከአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ጋር ይቀራረባሉ፡፡

## ማጠቃለያ

አባ ጽጌ ድንግል በ፲፱ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ የነበሩ ኢትዮጵያዊ ጻድቅ ናቸው፡፡ በወርኃ ጽጌ የሚቆመውን ‹‹ማሕሌተ ጽጌ››ን ደርሰዋል፡፡

## ተግባር

- መምህሩ ወጣቶች ‹‹ማሕሌተ ጽጌ››ን እንዲያጠኑና ይዘቱን ለጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# ኢትዮጵያዊው ሙሴ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ስለኢትዮጵያውያን ቅዱሳን እንዲያውቁ ማድረግ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** “ስለጽድቅ የሚሰደዱ ብፁዓን ናቸው” ማቴ. ፭÷፲

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** (ዝክረ ቅዱሳን ዘተዋሕዶ፣ በአዜብ በርሄ፣ 2000 ዓ.ም)

## መግቢያ

ወጣቶች ስለ ኢትዮጵያዊ ሙሴ ስምታችሁ ታውቃላችሁ?
የሰማችሁትን ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ?
ሙሴ ጸሊም ለምን ተባለ?

## የሳምንቱ ትምህርት

ሙሴ ጸሊም (ኢትዮጵያዊው ሙሴ) ከአባ መቃርስ ጋር ከመገናኘቱ በፊት በባርነት የሚኖር፣ በፀሐይ የሚያመልክ፣ በነፍስ ገዳይነቱ የታወቀና የሌቦች ሁሉ አለቃ ነበር፡፡ በግብጽ ናትሩን በሚገኘው ገዳም ቅዱስ ኤስድሮስን ካገኘ በኋላ ስለ ክርስትና ሃይማኖት እውነተኛነትና ስለ እግዚአብሔር ፍቅር ተማረ፡፡ ከእኩይ ምግባሩ ተመለሰ፡፡ ራሱን ከሰሰ፤ ለንሰሐ የሚገባ ፍሬ አፈራ፤ ከታላቁ መቃርስ ጋር በመገናኘት ንስሐ ገብቶ ተጠመቀ፡፡

ሙሴ ጸሊም (ኢትዮጵያዊው ሙሴ) በጥምቀት የእግዚአብሔርን የልጅነት ሥልጣን ከተቀበለ በኋላ ኃጢአቱ እንደተሰረየለት የእግዚአብሔር መንፈስ ለቅዱስ መቃርስ ገለጸለት፡፡ ሙሴ ጸሊም ሥርዓተ ምንኩስናን እየተማረ የቅድስናን ኑሮ ቀጠለ፡፡ የዓለምን ፍቅር ከልቡ አውጥቶ መነኮሰ፤ የቅስና ማዕረግ ተቀበለ፡፡ በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ከስድስቱ ደቀመዛሙርቱ ጋር በበርበርያን ወታደሮች በመገደል ታሪኩን በሰማዕትነት ሞት ደመደመ፡፡

www.zeorthodox.org

ሙሴ ጸሊም በአንድ ወቅት በጥፋተኛ መነኩሴ እንዲፈርድ ለዳኝነት መመረጡን ሲሰማ፤ ቀዳዳ ባለው ጆንያ አሸዋ ሞልቶ በጀርባው ተሸክሞ ወደ መነኮሳቱ መጣ፡፡ በጀርባው ከተሸከመው ቀዳዳ ጆንያ የሚፈስሰውን አሸዋ እያዩ ለተገረሙት መነኮሳት “የእኔ ኃጢአት ከኋላዬ እንደዚህ አሸዋ ይከተለኛል፤ ለእኔ ግን አይታየኝም፡፡ ዛሬ ደግሞ እኔም በሌሎች ጥፋት ላይ እፈርድ ዘንድ አይገባኝም፡፡” በማለት መለሰላቸው፡፡ ይህን የሰሙት ከሳሽ መነኮሳትም አጠፋ ለተባለው አባት ይቅርታ አደረጉለት፤ ይቅርታም ጠየቁ፡፡

## ማጠቃለያ

ኢትዮጵያዊው ሙሴ ወደ ክርስቶስ መንግሥት መጥቶ በመልካም የቅድስና ተግባሩ ቀድሞ በኃጢአት ያደፈ ታሪኩ የተለወጠለት ጻድቅ ሰው ነው፡፡ በምናኔ፣ በትሕትናና በትዕግሥት ዘመኑን የፈጸመ፤ በሰማዕትነትም ያረፈ ታላቅ አባት ነው፡፡

## ተግባር

- መምህሩ፤ ወጣቶች ከሙሴ ጸሊም ታሪክ ምን እንደተማሩ ይጠይቃቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ቅዱሳን መላእክት ሎጥን ከሰዶም አወጡት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሰዎች በመላእክት እንደሚጠበቁ እና ከጥፋት እንደሚድኑ ለወጣቶች ማስገንዘብ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** “እንዳትጠፋም ወደተራራው ሸሽተህ አምልጥ” ዘፍ. ፲፱÷፲፯

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ዘፍ. ፲፱÷፩-፳፫፣ ፪ጴጥ. ፪÷፯

## መግቢያ

ቅዱሳን መላእክት ዋና ሥራቸው እግዚአብሔርን ሳይደክሙ ማመስገንና ሰዎችን ሳይሰለቹ መጠበቅ ነው፡፡ ከእግዚአብሔር እየተላኩ ችግረኞችን ይረዳሉ፡፡ ቅዱሳን መላእክት እግዚአብሔርን በሚፈሩ ሰዎች ዙሪያ አሉ፤ ከክፉም ይጠብቃሉ፡፡ መዝ. ፴፫÷፯፣ ዕብ. ፩÷፲፬፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

ሎጥ እግዚአብሔርን የሚፈራ አባት ነበር፡፡ በኃጢአተኞች መካከል ሲኖር ሳለ ጻድቅ ነፍሱን አስጨንቆ በጽድቅ የተጓዘ ቅዱስ ነው፡፡ በዙሪያው ይኖሩ የነበሩ የሰዶም ሰዎች በዐመጽ ጸንተው ሲኖሩ እግዚአብሔር ሊቀጣቸው ፈለገና ሁለት መላእክትን ወደ ሰዶም ላከ፡፡ መላእክቱ በሎጥ ቤት እንግድነት ገብተው ዕረፍት አደረጉ፡፡ ሎጥም ለቅዱሳን መላእክት የፍቅር ግብዣ አደረገ፡፡

ሲመሽ ዐመጸኞቹ የሰዶም ሰዎች የሎጥን ቤት ከበቡ፡፡ ሎጥን ጠርተው “በዚህ ሌሊት ወደ ቤትህ የገቡትን ሰዎች አምጣ እንወቃቸው” አሉት፡፡ ሎጥ “ወንድሞቼ ሆይ ወንድ ያላወቁ ሁለት ሴቶች ልጆቼን ልስጣችሁ በቤቴ ጣራ ሥር ባረፉት እንግዶች ግን ክፉ አታድርጉ፡፡” አላቸው፡፡

የሰዶም ሰዎች ግን የሎጥን ቤት በር ለመስበር ሞከሩ፡፡ ሁለቱ መላእክት ሎጥን ወደ ቤቱ አስገብተውት፣ የሰዶምን ሰዎች ዓይን አሳወሩአቸው፡፡ በክፉ ሥራቸው የተቀጡት የሰዶም ሰዎች ዐይናቸው ታውሮ ደጃፉንም ለማግኘት ሲፈልጉ ደከሙ፡፡

ሁለቱ መላእክት ሎጥን “ቤተሰብህን ሰብስብ፤ ይህችን ከተማ ልናጠፋ ከአምላክህ ተልከን መጥተናል፤ የግፋቸው ጩኸት በእግዚአብሔር ፊት ደርሶአልና፡፡” አሉት፤ ሎጥም ቤተሰቡን ሰብስቦ “ተነሡ ከዚህ ስፍራ ውጡ እግዚአብሔር ይህችን ከተማ ያጠፋልና” አላቸው፡፡ አማቾቹ ግን የሚያፌዝባቸው መስሏቸው በዘገዩ ጊዜ ቅዱሳን መላእክት እጆቻቸውን ይዘው ልትጠፋ ካለችው ከተማ አወጡአቸው፡፡ ወዲያውኑ የሰዶም ምድር በእሳት ነደደች፡፡

በዐመፃቸው ከጠፉት ሰዶማውያን ጋር የእግዚአብሔር ሰው ሎጥ አልጠፋም፡፡ እግዚአብሔር መላእክቱን ልኮ እርሱን

www.zeorthodox.org

በመፍራት የኖረውን ሎጥን አድኖታልና፡፡ ከኃጢአት ርቀው እግዚአብሔርን የሚያመልኩ ሰዎች ከሞትና ከመከራ ይድናሉ፤ እግዚአብሔር ሳያንቀላፋ ሕዝቡን የሚጠብቅ አምላክ ነውና፡፡

## ማጠቃለያ

ሎጥ በኃጢአተኞች መካከል በጽድቅ ሥርዓት የኖረ ቅዱስ ሰው ስለነበረ እግዚአብሔር መላእክቱን ልኮ ልትጠፋ ካለችሁ የሰዶም ከተማ አወጣው፤ አመፀኞችን ግን ቀጣቸው፡፡

## ተግባር

- መምህሩ ወጣቶችን "ከዛሬው ትምህርት ምን ተማራችሁ?" በማለት ያወያያቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# የተፈጥሮ አደጋዎች

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ስለ ተፈጥሮ አውቀው እንዲንከባከቡ፣ እንዲጠብቁና በአግባቡ እንዲጠቀሙ መምከር፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** "ቀኖቹ ክፉዎች ናቸውና ዘመኑን ዋጁ" ኤፌ. ፭÷፲፮

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ሮሜ. ፩÷፳

## መግቢያ

ተፈጥሮ የእግዚአብሔርን ጥበብ ማድነቂያ የምስጋና ርእስ ነው፡፡ ተፈጥሮን በማየት ፈጣሪውን ማድነቅ ተገቢ ነው፡፡ ተፈጥሮን በአግባቡ መጠቀም ባለመቻላችን በየጊዜው የተፈጥሮ አደጋዎች እየተከሠቱ ነው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

የተፈጥሮ ፈጣሪ እግዚአብሔር ነው፡፡ እግዚአብሔር የፈጠረው ውብ ዓለም በውበቱ እንዲቀጥልና ተፈጥሮ የሰው ልጅ የሥጋት ሁሉ ምክንያት እንዳይሆን ስለ ተፈጥሮ በሚገባ ማወቅ፣ መንከባከብ እና መጠበቅ አስፈላጊ ነው፡፡

**የተፈጥሮ አደጋዎች፡-** የመሬት መንቀጥቀጥና መንሸራተት፣ የአየር ብክለት፣ የዖዞን መሳሳት፣ የሙቀት መጠን መጨመር፣ ድርቅ፣ ጐርፍ፣ የእሳተ ገሞራ ፍንዳታ፣ አውሎ ነፋስና ሱናሚ ከተፈጥሮ አደጋዎች ይካተታሉ፡፡

### የተፈጥሮ አደጋዎች ለምን ይከሠታሉ?

- ሰው ተፈጥሮን በሚገባ ተረድቶ መንከባከብ እና መጠበቅ ስላልቻለ
- ሰው ሠራሽ ነገሮች ዘላቂውን የሕይወት ውበት ስለሚያደበዝዙ (ለምሳሌ፡- ፋብሪካዎች፣ መኪናዎች፣ ሌሎችም የፋብሪካ ውጤቶች እና ተረፈ ምርቶች ወዘተ)
- ሰው የተፈጥሮ ሁሉ ፈጣሪ የሆነውን እግዚአብሔርን በኃጢአቱ ስለሚያሳዝን
- በየጊዜው እየጨመረ የመጣው የሕዝብ ብዛትና የሰው አልጠገብ ባይነት (የምኞቱ ብዛት)

www.zeorthodox.org

## የተፈጥሮ አደጋዎችን እንዴት መከላከል ይቻላል?

- ተፈጥሮን በሚገባ በመረዳት፣ በመንከባከብ እና በመጠበቅ
- የተጠቀምነውን በመተካት (ለምሳሌ:- ዛፍ ስንቆርጥ ሌላ መትከል)
- በእንጨት ማገዶ፣ በእንፋሎትና በነዳጅ ኃይል የሚሠሩ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በኤሌክትሪክ በመተካት
- የዕፀዋት ተክሎችን በማብዛት
- ያለኝ ይበቃኛል ማለትን በመልመድና ለቀጣዩ ትውልድ በማሰብ
- ተፈጥሮን የሚጎዱ ነገሮችን በመቀነስ
- ከተፈጥሮ ፈጣሪ ጋር በመስማማት
- ተፈጥሮን በአግባቡ በመጠቀም
- ለተፈጥሮ አደጋ አጋላጭ ሁኔታዎችን በማጥፋት

### ማጠቃለያ

የተፈጥሮ አደጋዎች የሚከሠቱት በአምላክ ቁጣ ብቻ ሳይሆን ሰው በአግባቡ ተፈጥሮን ባለመጠቀሙ ነው፡፡ ተፈጥሮን መረዳት፣ መንከባከብና በአግባቡ መጠቀም ይጠበቅብናል፡፡

### ተግባር

- መምህሩ ወጣቶችን ተፈጥሮን እንዴት እንከባከብ? በሚል ርእስ ያወያያቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ትዕግሥት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** *ወጣቶች ትዕግሥትን ገንዘብ እንዲያደርጉ መምከር፡፡*

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *"በትዕግሥት የጸኑትን ብፁዓን እንላቸዋለን፡፡" ያዕ. ፭÷፲፩*

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** *ዕብ. ፮÷፲፩-፲፪፣ ሮሜ. ፲፪÷፲፪ እና ፩ጴጥ. ፫÷፳*

## መግቢያ

*ትዕግስት ፀብን የሚያቀዘቅዝ የፍቅር መንፈስ፤ የሰውን እጅ ደም ከማፍሰስ የሚጠብቅ ልበ ሰፊነት ነው፡፡ ትዕግሥተኛ ሰው ማለት፤ የተረጋጋ መንፈስ ያለው፣ ልበ ሰፊ የሆነ፣ የማይታወክ ሰብእና ያለው፣ ቻይ፣ ጽኑዕና ትሑት ማለት ነው፡፡ ትዕግሥት ቁጣን ያበርዳል፤ የወዳጅነትን ዕድሜ ይጨምራል፤ መልካም ግንኙነትን ከመበላሸት ይታደጋል፡፡ ትዕግሥት የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ነው፡፡ ገላ. ፭÷፳፪፡፡*

## የሳምንቱ ትምህርት

*ትዕግሥት የግንኙነት ዋስትና ነው፡፡ በመከራ መጽናትን፣ ቁጣ እስኪያልፍ የሚደረግ ጸጥተኝነትን፣ ልበ ሰፊነትን፣ በነገር ሁሉ መረጋጋትንና ቻይነትን ያጠቃልላል፡፡ ፩ጴጥ. ፪÷፳፩፡፡ ሮሜ. ፲፪÷፲፪፡፡*

*ትዕግሥት የእግዚአብሔር የባሕርይ መገለጫ ነው፡፡ እግዚአብሔር ታጋሽ ነው፡፡ መዝ. ፻፲፫÷፰-፱፣ ዮና. ፬÷፪፡፡ እግዚአብሔር ለቁጣ የዘገየ ለምሕረት የቀና አምላክ ነው፡፡ ኃጥአንን ወደ ንስሐ የሚያመጣቸው የእግዚአብሔር ትዕግሥት ነው፡፡ እግዚአብሔር ፍርድን በማዘግየት ሰዎች ሁሉ ወደ መዳን እንዲደርሱ ስለመዳናቸው ይታገሳል፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስ "ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ ማንም እንዳይጠፉ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሳል" በማለት አስተምሯል፡፡ ፪ጴጥ. ፫÷፱፡፡*

*መጽሐፍ ቅዱስ በትዕግሥት የጸኑትን ብጹዓን ይላቸዋል፡፡ ኢዮብ ታገሠ እግዚአብሔር በእጥፍ ባረከው፡፡ ያዕ. ፭÷፱-፲፩፡፡ አብርሃም ታገሠ ምድረ ርስትን ወረሰ፡፡ ዕብ. ፮÷፲፭፡፡ ሣራ ታገሠች በስተርጅና ዘርን ለመፀነስ ኃይልን በእምነት አገኘች፡፡ ዕብ. ፲፩÷፲፩፡፡*

www.zeorthodox.org

*በእምነትና በትዕግሥት የተስፋውን ቃል የሚወርሱትን እንድንመስል ቃሉ ያዘናል፡፡ ዕብ. ፮÷፲፪፡፡ ብንታገስ የተሻለ እንቀበላለን፡፡ ብንታገስ እንከብራለን "በለሷን የሚጠብቅ ፍሬዋን ይበላል ጌታውን የሚጠብቅ ይከብራል" እንደተባለ፡፡ ትዕግሥት በፍቅር፣ በደስታ፣ በትሕትናና በይቅርታ ይገለፃል፡፡ የመታገስ ፍሬው ብዙ፤ ክብሩም ትልቅ ነው፡፡ ስለዚህ ለሁሉም ነገር ትዕግሥት ያስፈልጋል፡፡ ባለመታገስ ምክንያት የሚበላሹ ነገሮች ብዙ ናቸው፡፡ ለጥቂት ደቂቃዎች መታገስ ባለመቻላቸው ምክንያት ዘላቂ*

ሕይወታቸውን ያበላሹ ጥቂቶች አይደሉም፡፡

## ማጠቃለያ

ትዕግሥት በእምነት ተስፋ የምናደርጋቸውን የምንቀበልበት እጅ ነው፡፡ ቁጣን የሚያሳልፍ ብርታት ነው፡፡ የትዕግስት ሕይወት የተሻለ ለመቀበልና በእምነት ጸንተን በምንጠብቀው ጌታ ለመክበር የሚያበቃ ክርስቲያናዊ ሕይወት ነው፡፡ በሁሉ እንታገስ፡፡

## ተግባር

- ወጣቶች የትዕግሥትን ሕይወት እንዴት ማሳደግ ይችላሉ? በሚል ርእስ መምህሩ ያወያያቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሰጠው ተስፋ ተፈጸመ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** እግዚአብሔር በተስፋ ቃሉ የታመነ እንደሆነ ወጣቶች እንዲገነዘቡ ማድረግ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** "እግዚአብሔር የተስፋውን ቃል ለሚወርሱ ፈቃዱ እንደማይለወጥ አብልጦ ሊያሳያቸው ፈቀደ፡፡" ዕብ. ፮÷፲፯

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ኢያሱ. ፯-፲፭ እና ዕብ. ፬÷፰-፲

## መግቢያ

እግዚአብሔር በተስፋ ቃሉ የታመነ ነው፡፡ የተናገረውንም በመፈጸም የታወቀ ነው፡፡ እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለዘሩ አዲሲቱን ምድር እንደሚሰጣቸው በራሱ ማለ፤ ሕዝቡን በማውረስ ተስፋቸውን ፈጸመ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

እግዚአብሔር ለእስራኤል አባቶች የገባውን ቃል ኪዳን፤ የሰጠውንም ተስፋ ፈጽሞአል፡፡ በቃል ኪዳናቸውም ለልጆቻቸው ሞገስ በመሆን ከሞትና ከጠላት አድኖአቸዋል፡፡ ለኖህ፣ ለአብርሃምና ለያዕቆብ የሰጠውን ተስፋ በገዛ ዘመናቸው ፈጽሞ በልባቸው ሃሴት ጨመረ፡፡ ኖህን ከሞት በመከለል፤ አብርሃምን በልጅ በመባረክና ምድረ ርስትን በማውረስ፤ ያዕቆብን ባርኮ አብዝቶ በመመለስ ተስፋቸውን ፈጽሞአል፡፡

እግዚአብሔር ከያዕቆብ ልጆች ጋር ቃል ኪዳን አደረገ፡፡ የባርነትን ቀንበር ሰብሮ በነፃነት ወደ ተስፋይቱ ሃገር እየመገበ በረሐውን ገነት አድርጎ መራቸው፡፡ ለሕዝቡ የሰጠው ተስፋ ለዘራቸው በተሰጣቸው በከነዓን መኖር ነው፡፡ እግዚአብሔር የኢያሪኮን ቅጥር ሰብሮ፤ የጠላትን ጉልበት አርዶ አወረሳቸው፡፡ ይህንም በማድረጉ ለሕዝቡ የሰጠው ተስፋ ተፈጸመ፡፡

እግዚአብሔር ለእስራኤል ዘነፍስ (ለአዲስ ኪዳን አማኞች) የተሻለ ተስፋ ሰጥቷል፡፡ በክርስቶስ በማመን ተጠምቀን የልጅነት ሠልጣን ለተቀበልነው ሰማያዊት ኢየሩሳሌምን እንደሚያወርሰን የጸና ተስፋ ሰጥቶናል፡፡ ይህም በጊዜው የሚፈጸም ነው፡፡ አምላክ ሁሉን አዲስ ያደርጋል፤ እንባን ያብሳል፤ ሐዘንን ያርቃል፤ አሮጌውን ሥርዓት ያሳልፋል፤ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ባመንበት ልጆቹ ፊት ይገለጣሉ፡፡ አምነን፣ አክብረነው፣ በእምነት ጸንተን እና ትእዛዙን አክብረን እንሙት እንጂ ሊያወርሰን የታመነ ነው፡፡ ራእ. ፳ ፣ ፳፩፡፡

ከእግዚአብሔር የሆነ ተስፋ በእምነት የተረጋገጠ ነው፡፡ እግዚአብሔር ተስፋ የሚያደርጉትን የማያሳፍር፤ ስለ ተስፋ ቃሉም

www.zoorthodox.org

የማይዘገይ እውነተኛ አምላክ ነውና፡፡ ለሚያወርሰን ተስፋ መንፈሱን መያዣ አድርጎ ሰጥቶናል፡፡ ኤፌ. ፩÷፲፬፡፡

## ማጠቃለያ

እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሰጠው ተስፋ ተፈጸመ፡፡ እርሱ ስለ ተስፋ ቃሉ የማይዘገይ ተስፋ ያደረጉትን የማያሳፍር የታመነ አምላክ ነው፡፡ ሰው እግዚአብሔርን ተስፋ ቢያደርግ ያተርፋል፤ ተስፋውም በልብ ደስታን ይጨምራልና፡፡

## ተግባር

መምህሩ የሁለቱን ኪዳናት ተስፋ ወጣቶች እንዲያነጻጽሩ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# በኢያሱ መሪነት የተደረጉ ጦርነቶች

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** እግዚአብሔርን የያዙ ሰልፈኞች ድል እንደሚጎናፀፉ ለወጣቶች ማሳወቅ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** “እግዚአብሔር ከኢያሱ ጋር ነበር፤ ዝናውም በምድር ሁሉ ላይ ወጣ፡፡” ኢያሱ. ፮÷፳፯

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ኢያሱ. ፯-፳፬

## መግቢያ

ኢያሱ በግብጽ የተወለደ እስራኤላዊ ነው፡፡ ከግብጽ ወደ ከነዓን በተደረገው ጉዞ ላይ የሙሴ ዋና ረዳት ነበረ፡፡ ሙሴ ባረፈ ጊዜ የእስራኤል አዲሱ መሪ በመሆን አዲሱን ትውልድ ወደ ከነዓን መራ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

ኢያሱ በነገር ሁሉ እግዚአብሔር አብሮት የነበረ፤ ብዙ ሰልፎችን በእግዚአብሔር ስም እና ግርማ ያሸነፈ የተሳካለት ዝነኛ መስፍን ነበረ፡፡ ሙሴ በነበረበት ዘመን ከአማሌቅ ጋር በተደረገው ጦርነት የጦር መሪ ነበር፡፡ በጸሎትና በትጋት አማሌቅን አንበረከከ፡፡ ዘጸ. ፲፯÷፰-፲፩፡፡

ኢያሱ ከሙሴ ሞት በኋላ አዲሱን ትውልድ የመራ አዲስ መሪ ነው፡፡ በተፈተነ እምነቱ፣ በረጅም ጊዜ የማስተዳደር ልምድና በሀገር ጀኔራልነቱ ብዙ ምርኮ አብዝቷል፡፡ በእግዚአብሔር ያለውን እምነት በጽንዓት ጠብቆና ትእዛዛቱን አክብሮ ሕዝቡን በቅንነት መርቷል፤ ከነዓንን አውርሷል፤ ርስትን አከፋፍሏል፡፡

ኢያሱ ከእስራኤል ዋና ዋና ጠላቶች ጋር ተዋግቷል፡፡ እነዚህ የእስራኤል ታላላቅ ጠላቶች ኢያቡሳውያን፣ ፌርዛውያን፣ አሞራውያን፣ ሞአባውያን፣ አሞናውያንና ኤናቃውያን ናቸው፡፡ ኢያ. ፱፡፡ ኢያሱን በብርታቱ፣ በእምነቱና በታማኝነቱ ምክንያት በሁሉም ሰልፎች እግዚአብሔር ድል አጎናጽፎታል፡፡ በርስታቸው ላይ የሠፈሩትን የባዕድ ጭፍሮች አባሯል፡፡ በከነዓን ዙሪያ የነበሩ ኔፍሊሞችን በመዋጋት ግዛቱን አስፍቷል፡፡ ዕብ. ፲፩÷፴፣ ኢያ. ፮÷፲፫-፲፮፡፡

ኢያሱ ለጦርነት ከመውጣቱ በፊት እግዚአብሔርን፤ “ለታላቁ ስምህ የምታደርገው ምንድን ነው?” በማለት ይጠይቃል፡፡ ኢያ.፯÷፱፡፡ ሰልፉ የእግዚአብሔር ከሆነ በኋላ ኢያሱ የድል ምስጋና ማቅረብ ይጠበቅበት ነበር፡፡

ኢያሱ በገባዖን ፀሐይ አቁሞ በሰልፍ ድል አድርጎ አምስቱን ነገሥታት ማርኮ ገደለ፡፡ የእስራኤልንም ሕዝብ ፍርሃት አራቀ፡፡ ኢያ. ፲÷፳፪-፳፯፡፡ ኢያሱ የኤናቅን ልጆት ገደለ፡፡ እግዚአብሔር ለሙሴ እንደነገረው ሁሉ ኢያሱ ምድሪቱን ሁሉ ያዘ፡፡ ለእስራኤል እንደ ክፍላቸውና እንደነገዳቸው ርስት አድርጎ ምድሪቱን ሰጣቸው፡፡ ምድሪቱም ከሰልፍ ዐረፈች፡፡ ሕዝቡ ከድሉ ባለቤት ጋር ቃል

www.zeorthodox.org

ኪዳን አደረጉ፡፡ ኢያሱ. ፲፩÷፳፫፡፡

## ማጠቃለያ

ኢያሱ በእግዚአብሔር ኃይል በከነዓንና በዙሪያዋ የተሰለፉ የእስራኤልን ጠላቶች ድል አደረገ፡፡ ለሕዝቡ ርስትን አከፋፈለ፡፡ በኢያሱ ዘመን ምድሪቱ ከሰልፍ ዐረፈች፤ እስራኤል ጠላቶቻቸውን በታላቅ ስሙ አስጨንቀው እግዚአብሔርን እያመለኩ ኖሩ፡፡

## ተግባር

➔ *መምህሩ ኢያሱ በሰልፍ እንዴት ድልን ተጎናፀፈ? በሚል ርእስ ወጣቶችን ያወያያቸው፡፡*

www.zeorthodox.org

# ኢያሱ ለሕዝቡ ርስት አከፋፈለ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያስቀመጠውንና ዘላለማዊ ርስት የሆነውን በረከት ወጣቶች ተስፋ እንዲያደርጉ መምከር፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** "ምድሪቱን ለእስራኤል ርስት አድርገህ አከፋፍላቸው፡፡" ኢያሱ. ፲፫÷፯

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ኢያሱ. ፲፫÷፯-፴፫

## መግቢያ

እስራኤላውያን ምድሪቱን ከወረሱ በኋላ በእግዚአብሔር ትእዛዝ ርስታቸውን በኢያሱ አማካኝነት ተከፋፈሉ፡፡ ክፍፍሉ የሕዝባቸውን ቁጥር መሠረት ያደረገ ነበር፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

ኢያሱ ጦርነቱን ከፈጸመ በኋላ እግዚአብሔር ርስት እንዲያከፋፍል አዘዘው፡፡ ኢያሱም ለዐሥራ አንድ ነገደ እስራኤል ርስትን አካፈለ፡፡ ለአንድ ነገድ ማለትም ለሌዊ ካህን ስለሆነ እግዚአብሔር ርስቱ እንደሆነ ተገለጠ፡፡ ኢያሱ ፲፫÷፴፫፡፡ የርስቱ አከፋፈል ሁለት ዓይነት ገጽታ ነበረው፡፡

፩ኛ. ለእያንዳንዱ ነገድ የተሰጠው የመሬት መጠን ከነገዱ ሕዝብ ብዛት ጋር ተመጣጣኝ ነበር፡፡

፪ኛ. ለየነገዱ የተሰጠው መሬት የታደለው በዕጣ ውሳኔ ነበር፡፡ ዘኍ. ፳፮÷፶፪

ኢያሱ ርስት ያከፋፈለው ቀድሞ ከሙሴ እንደሰማውና በእግዚአብሔር እንደታዘዘው ነው፡፡ የሮቤል፣ የጋድና የምናሴ ወገን በራሳቸው ምርጫ ከከነዓን ውጪ በዮርዳኖስ ወንዝ ምሥራቃዊ ክፍል ሰፈሩ፡፡

ይሁዳና ስምዖን በደቡብ፤ ብንያም፣ ዳን፣ ኤፍሬምና የምናሴ ግማሹ ነገድ በከነዓን መካከል፤ ይሳኮር፣ ዛብሎን፣ ንፍታሌምና አሴር በሰሜን ሰፈሩ፡፡ ነገደ ሌዊ ርስት ባይካፈልም ከሁሉም ወንድሞቹ ዐሥራት ያስወጣ ዘንድ ሥርዓት ሆነ፡፡ ዕብ. ፯÷፰-፲፬፡፡ ኢያሱ ርስትን ካከፋፈለ በኋላ ሕዝቡ እግዚአብሔርን በማምለክ ጸንቶ እንዲኖር መከረ፡፡ በእርሱ ዘመን ሕዝቡ ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ግንኙነት መልካም ነበር፡፡

www.zeorthodox.org

እስራኤላውያን ርስታቸውን እያለሙ፣ ጠላትን በእግዚአብሔር ኃይል ድል እያደረጉ ርስታቸው እየሰፋ፣ ለሌዊ ዐሥራት

እያወጡና ፋሲካን እያከበሩ በጥንካሬ የኖሩት በኢያሱ ዘመን ነው፡፡

## ማጠቃለያ

የእስራኤል ነገዶች ከነዓንን ሲወርሱ እንደ ሁኔታቸውና እንደሕዝባቸው ብዛት በምርጫም በዕጣም ርስታቸውን ተከፋፈሉ፡፡ ሁሉም ለነገደ ሌዊ ዐሥራት ያወጡ ነበር፡፡ ለእኛ ግን ዘላለማዊ ርስት (ሰማያዊ ርስት) ይጠብቀናል፡፡

## ተግባር

መምህሩ የእስራኤልን ርስት አብነት በማድረግ ስለ ሰማያዊው ዘላለማዊ ርስት ይንገራቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ክፉ ልማድ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ከመጥፎ ልምዶች እንዲርቁ መምከር፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** “የወይናችንን ቦታ የሚያጠፉትን ጥቃቅኑን ቀበሮዎች አጥምዳችሁ ያዙልን፡፡” መኃ. ፪÷፲፭

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ምሳሌ. ፳፩÷፳፩ እና ፩ጴጥ. ፬÷፫-፬

## መግቢያ

- መጥፎ ልማድ የሚባሉትን ለጓደኞቻችሁ ንገሩ፡፡
- ሰው ከመጥፎ ልምድ /ክፉ ልማድ/ እንዴት መራቅ ይችላል?
- መጥፎ ልምድ በሰው ላይ የሚያደርሰው ጉዳት ምንድን ነው?

## የሳምንቱ ትምህርት

መጥፎ ልምድ ክፉ ነገርን የሚያበረታታ፣ በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአት የሆነውን የሚደግፍ፣ መጥፎ ሰብእና የሚፈጥር፣ ከቅድስና የሚያርቅና መልካም ነገር እየመሰለ ወደ ሞት የሚመራ መንገድ ነው፡፡ ክፉ ልምድ መጥፎ ዜጎችን ይፈጥራል፡፡ ክፉ ልማድ ያለው ማኅበረሰብ የሃገርን መልካም ገጽታ ያበላሻል፡፡

## የክፉ ልማድ ምንጭ ምንድን ነው?

- ያልተስተካከለ ማኅበረሰብ /በባዕድ አምልኮ፣ በክፋት፣ በጎጂ ባህል፣ በወንጀል፣ በሕገ ወጥነት ወዘተ የተጠመደ/
- ያልተፈተነ ባህል
- ከኃጢአት ጋር የተስማማ ቤተሰብ
- የእውቀት ማነስ
- ከእግዚአብሔር ቃል የራቀ ሕይወት
- ለመስተካከል ያልቆረጠ ሰብእና

www.zeorthodox.org

## ክፉ ልማድ የሚያስከትለው ጉዳት

- ከእግዚአብሔር ጽድቅ ይለያል

- ክፉትና ርኩሰትን እንደጽድቅ የሚቆጥር ትውልድ ይፈጥራል፡፡
- ለንስሐ የሚገባ ፍሬ እንዳናፈራ ይከለክላል፡፡
- መጥፎ ሰብእናን እንድናዳብር ያደርጋል፡፡
- የሃገርና፣ የትውልድን መልካም ገጽታ ያበላሻል፡፡

## ከክፉ ልማድ እንዴት እንላቀቅ፡-

- መጥፎ የሆነውን ልምድ በመለየት
- ሁሉን ፈትኖ መልካሙን በመያዝ
- የእግዚአብሔርን ቃል ዘወትር በመስማት፣ትእዛዛቱን አክብሮ በመገኘት
- ንስሐ ለመግባት በመወሰንና ውሳኔ በተግባር በመግለጽ
- መጥፎ ልምድ ከሚያወርሱን ሁኔታዎችና ሰዎች ሁሉ መራቅ

## ማጠቃለያ

ክፉ ልማድ መጥፎ ሰብእና ያላብሳል፤ ንስሐ ከመግባት ያዘገያል፡፡ ክፉ ልማድ ከዘላለማዊ ሕይወት ለይቶ ወደ ሞት መንገድ የሚመራ መጥፎ እና ተደጋጋሚ ስሕተትን ስለሚያጠቃልል በቆራጥነት ከዚህ ክፉት ለመለየት መወሰን አለብን፡፡

## ተግባር

➔ መምህሩ ወጣቶች መጥፎ ልምድን ከሚያወርሱ ሁኔታዎች እንዲርቁ ይምከራቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ስንፍና

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች በሰነፎች መንገድ እንዳይሄዱ መምከር፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** "የምታደርጉትን ሁሉ በትጋት አድርጉት፡፡" ቆላ. ፫÷፳፫

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** መዝ. ፲፫÷፩ እና ፪ተሰ. ፫÷፯-፲፫

## መግቢያ

ስንፍና ሓላፊነትን አለመወጣት፣ የሚጠበቅብንን አለማድረግና ጊዜን በከንቱ ማሳለፍን ያጠቃልላል፡፡ ስንፍና ለኃጢአት ያጋልጣል፤ ከታሰበልን አምላካዊ ዓላማ በታች እንድንኖር ያደርጋል፡፡ ስንፍና ለድህነተ ያጋልጣል፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

ስንፍና በራሱ ኃጢአት ነው፡፡ ለትልልቅ ኃጢአቶች ያጋልጣል፡፡ ሥራ የፈታ አእምሮ የሰይጣን ተንኮል ማስፈጸሚያ ይሆናል፡፡ ስንፍና ራስን ለዲያብሎስ አሠራር አሳልፎ መስጫ መንገድ ነው፡፡

አእምሮው በስንፍና የተያዘ ይከዳል፤ ኃጢአትን እንደ ውኃ ይጨልጣል፡፡ ስንፍና እግዚአብሔርን ያስከዳል፡፡ መዝ. ፲፫÷፩፡፡

በአቅም አለመሥራት፣ ሓላፊነትን አለመወጣት፣ ጊዜን በአግባቡ አለመጠቀም፣ እንቅልፍ ማብዛት፣ በነገሮች ቸልተኛ መሆንና የሚጠበቅብንን ያህል አለመኖር ስንፍና ነው፡፡ ሰው በአቅሙ ሊሠራ ይገባዋል፤ ሥራ የማይወድ ግን አይብላ ተብሏል፡፡ ፩ተሰ. ፫÷፲፡፡ ጊዜን በአግባቡ መጠቀም ባለመቻል እንቅልፍ ማብዛት ከስንፍና የመነጨ ሲሆን ውጤቱ የተበጫጨቀ ልብስ መልበስ ነው፡፡ ምሳሌ ፳፫÷፳፩፡፡ እግዚአብሔር ፍጥረታትን በቀናትና በሰዓታት ከፋፍሎ መፍጠሩ ጊዜን በአግባቡ እንድንጠቀም ለማስተማር ነበር፡፡

ሰነፍን የወለደ ኃዘኑ ይበዛል፡፡ ምሳ. ፲፯÷፳፩፡፡ ስንፍናን ገንዘቡ ያደረገ ፍጻሜውን ያበላሻል፡፡ ስንፍና ከእግዚአብሔር ልጆች ሊርቅ ያስፈልጋል፡፡ ክርስቲያኖች የሚያደርጉትን ሁሉ ለጌታ እንደሚያደርጉ በትጋት ያደርጋሉ፤ መልካም ለመሥራት አይታክቱም፡፡

www.zeorthodox.org

ስንፍና የሕይወት ስኬትና የአገር እድገት እንቅፋት ነው፡፡ የሰነፎች ሥራ ወሬ ነው፡፡ ቁጭ ብለው የሚሠሩትን ማማት ተግባራቸው ያደረጉ ሳይሠሩ የሚበሉ ሰነፎች በምድራችን በዝተዋል፡፡ ስንፍና ለበጎ ነገር ሁሉ አለመትጋትን ያመለክታል፡፡

ስንፍና ፍሬ ቢስ ያደርጋል፡፡ እግዚአብሔር ካሰበልን ዓላማ ያጎድለናል፡፡ ስንፍና ከእውቀት ማነስ፣ ተስፋ ከመቁረጥ፣ ሥራ ከመናቅ፣ በሌሎች ትክሻ ከመደገፍ እና ከቸልተኝነት (ቀጠሮ ከማብዛት) ይመነጫል፡፡

## ማጠቃለያ

ስንፍና ሕይወት በስኬት እንዳታጌጥ ይከለክላል፡፡ ለኃጢአት ያጋልጣል፡፡ ሰንፈው ከሚያሰንፉ ዋዘኞች ተጠበቁ፡፡

## ተግባር

- *መምህሩ ወጣቶች ስንፍናን ከሚያበረታቱ ሁኔታዎች ትጋትን ገንዘብ እንዲያደርጉ ርቀው ይምከራቸው፡፡*

www.zeorthodox.org

# ስደት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች የስደትን መንፈሳዊ ትርጉም እንዲያውቁ ማድረግ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** "በእውነትም በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ፡፡" ቆላ. ፫፥፳፫

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ዮሐ. ፫፥፩፱-፳፣ ማቴ. ፭፥፲-፲፩ እና ሐዋ. ፭፥፵፩

## መግቢያ

ስደት ከቦታ ወደ ቦታ በመገፋት የሚደረግ ፍልሰት ነው፡፡ ለክርስቶስ የተቆጠሩ፤ ለእግዚአብሔር እውነት የቀኑ ሰዎች ተሰደዋል፤ መከራን ተቀብለዋል፤ የበግና የፍየል ሌጦ ለብሰው በምድረ በዳና በበረሐ ተንከራተዋል፡፡ ዕብ. ፲፩፥፴፯፡፡ ስደት ከወገንና ከጥቅም መለየትን፣ ከአገር መባረርን፣ ከምቾት ሰገነት መነሣትንና ለታመነው ፈጣሪ ነፍስን አደራ ሰጥቶ በመከራ መጽናትን ያጠቃልላል፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ነቢያት ተሰደዋል፡፡ በሐዲስ ኪዳንም አምላካዊውን እውነት የተሸከሙ ቅዱሳን ተሰደዋል፡፡ ዓለም ለእግዚአብሔር ዓላማ ራሷን ማመቻቸት ስላልቻለች ለክብሩ የቀኑትን ታሳድዳለች፡፡ ዲያብሎስ የዘር ፍሬ ያለባቸውን (ከሴቲቱ ዘር የቀሩትን) ሊያሳድዱ ሠራዊቱን ከቶ ከወጣ ዘመናት አልፈዋል፡፡

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተራራው ስብከት "ስለ ጽድቅ የሚሰደዱ ብፁዓን ናቸው፡፡ መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና፡፡ ሲነቅፉአችሁና ሲያሳድዱአችሁ በእኔም ምክንያት ክፉውን ሁሉ በውሸት ሲናገሩባችሁ ብፁዓን ናችሁ፤ ዋጋችሁ በሰማያት ታላቅ ነውና፡፡" በማለት አስተምሯል፡፡ ማቴ. ፭፥፲-፲፪፡፡

ስለ ክርስቶስ ለሚሰደዱት ሽልማታቸው መንግሥተ ሰማያት ናት፡፡ ስለ ክርስቶስ የሚነቀፉት ዋጋቸው ታላቅ ነው፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ተሰዷል፡፡ ማቴ. ፪፥፲፭፡፡ በመሰደዱ የቅዱሳንን ስደት ባርኳል፡፡ ለእርሱ ያልራራች ዓለም ብታሳድደን አይክፋን፤ አብነታችን እርሱ ስደታችንን ለበረከት፤ መከራችንንም ለክብር ሊያደርገው የታመነ ነውና፡፡ በእውነት ክርስቶስን እየመሰሉ ለሚኖሩ ሁሉ ስደት ቃል ኪዳን ነው፡፡

ሐዋርያት በገዛ ወገኖቻቸው ተሰደዋል፡ ሐዋ. ፭፥፵፩፡፡ ክርስቲያኖች ይሰደዳሉ፡፡ ነገር ግን ስለሚያሳድዱን መጸለይ ተገቢ

www.zeorthodox.org

ነው፡፡ ሮሜ. ፲፪÷፲፬፡፡ በክርስትናችን ምክንያት በሚሆኑት መከራዎች ደስተኞች መሆን አለብን፡፡ ፩ጴጥ. ፬÷፲፪-፲፮፡፡ ስደት የእውነተኛ እምነት መፈተኛና የእውነተኛ አማኝ በክብር መገለጫ ነው፡፡ ፪ተሰ. ፩÷፬፡፡ በክርስትና ታሪክ ከ54 ዓ.ም - 313 ዓ.ም ድረስ የስደት ዘመን በመሆኑ ዘመነ ስማዕታት ይባላል፡፡ በእነዚህ ዓመታት ክርስቲያኖች ከመንግሥት ሥራ እየተባረሩ፣ ሮማዊ ዜግነት እየተቀሙ፣ ጥቅማቸውንና መብታቸውን እየተነፈጉ፣ለስደት እየተዳረጉ በብዙ መከራ ተጨንቀዋል፡፡ የእነርሱ በመከራ መጽናት ለክርስትናው እድገትን አምጥቷል፡፡

## ማጠቃለያ

ስደት ከወገን፣ ከጥቅምና ከምቾት መለየት ከአገርም መሰደድ (መገፋት) ነው፡፡ ለመልካም ነገር ሲባል የሚደረግ ስደት በክርስቶስ የተባረከ የክርስትና ኑሮ ነው፡፡ ክርስቲያኖች ከሰፈር ውጪ ይኖራሉ፤ ሰማያዊት ኢየሩሳሌምን ይወርሳሉ፡፡ በእውነት ክርስቶስን መስለው ለሚኖሩ ስደት ቃል ኪዳን ነው፡፡ የታመነው ጌታ ስደታችንን ለበረከት፤ መከራችንን ለክብር አድርጎ ሕይወታችንን ሊያስጌጠው የታመነ ነው፡፡

## ተግባር

- ➔ መምህሩ ክርስቲያኖች ለምን ይሰደዳሉ? በሚል ርእስ ያወያያቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# የንግግር ችሎታን ማዳበር

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች የንግግር ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ማድረግ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** "ንግግራችሁ በጨው እንደተቀመመ በጥበብና በጸጋ ይሁን" ቆላ. ፬÷፮

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ፩ሳሙ. ፪÷፳፮ እና ሉቃ. ፪÷፶፪

## መግቢያ

ንግግር የማንነት መገለጫ፣ የሰብእና አስረጅ፣ የሐሳብ ማንፀባረቂያና የግንኙነት ዋስትና ነው፡፡ ንግግር የልባችንን አሳብ ለሰዎች የምናስረዳበት በከንፈር የሚፈስ የልብ ፍሬ ነው፡፡ የንግግር ችሎታን ለማዳበር ማንበብና መጸለይ ያስፈልጋል፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

### የንግግር ችሎታን የማዳበር ጥቅም

- የፈለግነውን አሳብ በሚገባ እና በተሟላ ሁኔታ ለመግለጽ
- ሰዎች የሚረዱትን መልእክት ለማስተላለፍ
- ሌሎችን ወደ ክፉ ነገር የማይመራ፣ የሚያሳምን ተጽእኖ ፈጣሪ ንግግር ለመናገር
- ሰዎችን የማይጎዳና እኛንም የማያስገምት ንግግር ለመናገር፡፡
- ሰዎችን ለመልካም ነገር ለማነሣሣት

## የንግግር ችሎታን እንዴት ማዳበር ይቻላል?

**1. ያለንን ጸጋ በማወቅ፡-** ***ያለንን ሳናውቅ*** የሌለንን ልንሞላ አንችልም፡፡ ስለዚህ የተሰጠንን ጸጋ ማወቅና ማሳደግ ይኖርብናል፡፡

www.zeorthodox.org

**2. በማንበብ፡-** ***ንባብ ዓለም የደረስችበትን*** ከፍታ የምናውቅበት የመረጃ ምንጭ ነው፡፡ አንባቢዎች ስንሆን ጥሩ ተናጋሪዎች እንሆናለን፡፡ የሚያነብ ሰው ተወዳጅ ቃላትን ስለሚጠቀም ተደማጭ ነው፡፡ አንደበታችን የሚናገረው ከልባችን መዝገብ ከአእምሮአችንም ሰሌዳ ያገኘውን ነው፡፡ ስለዚህ የእውቀት አድማሳችንን ማስፋት አለብን፡፡ የንግግር ችሎታ የሚያዳብሩ ጽሑፎችን፣ ጥበብን የሚጨምሩ፣ መረጃ የሚሰጡ የመረጃ ምንጮችን መጠቀም መጻሕፍትን ማንበብ አለብን፡፡

**3. በማዳመጥ፡- ጥሩ የሚያዳምጡ ጥሩ ይናገራሉ፡፡** በእርጋታ ማዳመጥ የተሻለ ለመናገር ይጠቅማል፡፡ አምላክ በተፈጥሮ ሁለት ጆሮ አንድ አፍ የቸረን ብዙ እንድናዳምጥ ጥቂትም እንድንናገር ነው፡፡ ለሰዎች ከመናገራችን በፊት በሚገባ እናድምጣቸው፡፡ የሚደመጡ የመረጃ ምንጮች ጋር ግንኙነታችን ሊጠነክር ይገባል፡፡

**4. በመጸለይ፡- ጸሎት በአድማጮች ዘንድ** ተቀባይነት ያለው ማሳመን የምንችልበትን የንግግር ችሎታና ሐሳባችንን በሚገባ መግለጽ የሚያስችለን አንደበት እንዲኖረን ያደርጋል፡፡ የመደመጥ ሞገስ የሚሰጠው በጸሎት ነው፡፡ ንግግር የጥበብ አካልና አንደበት በመሆኑ ሳይነቅፍ ጥበብን በልግስና ከሚሰጠው አምላክ መለመን ተገቢ ነው፡፡ በማንበብና በማዳመጥ በውሳጣችን ያከማቸነው ዕውቀት በጥበብ ተቀምሞ ለሰው የሚደርሰው በጸሎት ሲታገዝ ነው፡፡

**5. ለማን? ምን? መናገር እንዳለብን በማወቅ፡-** የንግግር ችሎታ ያለው ሰው ለማን ምን መናገር እንዳለበት ስለሚያውቅ መርጦ ይናገራል፡፡ "አፍ ሲከፈት ጭንቅላት ይታያል" እንደሚባለው ንግግራችን እንዳያስገምተን በማስተዋል በተመረጡ እና አሻሚ ትርጉም በማይሰጡ ቃላት ሐሳባችንን መግለጽ አለብን፡፡

## ማጠቃለያ

ንግግር የማንነታችን መገለጫ የሐሳባችን ማብራሪያ ነው፡፡ ሰዎች በንግግራችን ይመዝኑናል፡፡ ስለዚህ ራሳችንን የመግለጥ ባህልን ማዳበር፤ ፍርሃትን ማራቅ፤ በትክክለኛ መረጃና ዕውቀት ላይ በተመሠረተ የተረጋጋ መንፈስ በጨው እንደ ተቀመመ በጥበብ የሆነ ንግግር ማድረግ አለብን፡፡

## ተግባር

➔ መምህሩ ወጣቶች የንግግር ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ይምከራቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# የሐዲስ ኪዳን መግቢያ ፩

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ስለ ሐዲስ ኪዳን ለወጣቶች ማስገንዘብ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** "ከእስራኤል ቤት ጋር አዲስ ኪዳን የምገባበት ወራት ይመጣል" ዕብ. ፰÷፰

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ኤር. ፴፩÷፴፩ እና ዕብ. ፰÷፰-፲፫

## መግቢያ

- ሐዲስ ኪዳን እንዴት ተሰጠ?
- በሁለቱ ኪዳናት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?
- ሐዲስ ኪዳን በውስጡ ስንት መጻሕፍትን አካቷል?

## የሳምንቱ ትምህርት

### 1. ትርጉም፡-

ሐዲስ ኪዳን ማለት አዲስ ውል፤ አዲስ ቃል ኪዳን፤ አዲስ ስምምነት ማለት ነው፡፡ ቃል ኪዳኑ የተደረገው በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል ነው፡፡ የቃል ኪዳኑ ሰጪ እግዚአብሔር ሲሆን የቃል ኪዳኑ ተቀባዮች በክርስቶስ አምነው በስመ ሥላሴ የተጠመቁ ናቸው፡፡ የአዲሱ ቃል ኪዳን ተስፋ የዘላለም ሕይወት ነው፡፡ የአዲሱ ቃል ኪዳን ምልክት ጥምቀት ሲሆን የተስፋው ማኅተም ቅዱስ ቁርባን ነው፡፡

### 2. የሐዲስ ኪዳን አመሠራረት፡-

እግዚአብሔር በኤርምያስ አድሮ "ከሕዝቤ ጋር አዲስ ኪዳን የምገባበት ወራት ይመጣል" እንዳለ አዲሱ ኪዳን ክርስቶስ በሥጋ በተገለጠባቸው ወራት በደሙ ተመሠረተ፡፡ ብሉይ ኪዳን በክርስቶስ ለተደረገው የማዳን ሥራ አመልካች ጥላ ነው፡፡ ኪዳኑ የጸናው (የተመረቀው) በእንስሳት ደም ሰለሆነ ኀሊናን አይቀድስም፡፡ በዘላለም መንፈስ አንድ ጊዜ ፈስሶ ዓለምን የቀደሰው የክርስቶስ ደም ግን ኀሊናን ያነፃል፡፡ ዕብ. ፱÷፲-፳፪፡፡ **አዲሱ ኪዳን የተመረቀው በኢየሱስ ክርስቶስ** የከበረ ደም ነውና ኪዳኑ አስተማማኝ ነው፡፡

www.zeorthodox.org

አዲስ ኪዳን የመነጨው ከእግዚአብሔር የማይነጥፍ ጸጋ ነው፡፡ እግዚአብሔር በአዲሱ ኪዳን በልጁ ሞት ከጠላቶቹ ጋር ታረቀ፡፡ ሮሜ. ፭÷፯-፲፡፡ የማይገባንን ኃጢአተኞቹን የራሱ ሕዝብ አደረገን፡፡ "ሕጌን በልባቸው አኖራለሁ፤ በልባቸውም እጽፈዋለሁ፤ እኔም አምላክ እሆንላቸዋለሁ፤ እነርሱም ሕዝብ ይሆኑኛል፡፡" ያለው አምላካዊ የጸና ቃል ተፈጸመ፡፡ ዕብ. ፰÷፲-፲፫፡፡ ሰዎች የዚህ ኪዳን በረከትና ሕይወት ተካፋዮች ለመሆን ለእግዚአብሔር ጸጋ በእምነትና በመታዘዝ ምላሽ መስጠት አለባቸው፡፡ ገላ. ፫÷፲፬፣ ፩ጴጥ. ፩÷፪፡፡

## 3. የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት:-

አዲሱን ኪዳን የመዘገቡ መጻሕፍት ሠላሳ አምስት ናቸው፡፡

## 4. የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ይዘት:-

**የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት አጠቃላይ ይዘት:-**

- የአምላክን በሥጋ መገለጥና በሥጋ ለባሾች መካከል እየተመላለሰ የጽድቅን ሥርዓት ማስተማር፤
- በመሲሁ በክርስቶስ መገለጥ የነቢያት ትንቢት ፍጻሜና የብሉይ ኪዳን ጥላዎችን አካል ማግኘት፤
- ሰዎች የሚሄዱበት ሕያው መንገድና በእርሱ ያመኑት የሚወርሱትን ዓለም
- የአዲሱ ኪዳን ተስፋና በዚህ ኪዳን ሰዎች የሚቆሙበትን ኃይል
- ሰዎች ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የሚገቡበትን ሥርዓት ያጠቃልላል፡፡

## ማጠቃለያ

ሐዲስ ኪዳን በክርስቶስ መገለጥ እውን ሆነ፡፡ በደሙ ተመረቀ፤ በእግዚአብሔር ጸጋ ለመደገፍ የሚፈልጉትን አቀፈ፡፡ ሐዲስ ኪዳን ለአንድ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ያመኑትን ሕዝብና አሕዛብ ሁሉ ያጠቃልላል፡፡ ሰዎች የአዲሱ ቃል ኪዳን አካል ለመሆን በክርስቶስ ማመንና በስመ ሥላሴ መጠመቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡

## ተግባር

- መምህሩ ወጣቶች የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን ዝርዝር ጠይቀው ጽፈው እንዲመጡ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# የሐዲስ ኪዳን መግቢያ ፩

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን ጭብጥ ወጣቶች እንዲገነዘቡ ማድረግ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** "አዲስ በማለቱ ፊተኛውን አስረጅቶአል" ዕብ. ፰÷፲፫

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ማቴ. ፳፮÷፳፮

## መግቢያ

ሐዲስ ኪዳን በእምነት ጽድቅን የምንቀበልበት፣ በመታዘዝ በሥራ ጽድቅን የምንፈጽምበትና (የጽድቅን ፍሬ የምናፈራበት)፣ መንግሥተ ሰማያትን የምንወርስበት ቃል ኪዳን ነው፡፡ ኤፌ. ፩÷፫-፲፣ ገላ. ፫÷፳፱፡፡ አዲስ ኪዳን በእንስሳት ደም ሳይሆን በአምላካችን በኢየሱስ ክርስቶስ ንጹሕ ደም የተመረቀ አስተማማኝ ኪዳን ነው፡፡ ይህን እውነት የገለጡ ሠላሳ አምስት መጻሕፍት የአዲሱ ኪዳን መጻሕፍት ይባላሉ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

### 1. የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት አከፋፈል፡-

1.1. የወንጌል ክፍል፡- (የማቴዎስ፣ የማርቆስ፣ የሉቃስና የዮሐንስ ወንጌል)
1.2. የታሪክ ክፍል፡- (የሐዋርያት ሥራ)
1.3. የመልእክታት ክፍል፡- (ሃያ አንድ መልእክታትን በውስጡ ይዟል)
1.4. የራእይ መጽሐፍ፡- (የዮሐንስ ራእይ)
1.5. የሥርዓት መጻሕፍት፡- (ስምንት የሥርዓት መጻሕፍት ተካተውበታል)

### 2. የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ዳሰሳ ጥናት፡-

**2.1. ወንጌል**

www.zeorthodox.org

ወንጌል የሚለው ቃል "ኢቫንጌሌዎን" ከሚለው የግሪክ ቃል የተገኘ ሲሆን ‹‹ምስራች›› ማለት ነው፡፡ ወንጌል የመሲሁን የኢየሱስ ክርስቶስን መምጣት ያበሰረች፤ የማዳኑንም ዜና የምስራች ብላ ለትውልድ ያወጀች የእግዚአብሔር መንግሥት ሕገ መንግስት ናት፡፡ ወንጌል የክርስቶስ ኢየሱስ ትምህርትና ተአምራት መዝገብ ናት፡፡ ሦስቱ ወንጌላውያን ማቴዎስ፣ ማርቆስና ሉቃስ ስለ ክርስቶስ ፍጹም ሰው መሆን፣ በተአምራቱና ትምህርቱ ላይ የጋራ ትኩረት ስላደረጉ ተመሳሳይ ወንጌላውያን ይባላሉ፡፡ ሦስቱ

ወንጌላውያን ኃያሉ አምላክ በደካማ ሥጋ መገለጡን፣ ባዕለ ጠጋው በበረት መተኛቱን፣ የዓለም ባለቤት መጠጊያ ማጣቱን፣ በተውሶ ጀልባ መጓዙን፣ በተውሶ መቃብር መቀበሩን፣ በትሑት ሰብእና በሥጋ ለባሾች መካከል እየተመላለሰ የጽድቅን ሥርዓት ማስተማሩንና ብዙ ተአምራት ማድረጉን በሚቀራረብ አገላለጽ ጽፈዋል፡፡ ማቴዎስ በትውልድ ሐረጉ፤ ማርቆስ በጥምቀቱ፤ ሉቃስ በብስራቱ መጻፍ ጀምረዋል፡፡ በትንሣኤው ጽሑፋቸውን ደምድመዋል፡፡

የዮሐንስ ወንጌል በክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት ላይ ያተኮረ ወንጌል ነው፡፡ ሲጀምር ከቀዳማዊነቱ በመነሣት “ቀዳሚሁ ቃል” ብሎ ነው፡፡ ወንጌላዊው ዮሐንስ ክርስቶስ ስለራሱ የተናገራቸውን የባሕርይው መገለጫ የሆኑቱን ንግግሮች መዝግቧል፡፡ ሰባት የተመረጡ ተአምራትን ጽፏል፡፡ የወንጌሉም ዓላማ ሰዎች ክርስቶስን በማመን ሕይወት እንዲበዛላቸው እንደሆነ በግልጽ ተገልጧል፡፡ ዮሐ. ፳÷፴፩፡፡

### 2.2. የታሪክ መጽሐፍ

የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ምሥረታ፣ አደረጃጀት፣ ዕድገትና ጉዞ የመዘገበው ብቸኛው የታሪክ መጽሐፍ የሐዋርያት ሥራ ነው፡፡ የሐዋርያት ሥራ በሃያ ስምንት ምዕራፎች የተከፈለ መጽሐፍ ሲሆን የመጀመሪያዎቹን ምእመናን የአንድነት ኑሮ፣ የደቀ መዛሙርቱን ብርቱ አገልግሎት፣ የመንፈስ ቅዱስን ሥራና የጸጋ ስጦታዎቹን ፍሬ መዝግቧል፡፡

## ማጠቃለያ

የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት በአምስት ክፍሎች የተጠቃለሉ ሲሆን ሰዎች በአዲሱ ኪዳን እንዲቆሙ ይመክራሉ፡፡

## ተግባር

- መምህሩ ወጣቶች የአራቱን ወንጌላውያን የምዕራፍ ብዛት እና ይዘት እንዲያጠኑ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# የሐዲስ ኪዳን መግቢያ ፫

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን በዳሰሳ ጥናት ወጣቶች እንዲገነዘቡ ማድረግ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** "የተጠራህለትን . . . . የዘላለም ሕይወት ያዝ፡፡" ፩ጢሞ. ፮÷፲፪

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ፪ጢሞ. ፫÷፲፭

## መግቢያ

- የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ስንት ናቸው?
- የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት በስንት ይከፈላሉ?
- በሐዲስ ኪዳን ብቸኛው የታሪክ መጽሐፍ ማን ነው? በውስጡስ ምን ይዟል?
- ወንጌል ማለት ምን ማለት ነው? ስንት ወንጌላውያን አሉ?
- ወንጌል የማን ትምህርት ነው?
- የወንጌል ዓላማ ምንድን ነው?

## የሳምንቱ ትምህርት

### 2.3. መልእክታት፡-

በሐዲስ ኪዳን ውስጥ የሚገኙ መልእክታት ሃያ አንድ ናቸው፡፡ ዐሥራ አራቱ የቅዱስ ጳውሎስ፣ ሦስቱ የቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ፣ ሁለቱ የቅዱስ ጴጥሮስ፣ ቀሪዎቹ ሁለቱ የይሁዳና የያዕቆብ ናቸው፡፡ በሐዲስ ኪዳን ውስጥ ያሉት መልእክታት ክርስትና የሮምን ድንበር እንደተሻገረ ያሳያሉ፡፡ የመልእክታት መሠረት ብሉይ ኪዳንና ወንጌል (የክርስቶስ ትምህርት) ናቸው፡፡ የመልእክታት ዓላማ ሰዎች ኃጢአተኝነትን እና ዓለማዊ ምኞትን ሊያስክድ በተገለጠው የእግዚአብሔር ጸጋ ታግዘው ክርስቶስን በማመንና በመከተል ወደ እግዚአብሔር ጽድቅ እንዲደርሱ ማድረግ ነው፡፡

www.zeorthodox.org

የቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት ለአብያተ ክርስቲያናትና ለግለሰቦች በአድራሻ የተጻፈ ነው፡፡ የሌሎቹ አገልጋዮች መልእክት ደግሞ ዓለም አቀፋዊ ነው፡፡ የቅዱስ ዮሐንስ ሁለት መልእክታት ብቻ ግለሰቦችን ይመለከታሉ፡፡

## 2.4. ራእይ፡-

በሐዲስ ኪዳን ውስጥ የምናገኘው የ‹‹ዮሐንስ ራእይ›› ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የአባቱን የእግዚአብሔር አብን ምክር በመልአኩ በኩል በፍጥሞ ደሴት በግዞት ለነበረው ለዮሐንስ አቡቀለምሲስ የገለጠለት የራእይ መጽሐፍ ነው፡፡ የዮሐንስ ራእይ በሐዲስ ኪዳን ውስጥ ያለ ብቸኛው የትንቢት መጽሐፍ ነው፡፡ የዮሐንስ ራእይ የክርስቶስን መልክ፣ ግርማና ድል አድራጊነት ይገልጣል፡፡ የአማኞችንም ዘላለማዊት ርስት ዓለም ውበት በፊታችን ይስላል፡፡ የዮሐንስ ራእይ በሃያ ሁለት ምዕራፎች የተከፈለ የተስፋችን ገጽ ነው፡፡ የዮሐንስ ራእይ የቤተክርስቲያንን ስፍረ ዘመን፣ የሰማይን አምልኮ፣ የቅዱሳንን ቅኔ፣ የሰማዕታትን በበጉ ደም የተደረገ ድልና የአማኞችን ተስፋ መዝግቧል፡፡ (የዮሐንስ ራእይን ከምዕራፍ 1 እስከ ሃያ ሁለት ድረስ ያንብቡ)

## 2.5. የሥርዓት መጻሕፍት፡-

የሐዲስ ኪዳን የመጨረሻው ክፍል የሥርዓት መጻሕፍት ክፍል ነው፡፡ ይህ ክፍል ስምንት የሥርዓት መጻሕፍትን አካቷል፡፡ መጻሕፍቱም ዲድስቅልያ፣ አብጥሊስ፣ ሥርዓተ ጽዮን፣ ግጽው ሲኖድ፣ ኪዳን ቀዳማዊ፣ ኪዳን ካልዕ፣ መጽሐፈ ቀሌምንጦስና ትእዛዝ ናቸው፡፡

## ማጠቃለያ

የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት እግዚአብሔር በዘመን መጨረሻ በአንድ ልጁ የተናገረውን የፍጻሜ ቃል መዝግበዋል፤ ከትውልዶች ጀምሮ ከዘመን አስቀድሞ የተሰወረው የተገለጠባቸው የሕይወት ገጾች ናቸው፡፡

## ተግባር

- መምህሩ ወጣቶች ከሦስቱ ሳምንት ትምህርት ምን እንደተረዱ ይጠይቃቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# የሴት ክብር

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች የሴትን ክብር እንዲያውቁ ማድረግ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** “የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ ከሴት ተወለደ፡፡” ገላ. ፬÷፬

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ፩ጢሞ. ፪÷፲፫ እና ዘፍ. ፪÷፳፩-፳፫

## መግቢያ

ሴት ከአዳም ጎን የተፈጠረች ምቹ ረዳት ናት፡፡ ሴት የቤት ውበት፣ የወንድ ክብር፣ የባሏ ሞገስ (ዘውድ) ናት፡፡ “ሴትን ያገኘ በረከትን አገኘ” ተብሎ እንደተጻፈ በረከት ናት፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

እግዚአብሔር የምትመስለውንና የምትመቸውን ረዳት ለአዳም ፈጠረለት፡፡ አዳምም ባያት ጊዜ “አጥንቷ ከአጥንቴ ሥጋዋም ከሥጋዬ ናት፤ ከወንድም ተገኝታለችና ሴት ትባል፡፡” አለ፡፡ ዘፍ. ፪÷፳፫፡፡

ሴት ከወንድ ጎን ብትገኝም ከወንድ ጋር እኩል ሥልጣን የተቀበለች፤ በክብርም ከወንድ የማታንስ ሰው ናት፡፡ እግዚአብሔር ገዥነትን ለሰው ሰጠ፡፡ ሰው የሚለው የአዳምና የሔዋን የጋራ ስም ነው፡፡ ስለዚህ ሴትም ከመለኮታዊ ክብር ተካፋይ ናት፡፡

ሴት እኅት፣ እናትና ሚስት ናት፡፡ ሴት በመጽሐፍ ቅዱስ የባሏ ዘውድ፣ የፈጣሪ ስጦታ፣ የቤቷ ውበትና የልጆችዋ መምህርት ተብላለች፡፡ ምሳ ፲፱÷፲፬፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ መልካም ሴት ምስጋና እንደሚገባት ይናገራል፡፡ ምሳ. ፴፩÷፲-፴፩፡፡

ሴት የሰላም መሣሪያ ናት፡፡ የዳዊትን እጅ ከደም ያዳነችው አቢግያ በዳዊት ፊት የተመሰገነችው የሰላም መሣሪያ በመሆንዋ ነው፡፡ ፩ሳሙ. ፳፫÷፪-፴፩፡፡ በሴት ምክንያት የሚነሣ ጦርነትም አይበርድም፡፡ የያዕቆብ ልጆች በዲና ምክንያት ትልቅ ፀብ ገጥሟቸዋል፡፡ ዘፍ. ፴፬÷፩-፴፩፡፡ በብንያማውያን ላይ የታወጀው ጦርነት በአንዲት ሴት ምክንያት ነው፡፡ ሃያ ሁለት ሺሕ ሰዎችም በጦርነቱ ሞተዋል፡፡ መሳ. ፲፱÷፲፮-፳÷፵፰፡፡

www.zeorthodox.org

የእግዚአብሔር ልጅ በሥጋ ሲገለጥ ያለወንድ ዘር ከሴት ነው የተወለደው፡፡ ገላ. ፬÷፬፡፡ ሴት በመውለድ እንደምትድን ጳውሎስ ተናግሯል፡፡ ፩ጢሞ. ፪÷፲፭፡፡ በእግዚአብሔር መንግሥት በእምነታቸው የተመሠከረላቸው ታላላቅ ሴቶች አሉ፡፡ በብሉይ ኪዳን ሣራ፣ ትዕማር፣ ሩት፣ ረዓብና አቢግያ ተመስግነዋል፡፡ በሐዲስ ኪዳን ሶስና፣ ማርያም ባለሽቶዋ፣ ማርያም መግደላዊት፣ ፌበን፣ ጵርስቅላና የማርቆስ እናት ማርያም ተከብረዋል፡፡ በአዲስ ኪዳኗ ቤተ ክርስቲያን ሠላሳ ስድስት ሴቶች ቅዱሳን ነበሩ፡፡ በብሉይ ኪዳንም ሕልዳና፣ ዲቦራ፣ ሐና እና ማርያም የሚባሉ እንስት ነቢያት ነበሩ፡፡ ከሴቶች

መካከል የተለየችና የተመረጠች ድንግል ማርያም ደግሞ የክብራቸው ምክንያት ናት፡፡ በሔዋን የተዘጋው ከእርሷ በተወለደው ተከፍቷልና መርገማቸው ተሽሮአል፡፡

### የሴት ክብር በተፈጥሮ

- ማርገዝ መቻል ለሴት ብቻ የተሰጠ ጸጋ ነው፡፡
- ቤትን ማስተዳደር በሴት ብልሃት የሚመራ ነው፡፡
- የእናትነት ፍቅር የተለየ ችሮታ ነው፡፡ ይህ ፍቅር የሚገባቸው እናት ለሆኑ ብቻ ነው፡፡
- ያለ ሴት ቤት አይሞቅም፤ ኑሮ አይሠምርም፤ መሪ ጀግና አይሆንም፡፡
- የመፈቀር ሞገስ የመወደድና የመደመጥ ግርማ በሴት ይበረታል፡፡

## ማጠቃለያ

ተፈጥሮም፤ ሳይንስም፤ ፍልስፍናም፣ ጥበብም፤ ሃይማኖትም ለሴት ልዩ ቦታ አለው፡፡ ሴት ከኃያላን ጀርባ ያለች ጉልበት፤ ከውበት ጀርባ ያለች ውብ ጥበብ፤ ከአገልጋይ አባቶች ጀርባ ያለች ብርታት ናት፡፡ እግዚአብሔር ለሴት ብቻ የሰጠው ውበት፣ ብልሃት፣ ጥበብ እና ትጋት አለ፡፡

## ተግባር

☒ መምህሩ ወጣቶች የሴትን ክብር እንዴት እንደሚረዱ በመጠየቅ ያወያያቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ክርስቶስ ሰው የሆነበት ምስጢር

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** *ወጣቶች ስለ ነገረ ሥጋዌ እንዲያውቁ ማድረግ፡፡*

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *"የዲያብሎስን ሥራ እንዲያፈርስ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ፡፡" ፩ዮሐ. ፫÷፰*

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ዮሐ. ፫÷፲፰፣ ሮሜ. ፰÷፱፣ ዮሐ. ፩÷፲፬ እና ገላ. ፬÷፬

## መግቢያ

ክርስቶስ ኢየሱስ በማይደፈር ዓለም፤ ማንም በማይቀርበው ብርሃን፤ በሚያስፈራ ግርማ ከአባቱ ከአብ ጋር በባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስም ጋር ሲኖር ሳለ፤ ፍቅር ስቦት ወደ ጠባቧ መንደር በጠባብ ደረትና በአጭር ቁመት ተወስኖ በሥጋ ማርያም ተገለጠ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

### 1. ክርስቶስ ለምን ሰው ሆነ?

አምላክ ሰው የሆነበት ምስጢር ሰውን ሰው ለማድረግ ነው፡፡ ቅዱስ አትናቴዎስ "የእግዚአብሔር ልጅ የሰው ልጅ የሆነው የሰው ልጆችን የሕያው እግዚአብሔር ልጆች ለማድረግ ነው፡፡" እንዳለ፡፡

ክርስቶስ ኢየሱስ ከልዕልና ወደ ትሕትና የወረደበት፤ ከታላቁ ዙፋን ወርዶ የድንግል ማርያምን ማኅፀንና መስቀልን ዙፋን ያደረገበት ምስጢር አዳምን ወደ ክብሩ ዓለም ለመመለስ፣ የዲያብሎስን ሥራ ለማፍረስ፣ የሰውን ገዥነት ለመመለስ፣ የጽድቅን ሥርዓት ለሥጋ ለባሾች ለማስተማር፣ ሞትን በሞቱ ለመሻር፣ ሰውን የመለኮታዊ ክብር ተካፋይ ለማድረግ ለአዳም ቤዛና አርአያ ለመሆን ነው፡፡

### 2. ክርስቶስ እንዴት ሰው ሆነ?

www.zeorthodox.org

አምላክ ሰው የሆነው በተዋሕዶ ነው፡፡ ከድንግል ማርያም ፍጹም ሥጋና ነፍስን ነስቶ፤ የአብርሃምን ዘር ይዞ፤ ከዳዊት ዘርና ሥር ተወለደ፡፡ መለኮት የሥጋን ገንዘብ ገንዘቡ አደረገ፤ ሥጋም የመለኮትን ገንዘብ ገንዘቡ አደረገ፡፡ "ቃል ሥጋ ሆነ" በማለት ሐዋርያው የጻፈው ለዚህ ነው፡፡ ዮሐ. ፩÷፲፬፡፡

ክርስቶስን ሰው እንዲሆን ያስገደደው የለም፤ ፍቅር ነው ከዙፋኑ የሳበው፡፡ የሰውን ውርደት በክብር ለመለወጥ ነው የመጣው፡፡ ኃያሉ ወልድ ደካማ የሆነውን የሰውን ሥጋ የተዋሐደው ሥጋን የተቆራኘውን ሞት ለመቁረጥ ነው፡፡ ክርስቶስ ለጨለማው ዓለም ብርሃን፤ ለወደቁት ትንሣኤ፤ ለቅቡፃን ተስፋ፤ ለሞቱት ሕይወት፤ የተቅበዘበዙትን የሚያሳርፍ መልካም እረኛ፤ እውነትን ለሚፈልጉ እውነት፤ የተጠሙንት ዳግም የማያስጠማ ዘላለማዊ ርካታ የሆነ የሕይወት ውኃ፤ የተራቡትን ዳግም የማያስርብ ዘላለማዊ የሕይወት እንጀራ ሆኖ ተገለጠ፡፡

ክርስቶስ ሰው የሆነበት ምስጢር ‹‹ምስጢረ ተዋሕዶ›› ይባላል፡፡ ምስጢረ ተዋሕዶ (ነገረ ሥጋዌ) አምላክ ለምን? እና እንዴት? ሰው እንደሆነ ይገልጣል፡፡ ክርስቶስ ሰው የሆነበት ምስጢር፡-

- ዓለምን ለማዳን፤ ዮሐ. ፫÷፲፯
- የዲያብሎስን ሥራ ለመግለጥ፤ ፩ዮሐ. ፫÷፰
- የሚቃወመንን የሕግ ጽሕፈት በመስቀል ጠርቆ ከመንገዳችን ለማስወገድ፤ ቆላ. ፪÷፲፬
- የጥልን ግድግዳ አፍርሶ ሰላም ለመስጠት፤ ኤፌ. ፪÷፲፮፣ ቆላ. ፩÷፳
- ለሰው ቤዛ ለመሆን፤ ኤፌ. ፩÷፯
- የእግዚአብሔርን የምሕረት ዓመት ለመስበክና መንግሥቱን በምድር ለመመሥረት፤ ሉቃ. ፬÷፲፯-፳፩

## ማጠቃለያ

ክርስቶስ ሰው የሆነበት ምስጢር ሰውን ወደታሰበለት መልካም ፍጻሜ ለማድረስ ነው፡፡ በሞት የተቋረጠው የዘላለማዊ ሕይወት ጉዞ በክርስቶስ ሞት ደግሞ ቀጥሏል፡፡ አምላክ ሰው በመሆኑ የዲያብሎስ ሥራ ተገልጧል፣ ምክሩ ፈርሷል፤ አዳም ወደ ክብሩ ዓለም ተመልሷል፡፡

## ተግባር

- መምህሩ ወጣቶች ተጨማሪ የነገረ ሥጋዌ መጻሕፍትን እንዲያነቡ ይጋብዛቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ክፉ ቅናት

**የትምህርቱ ዓላማ:-** ወጣቶች ከክፉ ቅናት እንዲጠበቁ መምከር፡፡

**የሚጠና ጥቅስ:-** “ቅንዓት አጥንትን ያነቅዛል፡፡” ምሳ. ፲፬÷፴

**ተጨማሪ ምንባብ:-** ምሳሌ ፳፬÷፲፱ እና ዘፍ. ፬÷፱

## መግቢያ

ቅንዓት አንድን ነገር ለማድረግ ያለንን መነሣሣትና ቁርጠኝነት ያሳያል፡፡ ቅናት በጎና ክፉ ተብሎ በሁለት ይከፈላል፡፡ ሰው በበጎው ጸጋ መልካም ለማድረግ እንዲቀና ከክፉ ቅናት እንዲከለከል መጽሐፍ ቅዱስ ይመክራል፡፡ በክፉ የሚቀኑ በክፉ ይበድላሉ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

ክፉ ቅንዓት ክፉ ኃጢአት ያሠራል፡፡ ክፉ ቅናት አጥንትን ያነቅዛል፡፡ ክፉ ቅናት የሌሎችን የማጥፋት፣ የራስን ብቻ የማሳደግና የወገንን ጥቅም የመንካት መንፈስ ነው፡፡ በክፉ ቅናት በተያዙ ሰዎች ሰይጣን ይሠራል፡፡ ሰይጣን ክፉ ቅናት ያደረባቸውን ሰዎች ለወንጀልና ለትልልቅ ኃጢአቶች ያነሣሣቸዋል፡፡ ቃየል በወንድሙ ላይ በክፉ ቀና፤ ሰይጣን የግድያ ክፉ ድርሰት ደርሶ በመተወን ወንድሙን እንዲገድል አደረገው፡፡ ዘፍ. ፬÷፱፡፡

ክፉ ቅንዓት በደልን ያበዛል፤ “እንዳትበድል አትቅና” የተባለውም ለዚህ ነው፡፡ በክፉ የሚቀኑ በክፉ ይፈተናሉ፡፡ ክፉ ቅናት ሲያድርብን የወንድማችንን እድገት አንፈልግም፡፡ መበለጥ ስለማንፈልግ የትኛውንም ኃጢአት ለመሥራት አንታክትም፡፡ በክፉዎች የምንቀና፤ በክፉም ቀንተን ኃጢአት የምንሠራ ከሆነ እግዚአብሔር ይቀጣናል፡፡

ክፉ ቅንዓት ራስን ይጎዳል፡፡ ሳኦል በዳዊት በክፉ ቀና፡፡ ዳዊት እልፍ ገዳይ መባሉ መንፈሱን ሰላም ነሳው፤ አመመው፡፡ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ሳኦል ዳዊትን ማሳደድ ጀመረ፡፡ የቅናት ጦር ይወረወርበት ነበር፡፡ በመጨረሻ በዳዊት ላይ ይወረውረው በነበረው ሰይፍ የራሱን አንገተ ቆርጦ ጊልቦአ ተራራ ላይ ሞተ፡፡ በክፉ የሚቀኑ (በክፉ ቅናት የተያዙ) መጨረሻቸው ሞት ነው፡፡ ጳውሎስ በክፉ የቀናበትን የልጅነት ጊዜ በመርገም ለእግዚአብሔር የዘላለም እውነት እንደቀና ሁሉ እኛም ለሚበልጠው መልካም ዕድል ልንቀና ይገባል፡፡ ለቤቱ፣ ለክብሩና ለምስጋናው በመልካም መቅናት ተገቢ ነው፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

ክፉ ቅንዓት አጥንትን የሚያነቅዝ፣ መንፈስን የሚያረክስ፣ አእምሮን የሚያባዝን፣ ወደ ክፉ ኃጢአት የሚመራና ሞትን የሚያመጣ ኃጢአት ነው፡፡ “ቅንዓት ጮሆ የማይወጣ ሰይጣን ነው፡፡” በክፉ አንቅና እንዳንበድል፡፡

## ተግባር

- መምህሩ በክፉ የሚያስቀኑ ምክንያቶችን በመጥቀስ ወጣቶች ለሚሻለው ጸጋ በበጎ እንዲቀኑ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# ቃና ዘገሊላ

**የትምህርቱ ዓላማ:-** ክርስቶስ በቃና ዘገሊላ ያደረገውን ወጣቶች እንዲያውቁ ማድረግ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ:-** "የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ፡፡" ዮሐ. ፪÷፮

**ተጨማሪ ምንባብ:-** ዮሐ ፪÷፩-፲፩

## መግቢያ

ቃና ዘገሊላ ከገሊላ ባሕር በስተምዕራብ የሚገኝ ስፍራ ነው፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመጀመሪያውን ተአምር በመፈጸም ክብሩን ገለጠበት፡፡ ድርጊቱ የተፈጸመው የካቲት ፳፫ ጌታችን ኢየሱስ ከገዳመ ቆሮንቶስ ከወጣ በኋላ ሲሆን በዓሉ በቤተ ክርስቲያን ጥር ፲፪ ቀን በታላቅ ድምቀት ይከበራል፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

በዶኪማስ የሰርግ ቤት ጌታችን ኢየሱስ፣ እናቱ ማርያምና ደቀ መዛሙርቱ ታደሙ፡፡ የወይን ጠጅ ባለቀ ጊዜ እመቤታችን ማርያም ለልጇ "የወይን ጠጅ እኮ የላቸውም፡፡" አለችው፡፡ ጌታም "ጊዜየ ገና አልደረሰም" አላት፡፡ እመቤታችን ማርያም ምልጃዋን ልጇ እንደተቀበለ ስላወቀች የሰርጉን ቤት አገልጋዮች "የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ" አለቻቸው፡፡

በአይሁድ የማንፃት ልማድ ምክንያት ስድስት ጋኖች በዚያ ነበሩ፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ጋኖቹን ውኃ ሙሉአቸው" አላቸው፡፡ አገልጋዮቹም እስከ አፋቸው ድረስ ሞሉ፡፡ ጌታም "አሁን ቀድታችሁ ለአሳዳሪው ስጡት" አላቸው፡፡ አገልጋዮቹም እንዳላቸው አደረጉ፡፡

አሳዳሪው ወይኑን በቀመሰ ጊዜ ሙሽራውን ጠርቶ "ሰው ሁሉ አስቀድሞ መልካሙን የወይን ጠጅ ያቀርባል፤ ከሰከሩም በኋላ መናኛውን፡፡ አንተስ መልካሙን የወይን ጠጅ እስከ አሁን አቆይተሃል፡፡" አለው፡፡

www.zeorthodox.org

ጌታችን ኢየሱስ ያለ ምንም ኬሚካል ውኃውን ወደ ወይን ጠጅ በመቀየሩ በቃና ዘገሊላ ክብሩን ገለጠ፤ ደቀ መዛሙርቱም አመኑበት፡፡ የክርስቶስ የወይን ጠጅ የመጀመሪያውን የተደከመበትንና ወጪ የወጣበትን የወይን ጠጅ መናኛ አደረገ፡፡ በዓለም ውስጥ ያለውን ክብር፤ ሃብትና ውበት የሚያስንቅ የሕይወት በረከት በክርስቶስ እጅ አለ፡፡ በፍቅሩ ግዛት ለሚያርፉ ይህ የበረከት በጀት አላቸው፡፡

በቃና ዘገሊላ ጌታችን የእናቱን ምልጃ ተቀብሎ ክብሩን በመግለጥ ዶኪማስን ከውርደት እንዳዳነው ሁሉ፤ ጊዜው ሲደርስ

በመስቀል ተሰቅሎ ንጹሕ ደሙን አፍስሶ የሕይወትን ጉድለት ሞልቶ አዳምንና ልጆቹን ከውርደት አድኖናል፡፡

## ማጠቃለያ

በቃና ዘገሊላ አምላካችን ክብሩን ገለጠ፤ ደቀመዛሙርቱም አመኑበት፡፡ ለዶኪማስ እንግዶች የሰጠው የወይን ጠጅ የቀደመውን መናኛ (ቅራሪ) እንዳስባለ የእርሱ መሥዋዕት ሆኖ መምጣት የኦሪት መሥዋዕትን አስንቆአል፡፡

## ተግባር

- መምህሩ የቃና ዘገሊላ በዓል አከባበር በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እንዴት ነው? በሚል ርእስ ወጣቶቹን ያወያያቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ጌዴዎን

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች መንፈሰ ጠንካራ አማኞች እንዲሆኑ መምከር፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** “በጌዴዎን ዘመን ምድሪቱ አርባ ዓመት ዐረፈች፡፡” መሳ. ፰÷፳፰

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** መሳ. ፮÷፲፩-፰÷፴፫

## መግቢያ

ጌዴዎን የኢዩአስ ልጅ ሲሆን እስራኤላውያን ምድያማውያን ከሚያደርሱባቸው መከራና ጭንቀት እንዲያሳርፋቸው እግዚአብሔር የጠራው የእስራኤል መስፍን ነው፡፡ መሳ. ፮÷፩-፳፬፡፡ የጣዖትን አምልኮ ከሕዝቡ ልብ ከነቀለ በኋላ ከሦስት መቶ ወጣቶች (ሰልፈኞች) ጋር በመሆን የምድያምን ጦር በመውጋት ድል ተጎናጽፏል፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

ጌዴዎን በአፍራ ስንዴ ሲወቃ የእግዚአብሔር መልአክ ተገጠለት፡፡ የእስራኤል መስፍን ሆኖ እንደሚሠራ መታጨቱንም መልአኩ አበሰረው፡፡ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት በመቅረቡ ተቀባይነት ሲያገኝ እግዚአብሔር እንደሾመው እርግጠኛ ሆነ፡፡፡ የበአልን ጣዖት አፍርሶ ይሩብአል ተባለ፡፡

እስራኤላውያን ወደ አምልኮተ እግዚአብሔርና ወደ ገቢረ ጽድቅ እንዲመለሱ በማድረግ ከእግዚአብሔር ጋር ወዳጅነቱን አጠናከረ፡፡ ምድያምን ለመውጋት ሠላሳ ሁለት ሺሕ ሠራዊት ቢያሰልፍም እግዚአብሔር ሦስት መቶዎቹን ብቻ ይዞ እንዲዘምት አደረገው፡፡ ጌዴዎን በጦርነቱ ኃይለኛ ሆነ፤ የእግዚአብሔር ታላቅ ኃይል በእርሱ ድካም ተገለጠ፡፡ ጌዴዎን የምድያምን ነገሥታት ወግቶ፤ በጦርነቱ ድል አደረገ፡፡ መሳ. ፯÷፩-፲፫፡፡

ጌዴዎን ለምድሪቱ ዕረፍት በማምጣቱ ምክንያት እስራኤላውያን ወደ እርሱ መጥተው “ከምድያም እጅ አድነኸናልና አንተ ልጅህም የልጅ ልጆችህም ግዙን” አሉት፡፡ ጌዴዎን ግን “እኔ አልገዛችሁም፣ ልጆቼና የልጅ ልጆቼም አይገዙአችሁም፣ እግዚአብሔር ይገዛችኋል፤” አላቸው፡፡ መሳ. ፰÷፳፪-፳፫፡፡

www.zeorthodox.org

ጌዴዎን ሰባ ልጆች ነበሩት፡፡ መሳ. ፰÷፴፡፡ ከእርሱ ሞት በኋላ የእስራኤል መስፍን የሆነው አቤሜሌክ ከሰባዎቹ የጌዴዎን ልጆች መካከል አንዱ ነው፡፡ ከጌዴዎን ሞት በኋላ እስራኤላውያን ወደ ጣዖት ፊታቸውን አዞሩ፡፡ መሳ. ፰÷፴፫-፴፫፡፡

ጌዴዎን በእስራኤል ላይ አርባ ዓመት በመስፍንነት ፈረደ፡፡ ጌዴዎን መንፈሰ ጠንካራ አማኝ፣ ጀግና የጦር መሪና አስተዋይ መስፍን ነበር፡፡ የጌዴዎን እምነት ከዕብራውያን ታላላቅ አባቶች ጋር ተጠቅሶአል፤ ዕብ. ፲፩÷፴፪፡፡ በምድያም ላይ የተቀዳጀው ድል

ለእግዚአብሔር የመታደግ ተግባር ምሳሌ ሆኖአል፡፡፡ ጌዴዎን ምድሪቱን ለአርባ ዘመናት አሳርፎአል፤ እስራኤላውያን የዘሩትን ማሳደግ፤ ያጨዱትን መብላት ችለዋል፡፡

## ማጠቃለያ

ጌዴዎን መንፈሰ ጠንካራ ሰው፣ ታላቅ የእምነት ጀግና፣ አስተዋይ መስፍንና ብልህ የጦር መሪ ነበር፡፡ በጌዴዎን ዕድሜ ሁሉ እስራኤል ከመከራ ዐረፈች፡፡

## ተግባር

☒ መምህሩ ወጣቶች ከመስፍኑ ጌዴዎን ምን እንደተማሩ ይጠይቃቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# የሠርጉ ቤት ጥሪ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ሰማያዊውን ጥሪ ቸል እንዳይሉ መምከር፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** "ወደ ሰርጉ ኑ፡፡" ማቴ. ፳፪÷፬

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ማቴ. ፳፪÷፩-፲፬ እና ምሳ. ፱÷፩

## መግቢያ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነገርን በምሳሌ ይገልጥ ነበር፡፡ መንግሥተ ሰማያትን በብዙ ምሳሌ መስሎ አስተምሯል፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

በአንድ ወቅት ጌታችን ኢየሱስ፤ "መንግሥተ ሰማያት ለልጁ ሰርግ ያደረገ ንጉሥን ትመስላለች፡፡ የታደሙትንም ወደ ሰርጉ ይጠሩ ዘንድ በሮቹን ላከ፡፡ ሊመጡም አልወደዱም፡፡ ደግሞ ባሮቹን ልኮ፡- እነሆ ድግሴን አዘጋጀሁ፣ ኮርማዎቼና የሰቡት ከብቶቼ ታርደዋል፡፡ ሁሉም ተዘጋጅቶአል፤ ወደ ሰርጉ ኑ በሉአቸው አለ፡፡ እነርሱ ግን ቸል ብለው አንዱ ወደ እርሻው፤ ሌላው ወደ ንግዱ ሄደ፤ የቀሩትም ባሮቹን ይዘው አንገላቱአቸው፤ ገደሉአቸውም፡፡ ንጉሡም ተቆጣ፤ ጭፍሮቹን ልኮ ገዳዮቹን አጠፋ፤ ከተማቸውንም አቃጠለ፡፡ ባሮቹ ወደ መንገድ መተላለፊያ ሄደው በጎዎችንና ክፉዎችን ሰበሰቡ፤ የሰርጉን ቤት ተቀማጮች ሞሉት፡፡ ንጉሡም የተቀመጡትን ለማየት በገባ ጊዜ የሰርግ ልብስ ያልለበሰ አንድ ሰው አየና፡- ወዳጄ ሆይ የሰርግ ልብስ ሳትለብስ እንዴት ወደዚህ ገባህ? አለው፡፡ በጨለማም እንዲጥሉት አዘዘ" በማለት ስለ ሰርጉ ቤት ጥሪ አስተማረ፡፡ ማቴ. ፳፪÷፩-፲፬፡፡

የሰርጉ ጠሪ እግዚአብሔር ነው፡፡ ጥሪው ለሰማያዊ በረከት ነው፡፡ የተጠራነው ሁላችንም ነን፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ "ከሰማያዊው ጥሪ ተካፋዮች የሆናችሁ ቅዱሳን ወንድሞች ሆይ የሃይማኖታችንን ሐዋርያና ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስን ተመልከቱ፡፡" በማለት የጥሪውን ታላቅነት ሰብኳል፡፡ ዕብ. ፫÷፩፡፡

እግዚአብሔር በዘላለም ሕይወት በሰማያዊ ጥሪ የሰውን ልጅ ጠርቷል፡፡ የዓለምን ሥራ ለመሥራት ሰበብ ካበዛን በረከቱ ያልፈናል፡፡ ጠሪ አክባሪ ነው፡፡ እግዚአብሔር ሊያከብረን ሳይንቅ በክብር ለክብር ጠርቶናል፡፡ ጠሪውንም ለማክበር ጥሪውን በክብር መቀበል አለብን፡፡ እግዚአብሔር በሰማያዊ ጥሪ ሰውን ሊጠራ ነቢያትንና ሐዋርያትን ላከ፤ ነቢያቱን ገደሉ፣ ሐዋርያቱን አንገላቱ፡፡ በዚህም ተቆጥቶ ቀጣቸው፤ ከታላቁ ዕድል (ከሕይወት መጽሐፍ) አጎደላቸው፡፡ በሰርጉ ቤት ለመታደም ጥሪውን አክብሮ መገኘት ብቻ ሳይሆን የክብር ልብስ ለብሶ (ያለንን በንጽሕና ጠብቀን) መታደም ያስፈልጋል፡፡ የሰርግ ልብስ ያልለበሰ ከቅድስቲቱ ከተማ፤ ከበጉም ሠርግ አይታደምም፡፡ ልብስ የተባለ ሃይማኖትን፣ ፍቅርን እና ክርስቶስን መልበስ ያስፈልጋል፡፡ ኤፌ. ፬÷፳፬፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

እግዚአብሔር በጽዮን ተራራ ለልጁ ሰርግ ጠርቶናል፡፡ ይህን ሰማያዊ ጥሪ በማክበር ነጩን ልብስ ለብሰን፤ በጸጋው ተደግፈን የጽድቅን ፍሬ በማፍራት በበጉ ሰርግ እንታደም፡፡

## ተግባር

- መምህሩ ወጣቶች የእግዚአብሔርን የድኅነት ጥሪ እንዲያከብሩ ይምከራቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የደቀመዛሙርቱን እግር አጠበ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች በትሕትና ወደ ልዕልና እንዲመጡ ማድረግ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** “እኔ ጌታና መምህር ስሆን እግራችሁን ካጠብሁ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ ትተጣጠቡ ዘንድ ይገባችኋል፡፡” ዮሐ. ፲፫÷፲፫

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ዮሐ. ፲፫÷፩-፲፬

## መግቢያ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ልዑል ሲሆን በትሕትና ተገለጠ፡፡ ባዕለ ጠጋው በከብት በረት መወለዱ፣ ንጉሡ ማረፊያ መጠጊያ ስፍራ ማጣቱ፣ ጌታ ሲሆን ዝቅ ብሎ የተማሪዎቹን እግር ማጠቡና ሁሉን እየቻለ ሁሉን በዝምታ ማለፉ፤ በልቡ ትሑትና የዋህ በሥራውም የትሕትና መምህር ስለሆነ ነው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመከራው ዋዜማ መጋቢት ፳፺ ቀን በቤተ ስምዖን የመጨረሻውን ራት ከደቀ መዛሙርቱ ጋር እየበላ ሳለ ከራት ተነሣ፡፡ ልብሱንም አኖረ፤ ማበሻም ጨርቅ ወስዶ ታጠቀ፤ በመታጠቢያው ውኃ ጨመረ፤ የደቀ መዛሙርቱን እግር ሊያጥብና በታጠቀበት ማበሻ ጨርቅ ሊያብስ ጀመረ፡፡ ወደ ስምዖን ጴጥሮስ መጣ፡፡ ጴጥሮስም፤ “ጌታ ሆይ አንተ የእኔን እግር ታጥባለህን?” አለው፡፡ ኢየሱስም መልሶ “እኔ የማደርገውን አንተ አሁን አታውቀውም፤ በኋላ ግን፤ ታስተውለዋለህ” አለው፡፡ ጴጥሮስ ግን “የእኔን እግር ለዘላለም አታጥብም፡፡” አለው፡፡ ጌታም መልሶ “ካላጠብሁ ከእኔ ጋር ዕድል የለህም፡፡”አለው፡፡

ቅዱስ ጴጥሮስ “ጌታ ሆይ ካጠብህ እጄንና ራሴንም እንጂ እግሬን ብቻ አይደለም” አለ፡፡ ጌታ ኢየሱስ “የታጠበ እግሩን ከመታጠብ በቀር ሌላ አያስፈልገውም” ብሎ መለሰለት፡፡ ጌታችን ኢየሱስ የተማሪዎቹን እግር አጠበ፡፡ በማበሻም ጨርቅ ካበሰ በኋላ ተቀመጠ፡፡ “ያደረኩላችሁን ታስተውላላችሁን?” አላቸው፡፡ “እኔ ጌታና መምህር ስሆን ካጠብኳችሁ እናንተም እንዲሁ አድርጉ” ብሎ አዘዛቸው፡፡

www.zeorthodox.org

ከታላቁ ዙፋን ፍቅር ስቦት የወረደው ጌታ በሥጋ ለባሾች መካከል የጽድቅ ሥራ እያስተማረ፤ እንደ እግዚአብሔር እየሠራ እንደ ሰው ተመላለሰ፡፡ ከጽድቅ ሥራዎች አንዱ ታናሽን ማክበር ነውና በታናሹ በዮሐንስ ተጠመቀ፤ የታናናሾቹን እግር አጠበ፡፡

## ማጠቃለያ

ከታላቁ ዙፋን የወረደው ጌታ የታናሾችን ሥራ በመሥራት የልዕልናን መንገድ አሳየ፤ የጽድቅን ሥርዓት ለሥጋ ለባሾች አስተማረ፡፡ እርሱ በትሕትና የደቀ መዛሙርቱን እግር እንዳጠበ እኛም በትሕትና ልንከባበር ይገባል፡፡

## ተግባር

- መምህሩ የክርስቶስ ትሕትና የተገለጠባቸውን ድርጊቶች በመጥቀስ፤ ወጣቶች በትሕትና ልዑላን እንዲሆኑ፤ ራሳቸውን ዝቅ በማድረግ በጊዜው በኃያሉ ክንድ ከፍ እንዲሉ ይምከራቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ሰሙነ ሕማማት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች በመስቀል የተከፈለውን የክርስቶስን ውለታ እንዳይረሱ ማስተማር፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** "ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን ተሸከመ፤ በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ፡፡" ፩ጴጥ. ፪÷፳፬

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ማቴ. ፳፮÷፶፪-፳፯÷፩-፳፮፣ ሐዋ. ፫÷፲፫-፲፮፣ ገላ. ፫÷፲፫ እና ፊልጵ. ፪÷፰

## መግቢያ

ሰሙነ ሕማማት ማለት የሕማማት ሳምንት ማለት ሲሆን፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ሁላችን በደል የተቀበለውን መከራ የምናስብበት ሳምንት ነው፡፡ ሰሙነ ሕማማት የክርስቶስ የድል ዋዜማ ነው፡፡ የመዳናችን ራስ በመከራ የተፈጸመበት ሳምንት ነው፡፡ በቤተክርስቲያናችን ከሆሳዕና እስከ ቀዳም ስዑር ያለው ጊዜ ሰሙነ ሕማማት ይባላል፡፡ በዚህ ሳምንት ልዩ ሥርዓተ አምልኮ ይፈጸማል፤ ግብረ ሕማማት በየሰዓቱ ይነበባል፤ ለክብሩ የአምልኮ ስግደት ይሰገዳል፤ ዳዊት ይስተዛዘላል፡፡ ከጸሎተ ሐሙስ በቀር በሌሎቹ ቀናት ሥርዓተ ቅዳሴ አይከናወንም፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

## የሰሙነ ሕማማት ቀናት የየራሳቸው ታሪክ አላቸው፡፡

1. **እሑድ- ሆሳዕና፡-** ‹‹ሆሳዕና›› ማለት "አሁን አድን (መድኃኒት)" ማለት ነው፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከቤተ ፋጌ ወደ ኢየሩሳሌም በአህያና በውርንጭላዋ ተጭኖ የገባበት ታሪክ የመታሰቢያ በዓል ነው፡፡ ማቴ. ፳፩÷፩-፲፫፡፡

2. **ሰኞ፡-** በዚህ ዕለት ጌታችን ኢየሱስ በቤተ መቅደስ ሲሸጡና ሲለውጡ የነበሩ ነጋዴዎችን በጅራፍ እየገረፈ አስወጣ፡፡ ማቴ. ፳፩÷፲፫፡፡ በተጨማሪም ፍሬ ያልተገኘባትን በለስ ረገመ፡፡ ማቴ. ፳፩÷፲፰-፳፡፡

3. **ማክሰኞ፡-** በዚህ ዕለት ጌታ ኢየሱስ ስለ ሥልጣኑ ተጠየቀ፡፡ የአይሁድንም ጥያቄ በጥያቄ መለሰ፡፡ ማቴ. ፳፩÷፳፫-፳፯፡፡

www.zeorthodox.org

4. **ረቡዕ፡-** በዚህ ዕለት ሲነሃድሪየም የተባለው የአይሁድ ሸንጎ ክርስቶስን ለመያዝ መከረ፡፡ ጌታም በቤተ ስምዖን የማርያምን መብአ ተቀበለ፡፡ ሉቃ. ፯÷፴፮-፶፡፡

5. **ሐሙስ፡-** በዚህ ዕለት ጌታ ኢየሱስ፡-

- የደቀ መዛሙርቱን እግር አጠበ፡፡ ዮሐ. ፲፫÷፮-፲፬፡፡
- ሥርዓተ ቁርባንን አስተማረ፡፡ ማቴ. ፳፮÷፳፮፡፡
- ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በማዕድ ተቀመጠ፡፡ ማቴ. ፳፮÷፳-፳፮፡፡
- በአትክልቱ ሥፍራ ጸለየ፡፡ ማቴ. ፳፮÷፴፮-፵፭፡፡
- በይሁዳ መሪነት በአይሁድ ጭፍሮች በፈቃድ ተያዘ፡፡ ማቴ. ፳፮÷፵፮-፶፯፡፡

## 6. ዐርብ፡- በዚህ ዕለት ኢየሱስ ክርስቶስ፡-

- በአይሁድ ሸንጎ ፊት ቀረበ፡፡ ማቴ. ፳፯÷፩
- በጲላጦስ አደባባይ በሐሰት ተከሰሰ፡፡ ማቴ. ፳፯÷፲፩
- ያለ በደሉ ሞት ተፈረደበት፡፡ ማቴ. ፳፯÷፳፫-፳፭
- በጨካኞች እጅ ተገረፈ፡፡ ማቴ. ፳፯÷፳፱
- እርጥብ መስቀል ተሸክሞ ወደ ቀራንዮ ተጓዘ፡፡ ማቴ. ፳፯÷፴፩
- በተሸከመው መስቀል ተሰቀለ፡፡ ማቴ. ፳፯÷፴፭
- ሰባት ተአምራት ተፈፈሙ፡፡ ማቴ. ፳፯÷፵፭-፶፬
- ሰባት የፍቅር ቃላት ተናገረ፡፡ ማቴ. ፳፯÷፵፭
- በፈቃዱ ነፍሱን ተወ፡፡ ማቴ. ፳፯÷፶
- በአርማትያሱ ዮሴፍ መቃብር ተቀበረ፡፡ ማቴ. ፳፯÷፶፯-፷፩

**7. ቅዳሜ፡- ቀዳም ስዑር ይባላል፡፡ በዚህ ዕለት ጌታ በመቃብር ነበር፡፡** ደቀ መዛሙርቱ በፍርሃት ደጅ ዘግተው ዋሉ፡፡ ዮሐ. ፳፡፡

## ማጠቃለያ

ሰሙነ ሕማማት ያለ በደሉ ተከስሶ በመገረፉ ቁስል የፈወሰንን የኢየሱስ ክርስቶስን ውለታ የምንዘክርበት ሳምንት ነው፡፡ ይህ ሳምንት ቅዱስ ሳምንት ይባላል፡፡ ጌታ ያደረገልንን በማሰብ የምናመሰግንበት ጊዜ ነው፡፡

## ተግባር

www.zeorthodox.org

- መምህሩ ሰሙነ ሕማማት በቤተ ክርስቲያናችን እንዴት እንደሚዘከር ለወጣቶች ይንገራቸው፡፡

# የክርስቶስ መስቀል

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** መከራ መስቀሉን ወጣቶች እንዲያስቡ ማድረግ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** "ኢየሱስ ክርስቶስ ነውርን ንቆ በፊቱ ስላለው ደስታ በመስቀል ታግሶ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጧል፡፡" ዕብ. ፲፪÷፪

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ፊልጵ ፪÷፯÷፱ እና ዕብ. ፬÷፯

## መግቢያ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከልዕልናው ወርዶ፤ የባሪያን መልክ ይዞ፤ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ፤ ለመስቀል ሞት ታዘዘ፡፡ የመዳናችንን ራስ በመከራ ፈጸመ፡፡ የሁላችንን ኃጢአት በእንጨት ላይ ተሸክሞ በመርገፉ ቁስል ፈወሰን፡፡ እንደ በግ የተቅበዘበዝነውን ወደ ነፍሳችን እረኛ ወደ እርሱ መለሰን፡፡ ፩ጴጥ. ፪÷፳፬

## የሳምንቱ ትምህርት

መስቀል ሁለት ዓይነት ሲሆን ዕፀ መስቀልና መከራ መስቀል ይባላል፡፡ የክርስቶስ መስቀል ስንል ዕፀ መስቀሉንና ስለ እኛ የተቀበለውን መከራ መስቀል እናስባለን፡፡ ክርስቶስ እርጥብ መስቀል ተሸክሞ ከሊቶስጥራ እስከ ቀራንዮ በመከራ ተጨንቋል፡፡ ነቢዩ ኢሳይያስ በትንቢቱ የክርስቶስን መከራ መስቀል ሲገልጥ "በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ፤ ሕማማችንም ተሸክሞአል፡፡ ስለመተላለፋችን ቆሰለ፤ በእርሱ ቁስል እኛ ተፈወስን፡፡ ተጨነቀ ተሰቃየም፡፡ በማስጨነቅና በፍርድ ተወሰደ፡፡ ከትውልዱ ይህን ማን አስተዋለ?" ብሏል፡፡ ኢሳ. ፶፫÷፩-፲፪፡፡

የክርስቶስ መከራ ንጹሕ ሆኖ ሳለ በኃጢአተኞች መነቀፍ፣ ያለ በደሉ መገረፍ፣ በአባቱ መተው፣ በግፍና በሐሰት የሞት ፍርድ መቀበልና በወዳጆቹ መከዳትን ያጠቃልላሉ፡፡ መከራ ሲቀበል በሸላቾቹ ፊት ዝም እንደሚል በግ በዝምታ ነው፡፡፡ ሲሰድቡት መልሶ አልተሳደበም፡፡ መከራ ስላበዙበት አልዛተም፡፡ 1ጴጥ. ፪÷፳፫፡፡

የክርስቶስ ዕፀ መስቀል ኃይላችን፤ መከራ መስቀሉ ትምክህታችን ነው፡፡ ገላ. ፮÷፲፬፡፡ በመስቀሉ ጥልን ገደለ፡፡ ኤፌ. ፪÷፲፮፡፡ በመስቀሉ ደም ሰላምን አደረገ፡፡ ቆላ. ፩÷፳፡፡ በመስቀሉ ጠላታችንን ከነጽሕፈቱ ከመንገዳችን ጠርቆ አስወገደው፡፡ ቆላ. ፪÷፲፬፡፡ የክርስቶስ መስቀል የድል ዓርማ ነው፡፡ የክርስቶስ መስቀል የሰላም ምልክት ነው፡፡ የክርስቶስ መስቀል ቃል አለው፤ የመስቀሉም ቃል ለሚጠፉትም ሞኝነት ነው፤ ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚብሔር ኃይል ነው፡፡ ፩ቆሮ. ፩÷፲፰፡፡

www.zeorthodox.org

የክርስቶስ መስቀል የውርደት ታሪክ ተዘግቶ፤ የድል ታሪክ የተጀመረበት የዕርቅ ማኅተም ነው፡፡ የክርስቶስ ዕፀ መስቀል

ለአማኞች ከጠላት ቀስት ማምለጫ ምልክት ነው፤ መከራ መስቀሉ ትምክህታቸውና አብነታቸው ነው፡፡ ስለስሙ ሲናቁ፣ ሲገረፉና ሲገፉ የጽናት አብነት አላቸው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ፤ "በነፍሳችሁ ዝላችሁ እንዳትደክሙ ከኃጢአተኞች በደረሰበት እንዲህ ባለ መቃወም የጸናውን አስቡ" በማለት በመከራው ጽናት አብነታችን እንደሆነ አረጋግጧል፡፡ ዕብ. ፲፪÷፫፡፡ ክርስቶስ በመከራ በመታገሡ እኛን አድኖአል፤ በአባቱ ቀኝ ተቀምጧል፤ ከስም ሁሉ በላይ የሆነውን ስም ተቀብሏል፤ የክብርና የምስጋና ዘውድ ጭኖአል፡፡ ዕብ. ፪÷፱-፲፯፤ ፲፪÷፪፤ ፊልጵ. ፪÷፱፡፡

## ማጠቃለያ

የክርስቶስ ዕፀ መስቀል የድል ዓርማችን፤ መከራ መስቀሉ የጽናት አብነታችን ነው፡፡ እርሱ በመስቀሉ ደም ጥልን ገድሎ ሰላምን አድርጓል፤ የክርስቶስ መስቀል ብዙ የድል ፍሬዎችን አውርሶናል፡፡

## ተግባር

- መምህሩ ወጣቶች የክርስቶስ መከራ መስቀል ያስገኘውን ጥቅም በዝርዝር እንዲገልጡ ያድርግ፡፡

www.zeorthodox.org

# የተለሰነ መቃብር

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች በእውነተኛ ማንነት እንዲቆሙ ማድረግ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** "የተለሰኑ መቃብሮችን ስለምትመስሉ ወዮላችሁ፡፡" ማቴ. ፳፫÷፳፯

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ማቴ. ፳፫÷፩-፴፱

## መግቢያ

ፈሪሳውያንና ጻፎች በክርስቶስ ትምህርት ተወቅሰዋል፡፡ ጌታ በተራራው ስብከት ግብዝነታቸውን እንዳንመስል አስጠንቅቋል፡፡ ማቴ. ፮÷፩-፲፰፡፡ እነዚህን ግብዞች በቀጥታ የገሠጸበት ትምህርት በማቴዎስ ወንጌል ተመዝግቧል፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

### የግብዞች ማንነት መገለጫዎች፡-

- ሲመጸውቱ መለከት ያስነፋሉ፡፡ ማቴ. ፮÷፪፡፡
- ሲጾሙ ለሰው ሊታዩ ይጠወልጋሉ፡፡ ማቴ. ፮÷፲፮፡፡
- ሲጸልዩ ለሰው ሊታዩ በአደባባይ ይንበረከካሉ፡፡ ማቴ. ፮÷፭፡፡
- በጣታቸው የማይነኩትን ለሰው ያሸክማሉ፡፡ ማቴ. ፳፫÷፬
- የማይኖሩበትን ያስተምራሉ፡፡ ማቴ. ፳፫÷፫፡፡
- የከበሬታ ስፈራና ስም ይፈልጋሉ፡፡ ማቴ. ፳፫÷፭፡፡
- በጸሎት ርዝመት እያሳበቡ የመበለቶችን ቤት ይበላሉ፡፡ ማቴ. ፳፫÷፲፬፡፡
- ትንኝን ያጠራሉ፤ ግመልን ይውጣሉ፡፡ ማቴ. ፳፫÷፳፬፡፡
- የወጪቱን ውጪ ያጠራሉ፤ ውስጣቸው ግን ግፍ ተሞልቶአል፡፡ ማቴ. ፳፫÷፳፭
- የሚያደርጉትን ሁሉ ሰው እንዲያይላቸው ይፈልጋሉ፡፡ ማቴ. ፳፫÷፭፡፡

www.zeorthodox.org

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተለሰኑ መቃብሮች መሰላቸው፡፡ መቃብር ውጪው በእምነ በረድ ያጌጠ የሚስብ መልክ አለው፤ ውስጡ ግን በበሰበሰ ሥጋና በአጥንት የተሞላ ነው፡፡ ጸሐፍትና ፈሪሳውያንም ውስጣቸው ግፍ፣ ኃጢአትና ርኩሰት ተሞልቶ ላያቸውን ያሳምሩ ነበር፤ የወጭቱን ውጪውን ብቻ እያጠሩ ውስጣቸው በክፋት ተዳድፎ ነበር፡፡፡ ስለዚህ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ፤ "በውጭ ለሰው እንደጻድቃን ትታያላችሁ፤ በውስጣችሁ ግን ግብዝነትና ዓመፅኝነት ሞልቶባችኋል፡፡" አላቸው፡፡

ለሰው እንደ ቅዱስ እየታዩ ውስጣቸው በነውር የተሞላ ማንነት ያላቸው ሰዎች የተለሰኑ መቃብሮች ይባላሉ፡፡ ክርስቲያን ለሰው እንዲታይ ሳይሆን ለአምላኩ በመታመን ይሠራል፤ በስውር ያየው አባቱ በግልጥ ይከፍለዋል፡፡ ግብዞች ግን በማይኖሩባት ማንነት እንደቲያትረኛ ሲተውኑ ይኖራሉ፤ ከመጋረጃ ጀርባ የተሸፈነ ክፋት አላቸው፡፡

## ማጠቃለያ

ውስጣችን በቅድስና ሊያጌጥ፤ ብርሃናችን በሰው ፊት ሊያበራ፤ በአሕዛብ መካከል ኑሯችን መልካም ሊሆን፤ ለሰው እንድንታይ ሳይሆን በስውር አይቶ በግልጥ ለሚከፍለን አምላክ በመታመን በጽድቅ ሥርዓት እየታዘዝን በመታመን ልንኳዝ ይገባል፡፡፡

## ተግባር

- መምህሩ ሰው ግብዝ ቢሆን በሚደርስበት ጉዳት ላይ በማተኮር ወጣቶችን ያወያያቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# እስራኤል በተስፋይቱ ምድር

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** የእስራኤላውያንን ኑሮ በከነዓን ለወጣቶች ማሳየት፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** “ፍሬዋንና በረከትዋን ትበሉ ዘንድ ወደ ፍሬያማ ምድር አገባኋችሁ፤ ነገር ግን በገባችሁ ጊዜ ምድሬን አረከሳችሁ፤ ርስቴን አጎሳቆላችሁ፡፡” ኤር. ፪÷፯

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ኢያሱ ፲፫÷፩-፳፬ እና መሳ. ፩÷፩-፳፩÷፳፫

## መግቢያ

እስራኤላውያን ከግብጽ ባርነት ከወጡ በኋላ አርባ ዓመታት በበረሐ ተጉዘው ምድረ ርስት ከነዓንን ወረሱ፡፡ የሕጉ መጽሐፍ ተነበበላቸው፡፡ ርስታቸውን ተካፈሉ፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ግንኙነት እንዲጠብቁ ተነገሩ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

የከነዓንን ምድር የወረሰው አዲሱ ትውልድ ነው፡፡ በኢያሱ የተመራው ይህ ትውልድ በዮርዳኖስና በሜዲትራንያን በባህር መካከል ያለውን መሬት ለመውረስና ግዛቱን ለማስፋት ከተለያዩ አገሮች ታላላቅ ነገሥታት ጋር ብርቱ ሰልፍ ገጥሟል፡፡ ምድሪቱ ዐርፋ በሰላም መኖር ሲጀምሩ፣ ኑሯቸው ሲደላደልና ስጋቸው ሲመቸው እግዚአብሔርን በኃጢአት አሳዘኑት፡፡ ርስቱን በማጎሳቆላቸውና ወደ ጣዖት ፊታቸውን በመመለሳቸው ምክንያት ተቀጡ፡፡ ኤር. ፪÷፳፫፡፡

የምድሪቱን በረከት እየበሉ የበረከትን ምንጭ የሕይወትም ጉድጓድ የያዕቆብን አምላክ በመተዋቸው ጠላት አስጨነቃቸው፡፡ በመከራቸው ሲጮሁ እግዚአብሔር ቸል አላላቸውም፤ መሳፍንትን እያስነሣ ለምድሪቱ ዕረፍት ለሕዝቡ ሰላም ይሰጥ ነበር፡፡

እስራኤላውያን በተስፋይቱ ምድር በመሳፍንት ይመሩ ነበር፡፡ የመሳፍንቱ ዘመን ሰው በፊቱ መልካም መስሎ የታየውን እንዲፈጽም በማድረጉ እስራኤል ለመከራ ተጋልጣ ነበር፡፡ እስራኤላውያንም በጽኑ ረኃብ ተጨንቀው ነበር፡፡ እስራኤላውያን በተስፋይቱ ምድር ተስፋቸውና አውራሻቸው የሆነውን እግዚአብሔርን ብቻ ሲያመልኩ ምድሪቱ በበረከት ትነበኝ ነበር፡፡ ሕዝቡም እንጀራን ጠግቦ ያድር ነበር፡፡

www.zeorthodox.org

የእስራኤልን የቀደመ ትውልድ ጉዞ የገታው አለማመንና አለመታዘዝ ነበር፤ የአዲሱ ትውልድ ችግር ደግሞ ለቃልኪዳኑ አለመታመን፣ በምኞት እግዚአብሔርን መርሳትና ጣዖት ማምለክ ነበር፡፡

እስራኤል በተስፋይቱ ምድር በነገሥታት ተገዝተዋል፤ በዘርና በሃይማኖት ተከፋፍለዋል፡፡ ብዙ ጊዜ ለጠላት እጃቸውን

ሰጥተዋል፡፡

## ማጠቃለያ

እስራኤላውያን በተስፋይቱ ምድር እርም የሆነውን በመተው፣ ጠላትን ተዋግተው ርስትን በማስፋት፣ እግዚአብሔርን በማምለክ፣ በመሳፍንትና በነገሥታት በመመራት፣ ሲክዱ እየተቀጡ ሲያምኑ በበረከትና በጥበቃው እየተከበቡ ኖረዋል፡፡ በርስታችን ላይ በንጽሕናና በጽኑ እምነት እንመላለስ፡፡

## ተግባር

- መምህሩ ወጣቶች በእምነት በመጽናት ለእግዚአብሔር በመታዘዝ እንዲኖሩ ይምከራቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ከሰዎች ጋር ተግባብቶ መኖር

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ከሰዎች ጋር ተግባብቶ የመኖር ጥበብን ወጣቶች እንዲገነዘቡ ማድረግ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** "ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ" ሮሜ. ፲፪÷፲፰

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ፩ተሰ. ፭÷፲፫-፲፭ እና ቆላ. ፫÷፲፪-፲፭

## መግቢያ

ለሰው ሰው ያስፈልገዋል፡፡ ሰዎች በጉዞአችን ሁሉ ይጠቅሙናል፡፡ ከሰው ጋር ተግባብቶ መኖር ትልቅነት ነው፡፡ የሰዎች አመለካከትና ጠባይ ይለያያል፡፡ ሰዎችን በመረዳት እንደጠባያቸው መቀበልና በሰላም መኖር ጥበብ ነው፡፡ መንፈሳዊ ሰው ከአስቸጋሪ ሰዎች ጋር እንኳን ቢሆን በየዋህነትና በልባምነት መኖር ይችላል፡፡ ቅዱሳን ከአራዊት ጋር ኖረዋል፤ ሰው ከሰው ጋር ተግባብቶ መኖር ለምን ይከብደዋል?

## የሳምንቱ ትምህርት

ከሰዎች ጋር ተግባብቶ መኖር መንፈሳዊ ጥበብ ይፈልጋል፡፡ ከሰዎች ጋር ያለንን ግንኙነት በመንፈስ ፍሬዎች መጠበቅ ይኖርብናል፡፡ ከሰዎች ጋር ተግባብቶ ለመኖር የሰዎችን ሥነ ልቦና፣ አመለካከትና ጠባይ ለይቶ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ ሰዎች እንድናከብርላቸው የሚፈልጉት ብዙ ነገር አለ፡፡ ማንነታቸውን መቀበል፣ ክብረ ነክ የሆኑ ቃላቶችን አለመጠቀም፣ ሰውን በሰውነቱ ማክበር፣ የሚጠሉትን አለማድረግና በሚወዱት ነገር ላይ ብቻ የተመሠረተ ድርጊትን መከታተል ከሰዎች ጋር ተግባብቶ ለመኖር ይጠቅመናል፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ፤ "ቢቻላችሁስ . . . ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ" ብሏል፡፡ አብረን መኖር የማንችለው በጎ ከሆነው ዓላማችን ከሚያሰናክለን፣ ከእግዚአብሔር ፍቅር ከሚለየንና ኃጢአትን ከሚያስለምደን ሰው ጋር ነው፡፡ የሰው ጠባዩ እንደመልኩ ስለሚለያይ ልበ ሰፊ ካልሆንን አብረን ለመኖር የሚፈትኑ ጠባዮች ያሉት ሰው ያጋጥመናል፡፡

www.zeorthodox.org

ከሰዎች ጋር ተግባብቶ ለመኖር በእኛ እንዲደረግ የማንፈልገውን በሌሎች ማድረግ የለብንም፡፡ ለእኛ እንዲደረግልን የምንፈልገውን ደግሞ በደስታ እናድርግላቸው፡፡ ወዳጅ ለማግኘት ጥሩ ወዳጅ ሆኖ መገኘት አስፈላጊ ነው፡፡ መልካም ሰዎች ከፈለግን መልካም የመሆን ሓላፊነት አለብን፡፡ ሰዎች ያደጉበት ማኅበረሰብ ባሕል፣ አካባቢ፣ የተማሩት ትምህርት፣ የሚከተሉት ርእዮተ ዓለም፣ የሚያምኑት እምነት፣ የሚመሩበት የኑሮ ዘይቤ፣ ከሰዎች የሚፈልጉት ነገርና የሚያራምዱት አመለካከት ይለያያል፡፡

ስለዚህ ከሰዎች ጋር ተግባብቶ ለመኖር በመጀመሪያ ሰዎችን መግባባት፣ የልባቸውን መሻት ማወቅና ሰብእናቸውን መቀበል ያስፈልጋል፡፡ ሰዎች አስቻጋሪ ሰብእና ሊኖራቸው ይችላል፡፡ የእኛ መልካምነት እንዲፈተን ከእነርሱ ጋር አብረን መኖር አለብን፡፡ እኛ መልካም ብንሆን እንኳ እየኖርን ያለነው ክፋት በተንሠራፋበት ዓለም ስለሆነ በዙሪያችን ክፉዎች ይኖራሉ፡፡

ስለዚህ ከሰዎች ጋር ባለን ግንኙነት ልበ ሰፊነት፣ ትዕግሥት፣ የዋህነት፣ ልባምነት፣ ይቅር ባይነት፣ የወንድምን ጥቅም ማስቀደም፣ እምነትና ፍቅር ያስፈልጉናል፡፡ በመካከላችን አለመግባባት ሲፈጠር በልበ ሰፊነት መወያየት፣ ችግሮችን በይቅርታ ማለፍና በፍቅር መኖር ይጠበቅብናል፡፡

## ማጠቃለያ

ከሰዎች ጋር ተግባብቶ መኖር ትልቅ ጥበብ ነው፡፡ በጉዟችን ሁሉ ሰዎች እንደሚያስፈልጉን በማመን በልበ ሰፊነትንና በይቅርታ መንፈስ ቢቻለን ከሰዎች ሁሉ ጋር በሰላም መኖር አለብን፡፡ የመልካም ምኞት መግለጫዎች መለዋወጥ፣ በሐዘንና በደስታ መጠያየቅ ከሰዎች ጋር ተግባብቶ የመኖር ግንኙነታችንን ያሳድጋሉ፡፡

## ተግባር

- መምህሩ የሰውን መልካም ግንኙነት በሚያፈርሱ ችግሮች ላይ ወጣቶችን ያወያያቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ድህነት

**የትምህርቱ ዓላማ:-** ወጣቶች በነገር ሁሉ መንፈሳዊና ሥጋዊ ብልጥግናን ገንዘብ እንዲያደርጉ መምከር፡፡

**የሚጠና ጥቅስ:-** "የእንቅልፍ ብዛት የተበጫጨቀ ጨርቅ ያለብስሃል" ምሳ. ፳፫÷፳፩

**ተጨማሪ ምንባብ:-** ምሳ. ፯÷፯-፲፩፣ ፪ተሰ. ፫÷፲ እና ፪ጢሞ. ፯÷፯-፲፯

## መግቢያ

ድህነት ሰው እንደምኞቱ እንዳይጓዝና እንዳሰበው እዳይኖር የሚያሰናክል ወጥመድና አንቆ የሚይዝ ቀንበር ነው፡፡ ድህነት ለመኖር የሚያስፈልገንን ማጣት ማለት ነው፡፡ የምርጫ ማጣት ችግርም ነው፡፡ ሰው ባዕለ ጸጋ አእምሮ ተሸክሞ ድሃ ሲሆን ያሳፍራል፡፡ ድህነት ብዙ ዓይነት መልክ አለው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

**1. የዕውቀት ድሆች፡-** መማር እየቻሉ የማይማሩና ለመማር ዕድል ያጡ ሰዎች የዕውቀት ድሆች ይሆናሉ፡፡ ሕይወትን የሚመራት የሕይወት ዕውቀት ነው፡፡ ዕውቀት ሲጎድል የሚጎድል ብዙ ነገር አለ፡፡ ሰው በመንፈሳዊም ሆነ በሥጋዊ ጥበብ የበረታ እውቀት ሲኖረው የተሻለ የኑሮ ሥርዓት ይመሠርታል፡፡ በዕውቀት ድሃ መሆን ምርጫ ያሳጣል፡፡ በኑሯችን የሚያስፈልጉንን መሠረታዊ ነገሮች እንዴት ማሟላት እንዳለብን ለማወቅ እንኳ ዕውቀት ያስፈልገናል፡፡ የሥጋዊ ብልጥግና መሠረቱ ዕውቀት ነው፡፡ የሃይማኖትም መሠረቱ መስማት ስለሆነ ለማመን ማወቅ ያስፈልጋል፡፡

**2. የሃብት ድሆች፡-** መሠረታዊ የኑሮ ጥያቄዎችን መመለስ ካለመቻል ድህነት ይመነጫል፡፡ ሰው መጠለያ፣ ልብስና ምግብ ካጣ ድሃ ሆነ እንላለን፡፡ ይህ ድህነት በሁለት መንገዶች ይመጣል፡፡

**2.1. በስንፍና፡- ስንፍና የድህነት መሠረት** ነው፡፡ መሥራት እየቻሉ አለመሥራት ስንፍና ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ፤ "ሊሠራ የማይወድ አይብላ" በማለት ለሰነፎች እንጀራ ማቅረብ ተገቢ እንዳልሆነ ተናግሯል፡፡ ፪ተሰ. ፫÷፲፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ከአገልግሎት በሚተርፈው ጊዜ ድንኳን ይሠራ ነበር፤ በኑሮው ለማንም ሸክም ሆኖ አልከበደም፡፡ ሰነፎች ግን ጊዜያቸውን በአልጋ ላይ ያሳልፋሉ፡፡ በምድራችን ተመልሶ እንደገና የማናገኘው እና ውድ ነገር ጊዜ ነው፡፡ ጊዜን ማባከን ሕይወትን ማባከን ነው፡፡ የሰነፎች ወዳጅ እንቅልፍ ነው፡፡ ጠቢቡ ሰሎሞን "የእንቅልፍ ብዛት የተቦጫጨቀ ጨርቅ ያለብሳል" እንዳለው እንቅልፍ ወዳጆች ድሆች መሆናቸው ሳይታለም የተፈታ ነገር ነው፡፡

ጠቢቡ ሰሎሞን "ወደ ገብረ ጉንዳን ሂድ፤ መንገድዋንም ተመልከተህ ጠቢብ ሁን፤ አለቃና አዛዥ ገዢም ሳይኖራት

www.zoorthodox.org

መብልዋን በበጋ ታሰናዳለች፤ አንተ ታካች እስከ መቼ ትተኛለህ? እንግዲህ ድህነት እንደ ወንበዴ ችጋርም ሰይፍ እንደ ታጠቀ ሰው ይመጣብሃል" በማለት እንቅልፋሞችን የሚቀሰቅስ የብልጥግና ደወል ጽፏል፡፡ ምሳ. ፮÷፮-፲፩፡፡

2.2. **መሥራት የሚያስችል ሰውነት በማጣት፡-** አካል ጉዳተኛ ሆነው መሥራት ሳይችሉ ነገር ግን ሥራ የሚሠሩ ትልቆች ናቸው፡፡ አካል ጉዳተኛ ሆነው የሚሠሩ ሰዎች አይታችኋል? እጅ ባይኖራቸው በእግራቸው የሚሠሩ አሉ፡፡ ዓይነ ስውር ሆነው ከፍተኛ ሥራዎችን የሚሠሩ፣ ለሌሎችም የሚተርፉ አሉ፡፡ በአካል ጉዳት ምክንያት መሥራት የማይችሉትን ግን መደገፍ ተገቢ ነው፡፡

3. **የመንፈስ ድሆች፡-** በክርስቲያናዊ ሕይወት የጸና የመንፈስ ድህነት ከእግዚአብሔር ጋር አንድ የሚያደርገን መንፈሳዊ ብልጥግና ነው፡፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ፤ "በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብፁዓን ናቸው፤ መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና" በማለት የመንፈስ ድህነት የመንፈስ ብልጥግና እንደሆነ አስተምሮናል፡፡ ማቴ. ፭÷፫፡፡

4. **የምግባር ድሆች፡-** ሰው የበጎ ነገር ባዕለ ጠጋ መሆን አለበት፡፡ ፪ጢሞ. ፮÷፲፮-፲፱፡፡ የምግባር ድህነት ኃጢአት ነው፡፡ የበጎ ነገር ባለጠጋ ለመሆን በመንፈስ ድሃ በመሆን የጽድቅ ፍሬዎችን ማፍራት ይጠበቅብናል፡፡

## ማጠቃለያ

የዕውቀት ድሆችን እናስረዳቸው (እናስተምራቸው)፤ በስንፍና ድሀ የሆኑትን ዓሣ መስጠት ሳይሆን ዓሣ ማጥመድ እናሳያቸው፤ በአካል ጉዳት፣ በዕርግና ምክንያት መሥራት ያልቻሉ ድሆችን እንርዳቸው (በኑሮ እንደግፋቸው)፤ በክርስቲያናዊ ሕይወት የጸኑ የመንፈስ ድሆችን እንማርባቸው፡፡

## ተግባር

- መምህሩ ወጣቶች ከዛሬው ትምህርት ምን እንደተረዱ ይጠይቃቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ስሕተትን ማመን

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ስሕተትን በማመን የመስተካከልን ትልቅነት እንዲያተርፉ መምከር፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** "ኃጢአቱን የሚሰውር አይለማም፤ የሚናዘዝባት የሚተዋት ግን ምሕረትን ያገኛል፡፡" ምሳ. ፳፰÷፲፫

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ፩ዮሐ. ፩÷፱-፲

## መግቢያ

ስሕተት የሚያስተውላት ባይኖርም የሕይወትን ሰላም የምታደፈርስ መርዝ ናት፡፡ ስሕተት የሰውን ኅሊና ታጎሳቁላለች፡፡ ስሕተትን ማመንና መስተካከል ትልቅነት ነው፡፡ ስሕተታችንን በጸጋ ተቀብለን በደስታ አርመን ስንስተካከል የኅሊናችንን ሰላም እናተርፋለን፤ ሰዎችን እናስደስታለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

ስሕተትን ማመን ማለት ደካማ መሆንን ተረድቶ በመበርታት መወሰን ማለት ነው፡፡ ሰው ደካማ መሆኑን ካልተረዳ ስሕተቱን በደስታ አያምንም፤ ሁልጊዜ ልክ ነኝ ብሎ የሚያምን ሰው ደግሞ ሰውነቱን ገና ያልተቀበለ ነው፡፡ የሚሠራ ይሳሳታል፤ የማይሠራ ይተቻል፡፡ ሳይሠራ ሌላውን የሚነቅፍ መቸም የማይታረመው ጣቶቹ በሌላው ላይ ስለተዘረጉና ራሱን የመመልከቻ ጊዜ በማጣቱ ነው፡፡ የሚሠራ ግን ይሳሳታል፤ ስሕተቱን አምኖ ራሱን በማረምና በመስተካከል ጉዞውን የሚቀጥል ደግሞ መንገዱን በንጽሕና በማቅናት ስኬታማ ይሆናል፡፡ ትልቁ ስሕተት አለመሥራት እንጂ ሠርቶ መሳሳት አይደለም፡፡

ስሕተታችንን የምናምነው የሚሳሳት፤ ፍፁም ያልሆነ፤ ደካማ ሥጋ መልበሳችንን ስናስተውል ነው፡፡ ስሕተትን ማመን ለቀጣዩ ጉዞ ስኬት ወሳኝ ነው፡፡ ስሕተቱን አምኖ መስተካከል የማይፈልግ ደግሞ ስሕተቱን ይጨምራል፡፡

ዳዊት ከቤርሳቤህ ጋር ተኛ፡፡ ቤርሳቤህ በፀነሰች ጊዜ ስሕተቱን በስሕተት ለመሸፈን ባሏን በጦር ሜዳ አስገደለ፡፡ የመጀሪያውን ስሕተት በጸጋ ተቀብሎ በማመን ቢስተካከል ኖሮ ሁለተኛውን የከፋ ስሕተት አይፈጽምም ነበር፡፡ ዳዊት ስሕተቱ ሲበዛ እግዚአብሔር ስለፈጸመው ስሕተት የሚነግረውን ላከለት፡፡ ስሕተታችንን አምነን እና በወቅቱ ታርመን ለመስተካከል ካልፈለግን ለሰው አፍ ተላልፈን እንሰጣለን፡፡ ዳዊት ከነቢዩ አፍ በምሳሌ ስሕተቱ ሲነገረው በራሱ ፈርዶ ንስሐ ገባ፡፡

www.zeorthodox.org

ስሕተትን ማመን ማለት በራስ መፍረድ ማለት ነው፡፡ የዳዊት ልብ ያረፈው ስሕተቱን አምኖ ንስሐ ሲገባ ነው፡፡ መዝ. ፶÷፩-፲፱፡፡ **እግዚአብሔር የስሑታንን *መንገድ*** የሚያቀናው በንስሐ ሲመለሱ ነው፡፡ ስሕተትን ማመን ከእግዚአብሔር፣ ከሰውና ከኅሊናችን ጋር ያስታርቀናል፡፡

ስሕተትን ማመንና ስሕተትን አለመድገም ምሕረትን ያስገኛል፡፡ ሰሎሞን "ኃጢአቱን (ስሕተትን) የሚሰውር (የማያምን) አይለማም፤ የሚናዘዝባት (የሚያምን) የሚተዋትም (ስሕተትን የማይደግም) ምሕረትን ያገኛል" ብሏል፡፡ ምሳ. ፳፰÷፲፫፡፡

## ማጠቃለያ

ስሕተትን ማመን ፍጹም ያልሆነ ደካማ ሥጋ መልበሳችንን ከማመን ይመነጫል፡፡ ስሕተትን ማመን በራስ መፍረድና በንሰሐ መመለስ ነው፡፡ ስሕተትን አለማመን ሌላ ስሕተትን ያስጨምራል፡፡ የሚሠራ ይሳሳታል፤ ትልቁ ስሕተት አለመሥራት ነው፡፡ ስሕተትን ማመን ትልቅነት ነው፡፡

## ተግባር

- መምህሩ ወጣቶች በምንም ሁኔታ ስሕተትን በማመን መስተካልን እንዲመርጡ ይምከራቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ወጣትነት (አካላዊ ዕድገት) ፩

**የትምህርቱ ዓላማ:-** ወጣቶች ስለ ወጣትነት ጠባያት እንዲገነዘቡ ማድረግ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ:-** "ኢየሱስ በጥበብና በቁመት በሞገስም በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ያድግ ነበር፡፡" ሉቃ. ፪÷፶፪

**ተጨማሪ ምንባብ:-** ፩ሳሙ. ፪÷፳፮

## መግቢያ

- በወጣትነት የሚታዩ አካላዊ ለውጦች ምንድን ናቸው?
- አካላዊ ለውጦቹ ለምን ተከሠቱ?

## የሳምንቱ ትምህርት

ሰው የልጅነት፣ የወጣትነትና የሽምግልና ዘመናትን ያፈራርቃል፡፡ ልጅነቱን ሳያስተውለው፤ ወጣትነቱን ሳይረዳው፤ ሽምግልናውን ሳይቀበለው ይኖራል፡፡ ሰው በልጅነትና በወጣትነት ወራቱ በተስፋ፤ በሽምግልና ወራቱ ደግሞ በትዝታ ይኖራል፡፡

ወጣትነት የልጅነትና የሽምግልና ድልድይ ነው፡፡ በወጣትነት ጊዜ አካላዊ፣ ሥነ-ልቦናዊ፣ ማኅበራዊ ለውጦች ይታያሉ፡፡ ሰውነታችን አካላዊ እድገት ያመጣል፡፡ ይህ እድገት የሚመጣው ጊዜውን ጠብቆ ነው፡፡ ለውጡ የተፈጥሮ ሕግን ተከትሎ የመጣ ነው፡፡ እድገት በጊዜው አስፈላጊ ነው፡፡ እድገታችን ግን የሥጋ ግዝፈት ላይ ብቻ ሳይሆን የመንፈሳዊነት ልዕልናንም ሊያጠቃልል ይገባል፡፡ እድገት ዘርፈ ብዙ ነው፡፡ ዛፍ በሁሉም አቅጣጫዎች እንደሚያድግ ሁሉ እድገታችንም ዘርፈ ብዙ መሆን አለበት፡፡ የወጣትነት አካላዊ እድገት የሰውነት መስፋፋት፣ የድምፅ ለውጥ (መጎርነን መቅጠን)፣ በተለያዩ የሰውነታችን ክፍሎች ፀጉር መውጣት፣ የአዳማዊ (የሔዋናዊ) አቅም ማደግ፣ የውበት በሞገስ መገለጥና የቁመት መጨመርን ያጠቃልላል፡፡

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በየጥቂቱ እንደሰው በማደጉ በጥበብና በቁመት በሞገስም በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ተገለጠ፡፡ ሉቃ. ፪÷፶፪፡፡ በክርስቶስ እድገት ውስጥ አካላዊ እድገት ነበር፡፡ አካላዊ እድገት ብቻውን በቂ ስላይደለ በጥበብም ያድግ ነበር፡፡ አካላዊ እድገት የፍጥረታዊው ሰው ማንነት መጎልመስ ነው፡፡ ይህ የተፈጥሮ ሕግ ነው፡፡ በጥበብና በሞገስ ማደግ ደግሞ መንፈሳዊ እድገት ነው፡፡ ሰው በሥጋም በመንፈስም ካደገ በሰውና በእግዚአብሔር ፊት ውበት ይኖረዋል፡፡

www.zeorthodox.org

የእኛ ውበት ሚዛን የሚደፋው በሰው ፊት ብቻ ነው፡፡ በእግዚአብሔር ፊት ሚዛን የሚደፋው መንፈሳዊነት ነው፡፡ ማደጋችን በነገር ሁሉ እንዲገለጥ በጥበብና በሞገስ በሥጋና በነፍስ መሆን አለበት፡፡

## ማጠቃለያ

እድገት በጊዜው አስፈላጊ ነው፡፡ እድገታችን የሥጋ ግዝፈት ብቻ ሳይሆን በጥበብ የመንፈሳዊነትንም ልዕልና ያጠቃልላል፡፡ የወጣትነት አካላዊ እድገት ተፈጥሮአዊ ነው፡፡ ተፈጥሮአችንን በአግባቡ እንረዳ፡፡

## ተግባር

- "በወጣቶች ሕይወት አካላዊ እድገትን ተከትለው የሚመጡ ፈተናዎች" በሚል ርእስ መምህሩ ወጣቶችን ያወያያቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ወጣትነት (የጉልምስና ጊዜ) ፪

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች እግዚአብሔርን የወጣትነታቸው ውበት መሆኑን ተገንዝበው መልካም የሆነውን ሁሉ እንዲያደርጉ መምከር፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** "የጭንቅ ቀን ሳይመጣ በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ፡፡" መክ. ፲፪÷፩

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ፪ጢሞ. ፪÷፳፪

## መግቢያ

- የጉልምስና ጊዜ የትኛውን የዕድሜ ክልል ይመለከታል?
- ጉልምስናን ተከትለው የሚመጡ ፈተናዎች ምንድን ናቸው?
- የጎልማሶች ሥራ ምንድን ነው?

## የሳምንቱ ትምህርት

ወጣትነት በሥጋ የምንጎለምስበት፤ አካላዊ፣ መንፈሳዊ ሥነ-ልቦናዊና ማኅበራዊ እድገቶች የሚያስውቡት ጊዜ ነው፡፡ ወጣትነት የኃይል፣ የውበት፣ የጥበብና የዕውቀት ሕይወት ሲሆን እግዚአብሔርን የምናስብበት ወራት ነው፡፡ ሮጠን መቅደም፣ ታግለን መጣል የማንችልበት የጭንቅ (የሽምግልና) ወራት በጊዜው ይመጣል፡፡ ጭንቁ ሳይመጣ ከጭንቁ መውጫ መፍትሔ የምናበጅበት ጊዜ ደግሞ ወጣትነት ነው፡፡ በወጣትነት አእምሮአችን ያሰብነው፣ በጽኑ እምነት መመኪያችን አድርገን በሙሉ ኃይል ያገለገልነውና የውበታችን ባለቤት ያደረግነው እግዚአብሔር በሽምግልናችን ወራት ጌጥና አክሊል፤ በጭንቁ ወራት መፍትሔ ይሆነናልና፡፡

የወጣትነት ጊዜ የጉልምስና ጊዜ በመሆኑ የአመለካከት፣ የጠባይና የአካል ለውጦች ይታዩብናል፡፡ ጉልምስናን ተከትለው የሚመጡ ፈተናዎችም አሉ፡፡ ፈተናዎቹ ከራሳችን፣ ከሰዎችና ከሰይጣን ሊመነጩ ይችላሉ፡፡ የጉልምስና ጊዜ ትልልቅ ፈተናዎች ዝሙት፣ አባካኝነት፣ ተስፋ መቁረጥ፣ ሱስና ቁማር የመሳሰሉት ናቸው፡፡ የጉልምስና ጊዜ ስሜታችንን የምንከተልበት ጊዜ ነው፡፡ የሥጋን ስሜት በመንፈስ ፈቃድ ካልገታነው ቅን በሚመስል መንገድ ወደሞት ይመራናል፡፡ የጉልምስና ጊዜ በፍጹም ጥንቃቄና ማስተዋል የተመራ መሆን አለበት፡፡

www.zeorthodox.org

የጉልምስናን ጊዜ ካላወቅንበት ጎድቶንና መጥፎ ትዝታ አትሞብን ሊያልፍ ይችላል፡፡ ማንነታችንን ከሚጎዱ፣ መንፈሳችንን

ከሚያረክሱና ሰብእናችንን ከሚያሳድፉ ነገሮች መራቅ ያስፈልገናል፡፡

የጉልምስና ጊዜ በቃሉ መመራት አለበት፡፡ ጎልማሳ መንገዱን የሚያነፃው ሕጉን በመጠበቅ ነውና፡፡ መዝ. ፻፲፰÷፱፡፡ **የወጣትነት ጊዜ እንደ አቤል በየዋህነት**፤ እንደ ይስሐቅ በታዛዥነት፣ እንደ ዮሴፍ በራእይና በይቅርባይነት፣ እንደ ዳንኤል እግዚአብሔርን በማምለክ፣ እንደ ሦስቱ ወጣቶች በጽናት፣ እንደ ዮሐንስ መጥምቅ በአገልግሎትና እንደ ዮሐንስ ወንጌላዊ እግዚአብሔርን በመውደድ ማበብ አለበት፡፡

## ማጠቃለያ

የጉልምስና ጊዜ በፍጹም ጥንቃቄና ማስተዋል መመራት ስላለበት፡፡ ስሜታችን እንዳይገዛን በመንፈስ ፈቃድ ለመመራት መዘጋጀት አለብን፡፡ የወጣትነትን ወራት ለጭንቁ ወራት መልካም ፍሬ ሳናፈራበት እንዳያልፍ በጥንቃቄና በማስተዋል የተሰጠንን ዘመን /ዕድሜ/ በአግባቡ ተጠቅመን እግዚአብሔርን ደስ በሚያሰኝ ነገር ለመምራት መትጋት አለብን፡፡

## ተግባር

- መምህሩ "ጉልምስናን ተከትሎ የሚመጡ ፈተናዎችን እንዴት ድል እንንሣ?" በሚል ርእስ ወጣቶቹን ያወያያቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ወጣትነት (ራስን መቀበል) ፫

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ራሳቸውን እንዲያውቁና ማንነታቸውን እንዲቀበሉ መምከር፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** “ማደግህ በነገር ሁሉ እንዲገለጥ ይህን አስብ፡፡” ፩ጢሞ. ፬÷፲፭

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** መዝ. ፻፴፰÷፲፬

## መግቢያ

- ራስን መቀበል ማለት ምን ማለት ነው?
- ወጣቶች ራሳቸውን ለመቀበል የሚቸገሩት ለምንድን ነው?
- ራስን የመቀበል ፍሬ ምንድን ነው?

## የሳምንቱ ትምህርት

ወጣቶች ራሳቸውን ለመቀበል ይቸገራሉ፡፡ ራሳቸውን መቀበል ያልቻሉ ሰዎች የማንነት ኪሳራ ይገጥማቸዋል፤ የሕይወትን ትርጉምና የተፈጥሮን ውበት ማወቅ አይችሉም፤ በጉዟቸው ስኬታማ አይሆኑም፡፡

ራስን መቀበል ማለት በዚች ዓለም ላይ ይህ ሰውነት፣ አካል፣ ውበት፣ መልክና ሁለመና የእኛ/የእኔ/ ብቻ መሆኑን ተገንዝበን፤ የሆነውን ማንነት በደስታ መቀበልና ማክበር ማለት ነው፡፡ ባለን ውበት፣ የሰውነት አወቃቀርና ቁመት አለማፈር፤ የተወለድንበትን ቤተሰብና ሃገርን በደስታ መቀበል ማለት ነው፡፡ ንጉሥ ዳዊት “ግሩምና ድንቅ ሆኜ ተፈጥሬአለሁና ለዘላለም አመሠግንሃለሁ” በማለት ራሱን በመቀበል ስለ ውበቱ እግዚአብሔርን አመሰግኗል፡፡ መዝ. ፻፴፰÷፲፬፡፡ ራስን መቀበል ትልቅነት ነው፡፡ እግዚአብሔር የሰጠንን ሰውነት፣ ውበትና ቁመት በደስታ ተቀብለን እንደ ዳዊት ማመስገን አለብን፡፡ ጠቢቡ “ጥቁር ነኝ ነገር ግን ውብ ነኝ” ማለቱ ባለው መደሰቱን ያሳያል፤ ጥቁርነቱን አላፈረበትም፡፡ መኃ. ፩÷፭፡፡

ራስን መቀበል አለመቻል የሚያስከትለው ችግር፡-

www.zeorthodox.org

- ለራሳችን ያለንን አመለካከት ያዛባል፡፡
- ተስፋ መቁረጥን ያስከትላል፡፡
- ራስን መጥላትና ማጥፋት ሊያስከትል ይችላል፡፡
- በማንነታችን እያፈርን ከማኅበረሰቡ እንድንርቅ ያደርጋል፡፡

- ማኅበራዊና መንፈሳዊ ሕይወታችንን ያበላሻል፡፡
- የበታችነት ስሜት እያደረብን ጥቅም እንደማንሰጥ ስለምናምን ለስኬት እንዳንነሣ ያደርጋል፡፡

ራስን መቀበል አለመቻል የሚመነጨው ራስን ከሌሎች ጋር ከማነፃፀር ነው፡፡ ከእግዚአብሔር የተሰጠን መልክ፣ ውበትና ሁለመና የራሳችን ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ ራሳችንን (የሆነውን ማንነት) በጸጋ ተቀብለን በደስታ መኖር ስንጀምር በተሰማራንበት ስኬታማ እንሆናለን፡፡ በራስ መተማመንን እናዳብራለን፤ በሆነው ማንነት እግዚአብሔርን ማመስገን እንችላለን፡፡ ጳውሎስ "የተሰጠህን የጸጋ ስጦታ ቸል አትበል፤ ማደግህ በነገር ሁሉ እንዲገለጥ ይህን አስብ" በማለት ጢሞቴዎስን መክሮአል፡፡ ፩ጢሞ. ፬÷፲፫፡፡

## ማጠቃለያ

ራስን መቀበል በደስታ እንድንኖርና በተሰማራንበት ሁሉ ስኬታማ እንድንሆን ያደርገናል፡፡ ራስን መቀበል የምስጋና ምክንያት ይሆናል፡፡ ራስን አለመቀበል ደግሞ ራስን መጥላት ሊያስከትል ይችላል፡፡

## ተግባር

- "ወጣቶች ራሳቸውን ለመቀበል ለምን ይቸገራሉ" በሚል ርእስ መምህሩ ያወያያቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ዋቢ መጻሕፍት

- ሃብተማርያም ወርቅነህ (ሊቀ ሥልጣናት)፣ ጥንታዊ የኢትዮጵያ ሥርዓተ ትምህርት፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ቀ.ኃ.ሥ ማተሚያ ቤት፣ 1963 ዓ.ም
- ሃይማኖተ አበው፣ አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ 1986 ዓ.ም.
- አባ መልከ ጼደቅ (ሊቀ ጳጳስ)፣ ትምህርተ ክርስትና፣ አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ 1984 ዓ.ም፡፡
- አባ ጎርጎርዮስ (ሊቀ ጳጳስ)፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1974 ዓ.ም፡፡
- ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን (አዘጋጆች)፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እምነት፣ ሥርዓት አምልኮና የውጭ ግኙኙነት፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ 1988 ዓ.ም.
- ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን (አዘጋጆች)፣ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ትናንትና ዛሬ፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 1990 ዓ.ም.
- ሉሌ መልአኩ (መምህር)፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1997 ዓ.ም፡፡
- መሐሪ ትርፌ (ሊቀ ሊቃውንት)፣ መጽሐፈ ሐዲሳት ሠለስቱ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ አርትስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1989 ዓ.ም፡፡
- መጽሐፈ ስንክሳር፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1983 ዓ.ም
- መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1988 ዓ.ም፡፡
- መጽሐፈ ስንክሳር፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1983 ዓ.ም
- መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1988 ዓ.ም
- ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1988 ዓ.ም
- ዳኛቸው ካሳሁን (መልአከ ሰላም)፣ ክርስቲያናዊ ሥነ-ምግባር፣ አዲስ አበባ፣ ማኅበረ ቅዱሳን፣ 2003 ዓ.ም.
- ደረጀ ጅማ (መጋቤ አእላፍ)፣ ምን ያስጨንቃችኋል ክፍል ፪፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 2002 ዓ.ም፡፡
- መጽሐፍ ቅዱስ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980 ዓ.ም
- ሐረገ ወይን ቸርነት፣ ሴትና አህያ፣ አዲስ አበባ፣ 2005 ዓ.ም፡፡
- ምክረ ሥላሴ ገብረ አማኑኤል (ዶ/ር)፣ ጠቅላላ የቤተክርስቲያን ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ 2000 ዓ.ም.
- ኀሩይ ኤርምያስ (መምህር)፣ መዝገበ ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ 2002 ዓ.ም
- የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣ አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ 1996 ዓ.ም፡፡
- ቸርነት አበበ (መምህር)፣ የመጽሐፍ ቅድስ ጥናት፣ አዲስ አበባ፣ 2003 ዓ.ም
- H.G. Bishop Moussa; The Characteristics of Orthodox Teaching; Bishopric of

www.zoorthodox.org

Youth; Harmony Press, 2007.
- H.G. Gishop Mouusa, An Introduction to the New Testament, Bishopric of youth, Dar EL Geel Press, 2001.
- H.G. Bishop Raphail, The Meaning of Miracles, Bishopirc of Youth, 2010.
- Sunday School Curriculum, Grade 1 to Grade 12. The Coptic Orthodox Diocese of The Southern USA.
- Sunday School Lessons, Class 1 to Class 10, E.O.T.C Latin America Diocese.
- በጠቅላይ ቤተ ክህነት፡፡ 2000 ዓ.ም፡፡ የኢትዮ. ኦርቶ.ተዋ. ቤ.ክ ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፻ ዓ.ም፡፡ አዲስ አበባ ፣ ሜጋ ማተሚያ ቤት
- ምክረ ሥላሴ ገብረ አማኑኤል (ቀሲስ፤ዶ/ር)፡፡ 2000፡፡ በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም በግዕዝ ቋንቋ ፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ
- የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፡፡ 1996 ዓ.ም፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡
- ጎርጎርዮስ(ብፁዕ አቡነ)፡፡ 1996 ዓ.ም፡፡ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፡፡
- መሐሪ ትርፌ (በሊቀ ሊቃውንት)፡፡ 19 ዓ.ም፡፡ የጳውሎስ መጽሐፍ ንባቡና ትርጓሜው፡፡ አዲስ አበባ፡፡
- ዳንኤል ተሾመ፡፡ 19 ዓ.ም፡፡ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ሊታወቁ የሚገባቸው መሠረታዊ ጉዳዮችና የትርጉም ስልቶች፡፡ አ.አ
- Pulpet ; 19 A.D; Bible commentary The Epistle of paul to the ROMAN;
- Tadros Yakob Malaty (Father); 2007-2008 A.D; The Epistle of Saint Paul to the Romans; Alexandria,Egypt.
- መብራቱ ኪሮስ (ዲያቆን)፡፡ አጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ፡፡ የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ያልታተመ መማሪያ፡፡
- ጎርጎርዮስ (በብፁዕ አቡነ)፡፡ 1981 ዓ.ም፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፡፡ አዲስ አበባ፡፡

www.zeorthodox.org

- ምክረ ሥላሴ ገብረ አማኑኤል (ቀሲስ ፤ ዶ/ር )። 2001። የእግዚአብሔር መንግሥት ታሪክ 1ኛ እና 2ኛ። አዲስ አበባ።
- Lule Melaku (Asst. Professor); 2010; History of the Ethi. Orthodox Tewahido Church; A.A ; Elleni p.p.plc.
- ሰሎሞን መላኩ(ዲያቆን)። 2001ዓ.ም። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ወርቃማ ዘመናት። አዲስ አበባ። ባናዊ ማተሚያ።
- Syrian Sunday school curriculum.
- Introduction to Coptic orthodox Church ; Father Tadros Y Malaty
- Ian Gillman,Hans-Joachim Klimkeit ; Christian in asia before 1500 ;
- ዜና ሐዋርያት
- ገድለ ቅድስት አርሴማ
- ሺኖዳ(ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ) ቅንዓት
- የኢትዮፕያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ.ክ ፤ ስንክሳር ፤ በትንሳኤ ዘጉባዔ ማተሚያ
- ያሬጋል አበጋዝ (ዲ/ን)። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ሕይወቱና ትምህርቱ ፤ አዲስ አበባ
- በጌታቸው ኃይሌ(ፕሮፌሰር)። 1997 ዓ.ም። የአባ ባሕርይ ድርሰቶች
- ዳንኤል ክብረት(ዲ/ን)። 1998ዓ.ም። የቤተ ክርስቲያን መረጃዎች። አዲስ አበባ። ሜጋ ማተሚያ ቤት።
- .........። አዋልድ መጻሕፍት። ሐመረ ተዋሕዶ።
- Douglas J.D and Tenney M.c (1987) New International BIBLE DICTIONARY. ZONDERVAN'S.Grand Rapids,MICHIGAN USA
- Holy Trinity College.(2004) Patrology፡ Holy Trinity College module/ unpublished./
- Malaty T.Y( Father)Patrology ;
- Malaty T.Y( Father).(199). Tradition and Orthodoxy. Alexandria .Egypt.
- ማኅበረ ቅዱሳን። 2004 ዓ.ም። ቤተ ክርስቲያንህን እወቅ። አዲስ አበባ። የማዕረግ ቃል

www.zeorthodox.org

ማተሚያ ቤት፡፡
- ነገረ ማርያም
- Shenoda - Pope (1999). The Holy virgin Saint Mary. Cairo,Egypt.
- ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት፡፡ (1988) ወንጌል ቅዱስ ትርጎሜ፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ብሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት
- የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ትምህርት ቤት መማሪያ ፤ ካናዳ
- ሺኖዳ ሰው ምንድነው ፤ በብጹዕ ወቅዱስ፤
- ክርስቲያን አንትሮፖሎጂ
- ሺኖዳ (ብጹዕ ወቅዱስ ፤ አቡነ)፡፡ መንፈሳዊው ሰው
- John Mark (Father). 19 . Ascending the heights ; A lay man guide to the ladder of divine ascent
- አበራ (በሊቀ ጉባዔ ፤ አባ)፡፡ 1996 ዓ.ም፡፡ ትምህርተ ሃይማኖትና ክርስቲያናዊ ሕይወት፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ማኅበረ ቅዱሳን፡፡
- ሰሎሞን ሙሉጌታ (ቀሲስ)፡፡ 200 ዓ.ም፡፡ መሸኮርመምና ማሸኮርመም፡፡ በቦሌ ደብረ ሳሌም የረቡዕ ጉባዔ የተሠጠ ስብከት በzeorthodox.org የተለቀቀ ጽሑፍ፡፡ አዲስ አበባ
- ሰሎሞን ሙሉጌታ (ቀሲስ)፡፡ 2000 ዓ.ም፡፡ ቅድመ ጋብቻ፡፡ በቦሌ ደብረ ሳሌም የረቡዕ ጉባዔ የተሠጠ ስብከት በzeorthodox.org የተለቀቀ ጽሑፍ፡፡ አዲስ አበባ
- ተስፋ ገብረ ሥላሴ፡፡ 1988፡፡ መጽሐፍተ መነኮሳት፡፡ አዲስ አበባ
- ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፡፡ መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት፡፡
- ጥዑመ ልሳን፡፡() ያሬድና ዜማው፡፡ አዲስ አበባ፡፡
- ሙሳ (ሊቀ ጳጳስ)፡፡ ወጣትነትና የቅድስና ኑሮ፡፡ በመምህር ወንድወሰን ሶርሳ የተተረጎመ፡፡

www.zeorthodox.org